

# ምዕራፍ ፮

## ደጃች ታየ ጉልላቴ

ከዳግማዊ ምኒልክ ቀጥሎ መንገሥ የነበረበት ትክክለኛው ሰው እያለ ሌሎች የነገሡት ያለአግባብ እንደነበረ የሚተቹ በወቅቱ ቢኖሩም የኃይል ሚዛኑን እያዩ ነገሩን ከማራገብ ተቆጥበዋል።

ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ስድስቱ ወንዶች ልጆች መካከል አንዱ መርዕድ አዝማች ኃይሌ ሲሆኑ የሳቸውም ልጅ ከወይዘሮ እንጀሪ የተወለዱት ፊታውራሪ ጉልላቴ ኃይሌ ናቸው። ፊታውራሪ ጉልላቴ ኃይሌ አፄ ምኒልክን ከቤት ሠራተኛ በመወለዳቸው ይንቋቸው ነበርና አፄ ምኒልክ ገና ከሩቅ ብቅ ሲሉ ተነስተው ይቆሙ ነበር። አፄ ምኒልክም "እዩት ጉልላቴን ቀድሞ የሚነሳው እኮ እኔ ስደርስ ኖር ብሎ እንዳይነሳልኝ ማሳሳቱ ነው" እያሉ ለሰዎች ይናገሩ ነበር። ፊታውራሪ ጉልላቴ ኃይሌ መንገሥ ይመኙ ስለነበረና ምኒልክም ስለተጠራጠሩ አስረዋቸው እንደነበረም ይተረካል።

ከዳግማዊ ምኒልክ በኋላ ከሌሎቹ ዘውዱን ለመረከብ ከተሰለፉት መኳንንቶች ይልቅ ልጅ ታየ ጉልላቴ የሚለዩት ውልደታቸው ቀጥታ የሣህለ ሥላሴ የወንድ የልጅ ልጅ ስለሆኑና ሌሎቹ ራስ ተፈሪንም ጨምሮ ተወላጅነታቸውን የሚቆጥሩት በእናታቸው ወይም በሴት አያታቸው በኩል ስለኾነ ነው። ይህንኑ በመገንዘብ እቴጌ ጣይቱ የወንድማቸውን የራስ ወሌን የልጅ ልጅ አልማዝ መንገሻን ለልጅ ታየ ጉልላቴ ድረውላቸው የሠርጉ ሥነ ሥርዓት በቤተ መንግሥት ተከበረ። የዚህን ጊዜ አዝማሪ በዘፈንና በቀረርቶ ስማቸውን እያገነነ የሚከተለውን ገጥሞላቸዋል።





ደጃች ታዬ ጉልላቴ

ቀና ብዬ ባየው አፈሰሰ ቤቴ
መጥቶህ ከደነልኝ ታዬ ጉልላቴ

የእቴጌ ጣይቱ መሻርና የዘውዱ አወራረስ መሽጋሸግ በአድማ የተቀነባበረ ስለነበረ እንቅፋት ይሆናል ተብሎ የተጠረጠረውን ግለሰብ መከታተል ወይም ማጥፋት አስፈላጊ ስለነበረ ልጅ ታየ ጉልላቴን የልጅ ኢያሱ እንደራሴ ራስ ቢትወደድ ተሰማ ሥልጣን በያዙ በአራተኛው ቀን አስረው ወደ ወሎ ላኩና ልጎት በተባለ አምባ በእስረኛነት እንዲቀመጡ አደረጉ። በዚህም አምባ እስከ ስገሌ ዘመቻ ዘመን ድረስ ታስረውበታል። በኋላም ደጃዝማች ተብለው የጊሚራ ገዥ በመሆን ለሃያ አንድ ዓመት ርቀው እንዲቀመጡ ሆኗል። ለሹመታቸው የተሰጠው ምክንያት ደጃች ታየ ጉልላቴ በምኒልክ ጊዜ የጠመንጃ ጥገና በደንብ ተምረው ስለነበረና እሳቸውም ከሺ ጠመንጃ ጋር የሰለጠነ ሠራዊት ስለነበራቸው ጠረፍ ይጠብቅ የሚል ነው። ደጃች ታየ በፋንታቸው ቀኛዝማች መላኩንና ወይዘሮ አመዘነችን ይወልዳሉ።



ቀቅኛዝማች መልአኩ ታዬ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የደጃች ታዬን ልጅ መልአኩ ታየን እኔ ከልጆቼ ጋር ላሳድገው ብለው ወስደውት ነበር። መልአኩ ታየ ብልህና ቀልጣፋ ስለነበረ ከንጉሡ ልጆች ጋር በሚያድግበት ጊዜ ከነሱ በመልከም ጭምር በልጦ ይታይ ነበር። የእናቱን መልክ ቢይዝም ገጽታው ግን ቅድመ አያቱን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴን ይመስላል። ፈረስ ግልቢያም ይወድ ነበር።

እንደዚሁም በዚያን ጊዜ መልአኩ ልጆች ቀበና ወንዝ ውስጥ ይጫወቱ ስለነበረ አብሮ መጫወት ያዘወትር ነበር። አንድ ጊዜ ባልታወቀ ምክንያት የወንዙ ውሃ ተበክሎ ኖሮ ብዙ ልጆች በዚሁ ሰበብ ሲሞቱ ሌሎችም በተለያዩ በሽታዎች ተለከፉ። መልአኩ ደግሞ ቀኝ ክንዱ ላይ እንደ ብጉንጅ ዓይነት ነገር ስለወጣበት ንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታል ገብቶ መታከም ጀመረ። ሆስፒታል ውስጥ እንዳለ ህመሙ ጠንቀኛ ስለሆነ ቀኝ እጁ ይቆረጥ ሲባል ወላጅ እናቱና ራሱ መልአኩ አይቆረጥም ብለው ስለተከላከሉ መቆረጡ ቀርቶ በመድኃኒት ህክምና ብቻ ዳነ። ከዚህ ወቅት አንስቶ ቀኝ እጁ ስልል ብሎ ቀረ።




አቶ ግርማ መልአኩ

በወንድ ልጅነት ለንግሥናው የሚቀድሙት እኚሁ ቀኛዝማች መልአኩ መኾናቸው ስለሚታወቅ የጁ ላይ በአውራጃ አስተዳዳሪነት በተሾሙ ጊዜ ሕዝቡ "የአራት ንጉሥ ልጅ እያለ ሌላ አይነግሥም" ብሎ እሳቸውን ለማንገሥ ፈልጎ ስለአመጸ አገሩ በአይሮፕላን ተደበደበና ነገሩ ከሸፈ። በዚህም ምክንያት ተይዘው መጥተው ሲታሰሩ ለአራት ዓመት ሲሚንቶ ላይ ይተኙ ነበር። በዚሁ ጠንቅ ሳንባቸውን ታመው እያሉ



በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ፣ በልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንና በልዑል መኮንን አማላጅነት ከእስር ተፈቱ። ይሁንና ዕድሜያቸውን በአውራጃ ገዥነት፣ በዳኝነት፣ በደጃጅ ጠኝነትና በእስረኛነት ኖረው መጨረሻ ላይ በዚሁ በሽታ የተነሳ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። አቶ መልአኩ የሁለት ልጆች አባት የነበሩ ሲሆኑ እነሱም አቶ ግርማ መልአኩና ወይዘሮ አልማዝ መልአኩ ናቸው።



አቶ ዓቢይ ግርማ

የመልአኩ ልጅ የሆኑት አቶ ግርማ በግል ሥራ ሲተዳደሩ ኖረው በተወለዱ በ70 ዓመት ዕድሜያቸው መጋቢት 1 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው የካ ሚካኤል አስከሬናቸው አረፈ። አቶ ግርማ የሦስት ሴት ልጆችና የአንድ ወንድ ልጅ አባት ነበሩ። የሦስቱ ሴቶች ልጆች ስም ወይዘሮ አስቴር፣ ወይዘሮ ቆንጂትና ወይዘሪት እሴተ ሲሆኑ ወንዱ ልጅ ዓቢይ ግርማ ነው።

የአልጋው ቀጣይ መሆን የሚገባው ልጃቸው አቶ ዓቢይ ግርማ በአሁኑ ወቅት ወጣት ሲሆን የሚኖረው ካናዳ አገር በኩቤክ ውስጥ ነው። አቶ ዓቢይ ግርማ ትዳር ያልመሠረተና አባትየውም ወንድ ልጃቸው እሱ ብቻ ስለኾነ እንዲያገባና ወንድ ልጅ እንዲወልድ በሕይወት እያሉ በጣም ይመኙ ነበር።

# ምዕራፍ ፯

## ጎረምሳው አቤቶ ኢያሱ

የአቤቶ ኢያሱ እናት ሸዋረጋ ከእናትዋ ከወይዘሮ ደስታና ከዳግማዊ ምኒልክ ኃይለ መለኮት በድብቅ ተወለደች። ወይዘሮ ደስታ ቤተ መንግሥት ውስጥ ጠጅ ክፍል ስትሠራ የኖረች ቀይ ወፍራምና ቆንጆ ሴት ነበረች። እርግዝ በነበረበት ጊዜ ሸሽታ ወደ ወሎ ሄዳ ስትኖር ልጇን ሸዋረጋን ወልዳ፣ አሳድጋ ዳረች። ሸዋረጋም ወታደር ባሏን አግብታ ወደ ሐረርጌ ሄደች።

የሸዋረጋ ባል ከአንገቷ ላይ የማይለየውን ክታብ ስለተጠራጠረ ሚስቱን አግባብቶ ክታቡን ከፍቶ ሲያነበው የዳግማዊ ምኒልክ ልጅ መሆንዋን ይገነዘባል። እሱም ይደነግጥና ትንሽ ካሰበበት በኋላ ድሃ ወታደር ስለነበረ ሊሾም ሊሸለም ፈለገና ሚስቱን ወስዶ ለእቴጌ ጣይቱ ምስጢሩን አስረድቶ ይሰጣቸዋል። እቴጌ ጣይቱ ልጅቷን ይቀበሉና በድብቅ ወደ ቤተ መንግሥት አስገቧት። ከዚያም ልብስ አለባብሰው ከሌሎች ሴቶች ጋር አሰባጥረው አፄ ምኒልክን እጅ እንዲነሱ አስልፈው አቀረቧቸው። አፄ ምኒልክ ግን ከሌሎች ልጆች መካከል ትክ ብለው ሸዋረጋን ይመለከቱና "ይቺ የማነች ልጅ?" ብለው ቢጠይቁ የወይዘሮ ደስታ ልጅ መሆንዋ ይነገራቸዋል። ከዚያ ቀን በኋላ ልጅቷ ቤተ መንግሥት መኖር ጀመረች። ከጊዜ በኋላ ጉዳዩ ግልጽ እየኾነና ልጅቷም እያማረባት በመሄዱ የመኳንንቱን ቀልብ መሳብ ጀመረች። ከዚያም የአፄ ምኒልክ አብሮ አደግ ለሆኑት ለራስ ጎበና ዳጬ ልጅ ለወዳጆ ጎበና ተዳረች። መጨረሻ ላይ ግን የወሎውን ባላባት ራስ ሚካኤልን አገባች።

ልጅ ኢያሱ ከእናቱ ከአፄ ምኒልክ ሴት ልጅ ከወይዘሮ ሸዋረጋና ከወሎው ራስ ሚካኤል ዓሊ ጥር 25 ቀን 1888 ዓ.ም በወሎ ጠቅላይ ግዛት



ወረሂመኑ ተንታ ውስጥ ተወለደ። ስመ ክርስትናውም ክፍለ ያዕቆብ ተባለ።

የኢያሱ አባት ራስ ሚካኤል ወይም ክርስትና ከመነሳታቸው በፊት መሐመድ ዓሊ የተወለዱት ከኢማም ዓሊ አባቡላና ከግንደበረት ከተወሰደችው አገልጋይ ከወይዘሮ ጌቴ ነው። ግንደ በረት በምዕራብ ሸዋ ውስጥ የሚገኝ በባርያ ፍንገላ የታወቀ ወረዳ ነበር።

ልጅ ኢያሱ በአባቱ በኩል ከሌሎች እናቶች የተወለዱ እህቶችና ወንድሞች ነበሩት። እነሱም:-

| | |
|---|---|
| ደጃዝማች ደስታ | ደጃዝማች ዓሊ |
| ደጃዝማች ኃይለ ማርያም | ወይዘሮ ስሂን |
| ራስ ገብረ ሕይወት | ወይዘሮ ተዋበች ናቸው። |

ልጅ ኢያሱ ሰውነቱ ደልዳላ፣ ቁመቱ ዘለግ ያለና መልኩ የሚያምር ወጣት ነበር። እንደ አብዛኛው ወሎዬ ቤተ ዘመዶቹ መልከ መልካም ናቸው። ኢያሱ ገና በ12 ዓመቱ እቴጌ ጣይቱ የወንድማቸውን የራስ ወሌን የልጅ ልጅ የኾነችውን ጽጌ ሮማን መንገሻ ዮሐንስን በ8 ዓመቷ ድረውለት ነበር።

ዳግማዊ ምኒልክ ታመው በነበረበት ጊዜ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው የልጅ ልጃቸውን ልጅ ኢያሱን አልጋ ወራሻቸው መሆኑን አስታወቁ። ዕድሜው ገና 13 ዓመት ስለነበረ በልጅ ኢያሱ ስም ራስ ቢትወደድ ተሰማ አገር ሲያስተዳድሩ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ ዕድሜያቸውም ገፍቶ ነበርና በሚያዝያ ወር 1903 ዓ.ም ስለሞቱ ልጅ ኢያሱ ምትክ ይሾምልህ ቢባል "አሁን ትልቅ ነኝ ማስተዳደር እችላለሁ" ብሎ አሻፈረኝ አለ። ሆኖም ራስ አባተ ቧያለው እንደራሴ ለመሆን ሲሞክሩ ሌሎች ስላልተስማሙ አቤቶ ኢያሱ አገሩን ማስተዳደር ጀመረ። ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስና ሌሎችም የመስፍኑን ልጅነት እያዩ ያለሞግዚት አገር እንዲያስተዳድር የተስማሙት በእልህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከልብ እንደማይደግፉትና ውድቀቱን እንደተመኙ ግልጽ ነው።

ልጅ ኢያሱ ጉርምስና የሚያጠቃው ባህሪ ስለነበረው ያያትን ቆንጆ ሁሉ ሥልጣኑን በመጠቀም ማግኘት ቻለ። ቆንጆ ትሁን እንጂ ባል ቢኖራትም ባይኖራትም ግድ አልነበረውም። ያንገራገሩትንም ሰዎች ራሱም ኾነ

አሽከሮቹ ይገድሉ ጀመር። ይህ ጠባዩ መኳንንቶቹንም አስከፍቷል። በተለይ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ይህንኑ አልወደዱለትም ነበር። አልፎ ተርፎም እሱ ራሱ ያወጣውን የሰዓት እላፊ አዋጅ እየሻረ ሌሊት ከአራዳ ዘበኞች ጋር ሲታኮስ ያድራል። እየዋለ እያደረ በየቦታው ከተለያዩ ጎሣ የባላባት ልጆች ሙስሊሟንም ክርስቲያንዋንም በዕቁባትነት ማስቀመጥ ጀመረ። አንዳንድ ሰዎች ልጅ ኢያሱ ከእያንዳንዱ ጎሣ መካከል በመውለድ አንድነትን ለማስፊን ሃሳብ ነበረው ይላሉ።



ልጅ ኢያሱ ከሞግዚቱ ከራስ ቢትወደድ ተሰማ ጋር

ልጅ ኢያሱ ገና ዘውድ ሳይጭን አባቱን ራስ ሚካኤልን የወሎ፣ የትግሬና የጐጃም ንጉሥ አድርጎ ሲሾም በሌላ ወገን ግን የሸዋ መኳንንቶችን ያዋርድና ያርቅ ነበር።

ልጅ ኢያሱ ለስድስት ዓመት ያህል በመንግሥቱ ሥልጣን ሲያዝበት ቆይቶ ተቃዋሚዎች ተነሱበት። ከተወነጀለባቸው ጥፋቶች መካከል አንዱና ወንኛው ሰልሟል የሚለው ነበር። የተቃዋሚዎች ኃይል ጫና እየከበደው በሄደ ጊዜ ልጅ ኢያሱ ሐረር ሄዶ ከሶማሌና ከአፋር ባላባቶች ጋር ይመክር ጀመር። ልጅ ኢያሱ ሐረር ላይ ሆኖ ተፈሪን



ከሐረር ሽሮ ወደ ከፋ በሹመት እንዲሄዱ ቢያዝም አንዴ ከረምቱ ይለፍልኝ፣ አንዴ አልተዘጋጀሁም፣ እያሉ ሰበብ ይፈጥሩ ነበር። እንዲያውም በየጧቱ በየመኳንንቱ ቤት እየሄዱ ይወያዩ ነበር።

በልጅ ኢያሱ መወንጀል ያልተስማሙ ነበሩ። እነዚህም ደጃች ባልቻ፣ ሊጋባ በየነና ሌሎችም እንደሆኑ ይታወቃል። ልጅ ኢያሱ በተወነጀለበት ሁሉ ጥፋተኛ መሆኑ ሙሉ በሙሉ አልታመነበትም። እንዲያውም ግፊት ሲበዛ መጨረሻ ላይ መቀበል ግድ ሆነባቸው እንጂ፣ ሊቀ ጳጳሱ መስለሙን "አላምንም!" ብለው አስቸግረው ነበር። ሆኖም ግን የነበሩት ተቃዋሚዎች መጨረሻ ላይ አብረው እንዲያድሙ ተገደዋል።

ልጅ ኢያሱ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችንና ሙስሊሞችን እኩል የአገር ፍቅር እንዲኖራቸው ብሔራዊ ስሜታቸውን እያነሳሳ ኃያል መሪ ለመሆን ጥረት አድርጓል። ለክርስቲያኑ ቤተ ክርስቲያን ሲያሠራ ለሙስሊሙም መስጊድ አሠርቷል። በወቅቱ ስለእሱ የሚናፈሰው ወሬ ለሙስሊሞች ያደረገው ብቻ እንጂ ለክርስቲያኖች የሠራው አይወራም ነበር። ይሁንና የአዲስ አበባ ቀጨኔ መድኃኔ ዓለምና የሐረር መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን አሠርቷል። የእህቱ የወይዘሮ ስሂን ሚካኤል፣ የልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን፣ የእመቤት ሆይ ዓለም ፀሐይ ኢያሱ፣ የወይዘሮ እስተዳር ገብረ ሕይወት ሚካኤልና የሌሎች ተወላጆቹ መቃብር ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም አሁን የቤተ ክህነቱ የገንዘብ ቤት በመሆን የሚያገለግለው መቃብር ቤት ነው። ጃንሆይም በዘመናቸው የማይገኙበት ይኸው የቀጨኔ መድሃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ነበር።

የቅርብ አሽከሮቹ በሙሉ ከእሱ ሕይወት በኋላም ሁሉ አለመስለሙን ይምሉ ይገዘቱ ነበር። ወይዘሮ አስካለ ማርያም ጆቴን አስልሞና ሙሚና አሰኝቶ አግብቷል የተባለውን ወይዘሮዋ እንዳልሰለሙ ልጃቸው ወይዘሮ ጽጌ ሻረው በኋላ ላይ አስተባብለዋል። በአንጻሩ ግን በጽሑፍ ጭምር የመሐመድ ዘር ነኝ ብሎ መስለሙን አውጆ ነበር እየተባለ ይጠቀሳል።

እንዲያውም የንጉሥ ሚካኤል እልፍኝ አሰከልካይ ደጃች ከበደ ወልደ ማርያም በአባቱ በንጉሥ ሚካኤልና በልጅየው በአቤቶ ኢያሱ መካከል ስለሃይማኖቱ ጉዳይ የነበረውን ውዝግብ ሰምተው ለሌሎች ሰዎች የሚከተለውን ተናግረዋል ይባላል። አቤቶ ኢያሱ አገልድሞ፣ ራሱ ላይ ጠምጥሞ፣ በትክሻው ድሪር አጥልቆ ድንገት ሲገባ "ምነው አንተ የአባትህን ሃይማኖት ትተህ ስለምክ?" ብለው ሲቆጡ

"የአባትህን ሃይማኖትስ የለወጥክ አንተ ነህ!" ብሎ አፀፋውን በቁጣ መልሶ ሄደ ብለው ተናገሩ ተብሏል።



አቤቶ ኢያሱ ሚካኤል

የአቤቶ ኢያሱ ሁኔታ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም በይፋ ግን ሃይማኖቱ ክርስቲያን መሆኑ ግልጽ ነው። መጨረሻ ላይ እንኳን እጁ የተያዘው ቅብጽያ ገዳም ውስጥ ተሸሽጎ ነበር። በጠቅላላው በአቤቶ ኢያሱ ላይ እበላ ባዩ ሁሉ የስም ማጥፋት ዘመቻ ሰላካሄዱበት የሚወዱት እንኳ በዘመኑ ደፍረው ሊከራከሩለት አልቻሉም።





ልጅ ኢያሱ በሰባት ዓመቱ ዳዊት ሲደግም

አባቱ ንጉሥ ሚካኤል መሻሩንና የተሻረበትን ምክንያት እንደሰሙ "እኔ እቆጣውና አርመው የነበረውን ሳያማክሩኝ እንዴት ከአባቱ ዙፋን ያወርዱታል" ብለው ተቆጡ። የንጉሥ ሚካኤል ክርስቲያንነት በጣም የጠለቀ ስለነበረ ቄሶች 'ያላመነና ያልተጠመቀ መንግሥተ ሰማያት አይገባም' እያሉ ሲነግሯቸው ለወላጆቻቸው ከመጨነቃቸው የተነሳ "ወላጆቼ ከመቃብር እንደገና ቢነሱ የክርስትና ሃይማኖት እንዲከተሉ አስጠምቃቸው ነበር በማለት አዘውትረው ይናገሩ ነበር ይባላል። በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ታላቁ ራስ ዓሊ ሴሩ ጓንጉል ተመሳሳይ አመለካከት እንደነበራቸው ተዘግቧል። በዚህ የተነሳ ንጉሥ ሚካኤል በክርስትና ሃይማኖት ፍቅር ልባቸው የነደደ መሆኑ እየታወቀ ልጃቸው ጭልጥ ብሎ የእስልምና ተከታይ ነበረ ለማለት ያስቸግራል።

ልጅ ኢያሱ አንዳንድ ተራማጅ የሆኑ አዋጆችን አውጥቷል። ለምሳሌ የሌባ ሻይንና የቁራኛ ፍርድን ከማስቀረቱም በላይ የባለርስትና የጭሰኛን ግንኙነት በተመለከተም የተሻሻለ ሕግ አውጥቷል። በተጨማሪም የልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ምንም አጭር ቢሆንም ሠላም የሰፈነበትና የጥጋብ ጊዜ ስለነበረ ሕዝቡ የሚከተለውን ገጠመ።



አቤቶ ኢያሱ ከአብደላ አሊ ሳዲቅ ቤተሰብ ጋር በሐረር

"አባ ጤና ኢያሱ
ዳቦ ነው ትራሱ"
"ኢያሱ አባ ጤና ዘለቀ ወይ በእርግጥ
እሱ አያስደነግጥ በቅሎው ወበር አትረግጥ"

አቤቶ ኢያሱ በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት ሦስት ዓመት በመማሩ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ከውጭ አገር ሰዎች ጋር መግባባትም ችሎ ነበር። በተጨማሪም ትልቅ ራዕይ የነበረውና አያቱ የጀመሩትን



የአወሮፓ ሥልጣኔ ለማጣደፍና ኢትዮጵያን ኃያል አገር ለማድረግ መታገል ጀምሮ ነበር። ስለኾነም በወቅቱ የነበሩ ወጣት ምሁሮችን ድጋፍ አገኘ።

ልጅ ኢያሱ የመጀመሪያው ዓለም ጦርነት ባስጋበት ጊዜ አጋርነቱ ከቱርክና ከጀርመን ጋር መሆኑን ከማሳየቱም በላይ ከጀርመናዊቷ አስትርያ መሣሪያ ለመግዛት ተዋዋለ። እንዲያውም ጀርመንን ለማገዝ ታንጋኒካ (አሁን ታንዛኒያ) ወታደር ልኳል። እነዚሁ ወታደሮች እሩቅ እጠገብ ስለቀሩ ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በጋብቻ ተሳስረው በአሁኑ ወቅት የልጅ ልጆቻቸው ወደ ሰባት መቶ ቤተሰብ ያህል እዚያው ገበሬ ሆነው ቀርተዋል። ታንዛኒያ ነፃ ከወጣች ጊዜ አንስቶ የነዚህ ሰዎች ዜግነት ጉዳይ እያነጋገረ ይገኛል።

አቤቶ ኢያሱ ባይሳካለትም ሁሉን የኢትዮጵያ ጎሣ በማስተባበር ኤርትራን፣ ጅቡቲን፣ የበርበራንና የሞቃድሾን ሶማሌ የማስመለስ ዕቅድ ነበረው። ከዚህም የተነሳ አቤቶ ኢያሱ 380 ሺህ ጦር ለማሰናዳት ለየደጃዝማቾቹ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የጦር ሠራዊት ብዛት በመንገር የራሱንም ወስኖ "ፈረሴ ቀይ ባሕር ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም" እያለ ያስፎክር ነበር።

ቱርክ የስዊዝ ካናልን ለመቆጣጠር ፈልጋ ቀደም ብላ በሜዲትራንያን በኩል ሞክራ ስላቃታት የጥቃቷን አካሄድ ለወጠች። የሶማሌን፣ የኢትዮጵያንና የሱዳን መንግሥቶች ከግብጽ ጋር በማስተባበር ከቱርክ ጋር እንግሊዝንና ፈረንሳይን ከስዊዝ ካናል ለማባረር በቀይ ባሕር በኩል ጦርነት እንዲከፍቱ ትገፋፋ ነበር። አቤቶ ኢያሱም በበኩሉ የሶማሌ ግዛቶችን ለመጠቅለል ይፈልግ ነበርና ለአራት ቀን ጅቡቲን ጎብኝቶ ዘንጉን ወደቡ ላይ ተክሎ "እስከ እዚህ ድረስ ግዛቴ ነው!" ብሎ ተመለሰ። ለቱርክ አምባሳደር አንድ፣ ለሶማሊ ባላባቶችም አሥራ ሁለት የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ላይ "ላ ሂላ ሐ ኢለላ" ብሎ ጽፎ ቢልክላቸው ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን በእኩልነት የሚያስተዳድር ንጉሥ መጣልን ብለው ደስ ስላላቸው ለአቤቶ ኢያሱ ገቡለት።

እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ይህንን ሁኔታ ሲረዱ የአቤቶ ኢያሱ ከጀርመኑ ንጉሥ ዳግማዊ ዊሊያምና ከቱርክ መሪ ሡልጣን ሞሐመድ 6ኛ ጋር መወዳጀቱ አስግቷቸው በየቆንሲሎቻቸው በኩል

የተቻላቸውን ደባ በመሥራት አቤቶ ኢያሱን ከሥልጣን ለማውረድ አሜሩ። ሐረር የነበረው የእንግሊዝ ቆንሲል ዕረፍት ሄደ ተባለና በምትኩ ሻለቃ ቲ. ኢ. ሎዌረንስ ኦፍ አረብያ በመባል የሚታወቀው፣ አረቦችን ቀስቅሶ በቱርኮች ላይ በማስነሳት ቱርኮች ይዞታቸውን እንዲለቁ ያስደረገ የእንግሊዝ ሰላይ የጦር መኮንን በስውር ሐረር ተልኮ የተቻለውን ደባ ሠርቶ ተመለሰ።



ንጉሥ ሚካኤልና አቤቶ ኢያሱ (የአፄ ምኒልክን ዘውድ ይመልከቱ)



ደባውም አቤቶ ኢያሱን ከሥልጣን ማውረድና በምትኩ ዝምተኛውንና የአወሮፓ ቋንቋ ችሎታ ያለውን የንጉሥ ሚካኤል ልጅ ... ሥላሴን ተወላጅ ደጃች ተፈሪ መኮንንን ለማሾም ነበር። አቤቶ ኢያሱን ለማስወገድ የከበቡትን መኳንንቶች ድክመትና ብርታት፣ የአካባቢ ሁኔታን በሚሰዮን ሰዎችና አገር ውስጥ በሚኖሩ ፈረንጆች እስጠኑና የሚከተለውን ሤራ ጀመሩ።

1) ለየመኳንንቱ ልጅ ኢያሱ መስለሙን ማስተጋባት

2) ሙሴ ሊዮን የሚባል አርመናዊ ፎቶግራፍ አንሺ የአቤቶ ኢያሱን መልክ በፎቶግራፍ ጥበብ የእስላም ልብስ የለበሱ አስመስሎ ሃያ ሺ ኮፒ ከግብጽ አገር አሳትሞ በማስመጣት በአድዋው ተወላጅ በባይከዳኝ ገብረ ሕይወት በኩል እንዲበተን ተደረገ።



ቲ. ኢ. ሎዎሬንስ

ልጅ ኢያሱን በሃይማኖት መለወጥ ወንጀሎ ማስረጃ እንዲሆኑ ብዙ ፎቶግራፎች በሞንታዥና በኮላዥ እየገጣጠሙ መበተንና ወሬ በማናፈስ ሕዝቡን እንዲያምጽበት ማድረግ ተቀዳሚ ተግባራቸው ኾነ። ተባባሪዎቻቸውም በአማርኛና በፈረንሳይኛ ጽሑፎች በድሬዳዋ ማተሚያ ቤት አሳትመው በማሰራጨት፣ በግልበጣው መካከል በገጠማቸው እንቅፋት ምክንያት እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ጽሑፎችንም በመበተን፣ መልሰም ሰብስቦ በማቃጠል የተተረማመሰ ብዙ ሁኔታ ታይቷል። የተገጣጠሙና የተበተኑትም ፎቶግራፎች የንጉሥ ሚካኤልንም ምስል ይጨምራሉ።

የልጅ ኢያሱ ትልቁ ጥፋት የአያቱ የአፄ ምኒልክን መኳንንቶች በከበሬታ አለመያዙና ለሕግ ተገዥ አለመሆኑ ነው። ሁለተኛ ደግሞ መካር ያልነበረውና እሱም ምክር የማይሰማ አፍላ ጎረምሳ ነበር። ነገረ ሠሪ ወይም ፈርማቶሪ ወይም ሰላይ አይወድም ነበርና ወሬ ሊያገኝ አልቻለም። በወቅቱ ከፖለቲካው እምብርት አዲስ አበባ ርቆ ለበጠኝ ወር ሐረር መቀመጡም የመኳንንቶቹን አዝማሚያ የማያወቅ እንደነበር ያስረዳል። በተጨማሪም በሸዋ መኳንንት ዘንድ ተአማኒነት ያሳጣው የቤተ መንግሥቱን የወግ ዕቃዎች የአፄ ምኒልክንም ዘውድ

ጨምሮ ወደ ደሴ መወሰዱና ዋና ከተማውንም ወደ እዚያው ለማዛወር ማሰቡ ስለተወራ ነው።

መኳንንቶቹም በልጅ ኢያሱ ተግባር ደስተኛ ስላልነበሩ አድመው መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም እንዲሻር አደረጉ። በምትኩም የአፄ ምኒልክ ሴት ልጅ ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥት ተብለው ሲነግሡ ደጃች ተፈሪ መኮንን ራስ ተብለው አልጋ ወራሽ እንዲሆኑ ተወሰነ። የዚህ አድማ ጠንሳሾች ቤተ መንግሥት አካባቢ ያሉ መኳንንቶች ናቸው። በኋላ ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ተወሰነ ተብሎ ተገለጸ።



በሐረር ልጅ ኢያሱ ባለበት ስብሰባ ቲ. ኢ. ሎውሬንስ እንደተገኘ

“በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም” እንደሚባለው ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ለማጥላላት የተለያዩ ፎቶግራፎች በመገጣጠም እየበተነ ሰው ሲራብ እሳቸው ውሻ ሲመግቡ፣ ሌላም ፎቶግራፍ እየቀጣጠለ በትኗል።

ልጅ ኢያሱን የሚወዱ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም የመኳንንቱን ውሳኔ ለመቃወም አመች አልነበረም። አንድ ወታደር አቤቶ ኢያሱን ለማገዝ ወደ ሐረር ከመሄዱ በፊት እንደሚከተለው ሸለለ ይባላል።

“አባ ጤና ኢያሱ ጥይት ግዛ! ጥይት ግዛ! ወገብክን ይጭኑቀው!
እኛ ሰማን ወሬ አንተ የማታውቀው!”





ንጉሥ ሚካኤል (በሥዕል የተዘጋጀ ምስል)

የአቤቶ ኢያሱ መሻር ሐረር ላይ እንደተሰማ ከተማው ተረብሾ ወደ 500 ያህል ሰው ሞተ። አቤቶ ኢያሱም መሻሩን እንደሰማና የተሰጠውንም ምክንያት እንደተረዳ መኳንንቶቹንና ካህናቱን ቤተ መንግሥት ሰብስቦ መጽሐፈ ቄደር ተጠምቆ ስለመ የተባለውን አስተባበለ። ሐረር የነበሩትንም የካቶሊክ ጳጳስ ጠርቶ ሁኔታውን እንዲገነዘቡና ምስክር እንዲሆኑት አደረገ። አቤቶ ኢያሱ ወደ አባቱም ወደ ንጉሥ ሚካኤል መልዕክት ላከ። ጦርም አዘጋጅቶ ወደ ሸዋ ሊዘምት ሲል ከሸዋ የተላከ ጦር ሚኤሶ (ሐረርጌ) ላይ ገጥሞት ተሸነፈ። የአባቱም ጦር ወደ ሸዋ ገብቶ ሰገሌ ሜዳ ላይ ተሸንፎ ንጉሥ ሚካኤልም ተማረኩ። የዚህን ጊዜ ልጅ ኢያሱ በአዳል በረሃ አቋርጦ ወደ መቅደላ ሄደና ጦር ሰብስቦ ውጊያ ቢጀምር አልቀናውም። ከዚህ በኋላ በአውሳ በርሃ አድርጎ ቢጋብቻ የሚዛመዱት ራስ ሥዩም ዘንድ ምዕራብ ትግራይ ግዛት ሄደ። ዕርዳታ የማያገኝ መሆኑን ሲረዳ ወደ ምሥራቅ ትግራይ ዘልቆ ራስ ጉግሣ አርአያ ዘንድ ሄደ። የእስላም ባላባቶች ወደ ቆላ ግባና እኛ ዘንድ እንደብቅሃለን፣ ሚስትም እንድርሃለን በሠላምም ትኖራለህ ወይም ወደ ኤርትራ ይዘንህ እንጥፋ፣ ቢሉት ከአገሬ አልወጣም ሚስትም አለችኝ፣ መስለምም አልፈልግም ብሎ ቅብጽያ ገዳም ገብቶ ተደበቀ። እዚያም እንዳለ ራስ ጉግሣ ስለፈሩ ያዙትና ደሴ ወስደው ለራስ ተፈሪ አስረከቡት። መጨረሻ ላይ ወደ ሸዋ ተይዞ መጣና ሰላሌ በራስ ካሣ ኃይሉ ሥር ግዞት ወረደ። ይህ ሁሉ ግብግብ በጠቅላላው አራት ዓመት ፈጀ።

በራስ ካሣ ጠባቂነት በግዞት ሰላሌ እያለ ልጃቸውን ባገባው በራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት አቀነባባሪነት ከአሥመራ አይሮፕላን መጥቶ አራት ቀን ጠብቆት ተሰፋ ቆርጦ ከተመለሰ በኋላ ልጅ ኢያሱ ከእስር ቤት አምልጦ የሚቀበለው ሲያጣ ወደ ጐጃም ሲሄድ ተያዘ። ከዚህ በኋላ በግዞት ወደ ሐረር ተወስዶ በጋራ ሙለታ አውራጃ በግራዋ ከተማ እስር አምባ ሲኖር በ1928 ዓ.ም ተገደለ ተብሎ በሰፊው ተወራ።

— ፪ —

በ፲፱፻፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መስከረም ፡ በ፲፯ ቀን ።

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የጃንሆይን ፡ የአፄ ፡ ምኒልክን ። ትእዛዝ ፡ ስላፈረሱ ። ያባታችንን ፡ ያቡነ ፡ ማቴዎስን ፡ የእጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስንም ፡ የመሐላና ፡ የግዝት ፡ ቃል ፡ ስለጣሱ ። መኳንንቱም ። ሠራዊቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበ ። ላባታችን ፡ ላቡነ ፡ ማቴዎስና ፡ ለእጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ። ያስታወቁበት ፡ የጩኸት ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

ጃንሆይ ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ለሃይማኖትዎና ፡ ለመንግሥትዎ ፡ እጅግ ፡ ተጨናቂ ፡ ነበሩና ። ቀድሞ ፡ እንዳለፉት ፡ ንግሥታት ፡ ጊዜ ፡ ሠራዊታቸው ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ እንዳይተላለቅባቸው ፡ በመንግሥትዎም ፡ ንፋስ ፡ እንዳይገባበት ፡ አስበው ። ፈጽመው ፡ እቤት ፡ ሳይውሉ ፡ በ፲፱፻፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ። ሊቀ ፡ ጳጳሱና ፡ እጨጌ ፡ ቆማችሁ ። መኳንንቱንና ፡ ሕዝቡን ፡ ሰብስባችሁ ። ልጁን ፡ ኢያሱን ፡ ስጥቻችኋለሁና ፡ ከሱ ፡ ፈቃድ ፡ የወጣ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፡ ጥቁር ፡ ውሻ ፡ ይውለድ ። እሱም ፡ እናንተን ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የበደለ ፡ እንደሆነ ፡ ርጉም ፡ ይሁን ፡ ጥቁር ፡ ውሻ ፡ ይውለድ ፡ ብለው ፡ ሰጡን ። አባታችንም ፡ እጨጌም ፡ በዚሁ ፡ ቃል ፡ አውግዛችሁ ፡ ሰጣሁን ። እኛም ፡ ደስ ፡ ብሎን ፡ ተቀበል ። የግዝትም ፡ ቃል ፡ እንዳይናወጥብን ፡ ተጠንቅቀን ፡ ባለንበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በትሕትና ፡ ራሳችንን ፡ ደፍተን ፡ በተቻለን ፡ በሙሉ ፡ ልባችን ፡ መንግሥታችንን ፡ እየረዳን ፡ እስካሁን ፬ ቆየን ፡ ከግዝቱም ፡ ቃል ፡ የወጣ ፡ ሥራ ፡ እንዳልሰራን ፡ አባታችንም ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያውቃል ።

የምንናስታውቀውም ፡ ቃል ፡ ይኸ ፡ ነው ።

፩ኛ ፡

መገርመሬ ፡ ጃንሆይ ፡ ማረፋቸውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያወቀው ፡ ባረፉበት ፡ ሰሞን ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ትሕዛዝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈረሱን ፡ እየጫነ ፡ ጉግሥ ፡ ሲጫወት ፡ ሰነበተ ። የቀረው ፡ ቢቀር ፡ በዚያው ፡ ሰሞን ፡ ማዘንና ፡ መተከዝ ፡ ይገባ ፡ ነበር ። መኳንንቱና ፡ ሕዝቡም ፡ ለጌታው ፡ ሳያለቅስ ፡ እንባው ፡ እንዳረገዘ ፡ ቀረ ። ምኒልክን ፡ የመሰለ ፡ የድኃ ፡ አበት ፡ እናት ፡ የነጋሲው ፡ ንጉሣችን ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ አድርገ



— ፫ —

ው ፡ አስማምተው ፡ አሕዛብ ፡ አቅንተው ፡ በጸኑት ፡ መንግሥት ፡ በሰናትም ፡ ዐብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጧፍ ፡ ዕጣን ፡ ሳይበልላቸው ፡ ቀረ ። አጽማቸውም ፡ የወደቀበትን ፡ ቦታ ፡ አባታችንም ፡ ያውቁታል ። በጃንሆይ ፡ ማረፍ ፡ ሕዝቡ ፡ በግልጽ ፡ እንዳያለቅስ ፡ ማድረጋቸውና ፡ አለማስፈታታቸው ፡ መንግሥት ፡ እንዳይንቃነቅባቸው ፡ ይሆናል ። ተነገ ፡ ዛሬ ፡ ፍታት ፡ አስፈቱ ፡ ምጽዋት ፡ አድርጉ ፡ ይሉናል ፡ እያልን ፡ ስንጠብቅ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቀን ፡ ቆየን ። ያባታቸውንም ፡ ማረፍ ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጥሩት ፡ የቀሩት ፡ ለካ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ከለወጡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ኖሯል ።

፪ተኛ ።

ሃይማኖት ፡ መለወጣቸውንና ፡ ከክርስቲያን ፡ መንገድ ፡ መውጣታቸውን ፡ መግለጽ ፡ ከወጡት ፡ ዝምር ፡ የሠሩትን ፡ ያልተገባ ፡ ሥራ ። ሁሉን ። ጽፈን ፡ ለመጨረስ ፡ አይቻልምና ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ብቻ ፡ በጭር ፡ ቃል ፡ እናመለክት ።

ጌታችን ፡ ጃንሆይ ፡ የሮፓን ፡ ሥርዓት ፡ አኔው ፡ ተሽቀዳድሜ ፡ በገሬ ፡ ታላገባሁና ፡ በሁሊም ፡ ነገር ፡ እነርሱን ፡ ካልመሰልኋቸው ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ከተማ ፡ መጠበቁና ፡ የሮፓን ፡ ሥርዓት ፡ ማስለመጃ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ የሌሊት ፡ ዘበኛ ፡ ቢያቆሙ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ አሥር ፡ አሥር ፡ አሽከር ፡ እያስከተሉ ፡ ሌሊት ፡ እየዞሩ ፡ እንደ ፡ ሽፍታ ፡ ከዘበኞቹ ፡ ጋራ ፡ እየተታኰሡ ፡ ጠንክረው ፡ የሚጠብቁትን ፡ ዘበኞች ፡ እየገደሉ ፡ በከንቱ ፡ ደማቸውን ፡ እያፈሰሱ ፡ የቆመውን ፡ ደምብ ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ስላልረበ ፡ ነገር አፈረሡት ።

፫ተኛ ።

የእስላም ፡ ቃልቻች ፡ እየሰበሰቡ ፡ የመሐመድንና ፡ የግራኝን ፡ ታሪክ ፡ እያስነበቡ ፡ ያያቶቻቸውን ፡ ዘር ፡ እያስቈጠሩ ፡ የይማሞች ፡ ዘር ፡ ከመሐመድ ፡ ዘር ፡ የወረደ ፡ ነው ፡ አሰኝተው ፡ እስላምነታቸውን ፡ ካደላደሉ ፡ በኋላ ፡ የእስላም ፡ ሴት ፡ እየፈለጉ ። ያባ ፡ ጅፋርን ፡ ልጅ ። የእሕቱን ፡ ልጅ ። የእሚር ፡ ብዱላሂን ፡ ልጅ ። የነጋድራስ ፡ መሐመድን ፡ ልጅ ። ያዳልንም ፡ የባላባት ፡ ልጅ ። እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ አግብተው ፡ ቴበቱ ። የቀሩትማ ፡ የእስላም ፡ ሴቶች ፡ ስንቱ ፡ ተጽፊው ፡ ያልቃሉ ። ስንኳስ ፡ ያልተጠመቀችዋንና ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ብትሆን ፡ በመጽሐፋችን ፡ የታዘዘ ፡ አለ ።

— ፬ —

፩ተኛ ።

አባታችንም ፡ እጨጌም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ እያወቁና ፡ እየሰሙ ፡ መክረው ፡ ለመመለስ ፡ ተሸነፉ ። አባታቸው ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ልጃቸውን ፡ መክረው ፡ ከዚህ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ ይመልሱልናል ፡ ብለን ፡ ተስፋ ፡ ስናደርግ ፡ አሸንፈዋቸው ፡ ኖር ፡ እምና ፡ በፍልሰታ ፡ የእስላም ፡ ጾም ፡ ገዋም ፡ ነበርና ፡ አባታቸው ፡ ከተማ ፡ ደሴ ፡ ላይ ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ የክህደት ፡ ሥራ ፡ በጅሌና ፡ በጡሙጋ ። በዉና ። በጀላሌ ፡ ሲያደርጉት ፡ የከረሙ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ቢጽፉትም ፡ እያልቅ ፡ ለመስማትም ፡ ደስ ፡ እያሰኝ ። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ሲሰሩ ፡ መኳንንቱም ፡ ሠራዊቱም ፡ ዕያየ ፡ ዕየሰማ ፡ ሕጻን ፡ ቢሆኑ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ትዕግሥት ፡ ቢያበዛ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዘውዳቸውን ፡ ጭነው ፡ በክርስትና ፡ ጸንተው ፡ መንግሥታቸውን ፡ ጠብቀው ፡ መያዝና ፡ ማኖናት ፡ ጠልተው ፡ ዕድሜአቸው ፡ ለአውቀት ፡ ሲደርስ ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላቸው ፡ የቃልቻ ፡ ቃል ፡ እየሰሙ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ አልቋአል ። በመሐመድና ፡ ከግራኝ ፡ ዘር ፡ የወረዱት ፡ የይመጣሞች ፡ መንግሥት ፡ መነሻው ፡ ደርሷል ፡ እያሉ ፡ እምና ፡ ሐረርጌ ፡ የወረዱ ፡ ጊዜ ፡ እራቁ ፡ አደብራት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እጅ ፡ ሳይነሡ ፡ ቀሩ ። ከዚያም ፡ ሁሉ ፡ ዐብያት ፡ ክርስቲያናት ፡ ላንዱ ፡ እንኳ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይሰጡ ፡ የመላው ፡ ሐረርጌ ፡ እስላም ፡ እየተሰበሰበ ፡ የሚሠግድበት ፡ መሥጊድ ፡ ሒደው ፡ አብረው ፡ ሠገዱ ። ባምስቱም ፡ በር ፡ ዙሪ ፡ ላሉት ፡ መሥጊዶችና ፡ ቃልቾች ፡ አትርሱኝ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡ ።

፪ተኛ ።

ጃንሆይ ፡ ሐረርጌን ፡ የሰበሩ ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቲያን ፡ ፊዋጋ ፡ ያለቀውን ፡ እስላም ፡ ዐታውንና ፡ ቤቱን ፡ ሁሉ ፡ ጃንሆይ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለመንግሥት ፡ እርስት ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ለክህነትና ፡ ለከተማው ፡ ዘበኛ ፡ ከከተማ ፡ ለማይለይ ፡ ሰራተኛ ፡ ሰጥተውት ፡ የፈረሰውን ፡ መልሶ ፡ እየሠራ ፡ የዘባውን ፡ እያቀና ፡ ይህነን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ይዞት ፡ የኖረውን ፡ ቤት ፡ ለእስላሙ ፡ ልቀቁ ፡ ብለው ፡ አስለቀቁት ፡ ከህናቱም ፡ ከታቦቱ ፡ ተለይቶ ፡ ወጣ ፡ ድኅውም ፡ አልቅሶ ፡ ለቀቀ ።

፫ተኛ ።

ያሩሲ ፡ ጋላ ፡ ሸፍቶ ፡ ፊታውራሪ ፡ አባተ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ቢትወደድ ፡ ኃይሉ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሸፍታውን ፡ ለማርጋት ፡



— ፬ —

ጦር ፡ ቢልኩ ፡ ያኸውም ፡ ከጥፋት ፡ ተቋጥሮባቸው ፡ ተነቀቀበት ፡ ያኸም ፡ እስላም ፡ እንዳይነካ ፡ ለማድላት ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ የመሰለ ፡ በደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ ግዛት ፡ በውጋዴን ፡ አርብ ፡ እምሥቱን ፡ ወታደር ፡ ሱማሌ ፡ አርዶት ፡ ሥራት ፡ ሳይታይ ፡ ያልቁንም ፡ ሱማሌዎቹ ፡ እዲስ ፡ አበባ ፡ ቢመጡ ፡ ተሸልመው ፡ ሔዱ ፡ የክርስቲያኑም ፡ ደም ፡ እንደውሻ ፡ ደም ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ። ይህም ፡ ነገር ፡ እስላም ፡ በክርስቲያኑ ፡ መቀበቱ ፡ ነው ።

፬ተኛ ።

እንዲሁ ፡ ከተማ ፡ ድሬ ፡ ደዋ ፡ ላይ ፡ ቀድሞ ፡ ያልነበረውን ፡ መስጊድ ፡ ተሰርቶ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ ከወረዱ ፡ የእስላም ፡ አሊሞች ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ የእስላም ፡ ጥምጥም ፡ ጠምጥመው ፡ ገልድም ፡ እገልደመው ፡ ፈጽመው ፡ የክህደት ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ እመሥጊዱም ፡ ገብተው ፡ አብረው ፡ ሠገዱ ። ለመስጊዱም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡ ። የኛ ፡ ታቦት ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ተቋርቍሮ ፡ በመቃኛ ፡ የኖረውን ፡ ከህናቱም ፡ መኳንንቱም ፡ ቢያስታውቁ ፡ እስከሁን ፡ ሳይሰራ ፡ ቀርቶ ፡ የመሥጊዱ ፡ ሥራ ፡ በልጦ ፡ ቀደመው ፡

፭ተኛ ።

ጅጅጋ ፡ ላይ ፡ ዳርቻ ፡ አገር ፡ ነው ፡ በዚያ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀመጥ ፡ ክርስቲያን ፡ መቅደስ ፡ ካልተተከለለት ፡ ሰውነቱ ፡ ያማግጣል ፡ ብለን ፡ የተከልነውን ፡ ታቦት ፡ ይህ ፡ ለመሥጊድ ፡ የሚሆን ፡ ቦታ ፡ ነውና ፡ ታቦቱ ፡ ከሌላ ፡ ቦታ ፡ ሔዶ ፡ ይደረብ ፡ ብለው ፡ ከህናቱም ፡ ታቦቱን ፡ ይዘው ፡ ጊራ ፡ ከሚባል ፡ ቦታ ፡ ተዳብለው ፡ ተቀምጠዋል ። ይህስ ፡ የእስላም ፡ ወገን ፡ እጅ ፡ ነኝ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። አሁን ፡ መጠቅለያውን ፡ የሐረርጌ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ቀድሞ ፡ መስጊድ ፡ ነበርና ፡ ታቦቱ ፡ ይውጣና ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ መሥጊድ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ነበር ። በቅርብ ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ የሚነሣባቸው ፡ ቢሆን ፡ ለጊዜው ፡ ትተውታል ። ለኋላው ፡ ግን ፡ አሳባቸውን ፡ ሳይፈጽሙት ፡ አይቀሩም ።

፮ተኛ ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የሚከፋ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ እስከሁን ፡ ከእስላም ፡ ጋራ ፡ እየተጋደለ ፡ በክርስትና ፡ ጸንቶ ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ታውቆ ፡ እራሱን ፡ ችሎ ፡ የኖረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡

— ፱ —

የክርስቲያን፡ መንግሥት፡ ስሙን፡ ከምድር፡ አጥፍተው፡ ሃይማኖቱን ፡ አስለውጠው ፡ የእስላም ፡ ዜጋ ፡ ሊያደርጉ ፡ የመንግሥታችንና ፡ ያገራችንን፡ ክብርና ፡ ስም ፡ መጠሪ ፡ በሰንደቅ ፡ አላማችን ፡ ላኢላ ፡ ሐኢላላ ፡ መሐመድ ፡ ረሱል ፡ አላህ ። ብለው ፡ አስጽፈው ፡ ወስደው ፡ ለቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ቆንሲል ፡ አስረከቡት ። ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ማለት ፡ ትርጓሜው ፡ በመንግሥት ፡ ፋንታ ፡ ሆኖ ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ የሚታይና ፡ የሚታወቅ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ። ለዚሁ ፡ ምስክር ፡ መንግሥት ፡ ሲባል ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ የሌለው ፡ መንግሥት ፡ የለም ። የቱርክ ፡ መንግሥትም ፡ ቆንሲል ፡ ይህንን ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ተቀብሎ ፡ በዙ ፡ ደስታ ፡ አድርጎ ፡ ሽምጋኝ ፡ ከፍቶ ፡ እያጠጣ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ከዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖት ፡ የተመረጠ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶት ፡ ዛሬ ፡ አመነ ። ለዚሁም ፡ ምስክር ፡ ሰንደቅ ፡ አላማውን ፡ ለእስላሞች ፡ ጠቅላይ ፡ ለቱርክ ፡ መንግሥት ፡ አስረከበ ። እንግዴህ ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ የቱርክንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ ወንጀል ፡ ይሆንበታል ። እያለ ፡ በጉባዔ ፡ መረቀ ። የውጪ ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴዎች ፡ ይህንን ፡ ሰምተው ፡ ሰንደቅ ፡ አላማችሁን ፡ አስመልሱ ፡ እያሉ ፡ ቢመክሩ ፡ የሚሰማቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማው ፡ አሁንም ፡ በቱርክ ፡ ቆንሲል ፡ እጅ ፡ እንዳለ ፡ ነው ።

፲ረኛ ።

በፍጹም ፡ መስለማቸውን ፡ ለይቶ ፡ የሚያስታውቅ ፡ እስከ ፡ አርበ ፡ ትውልዳቸው ፡ በጠርቡሽ ፡ ላይ ፡ አጽፈው ፡ ወገናችሁ ፡ ነኝና ፡ እስላምነቴን ፡ እወቁ ፡ ብለው ፡ ለሐረርና ፡ እስላም ፡ ሱማሌ ፡ ሽለማት ፡ ሰጡ ። ድብቅ ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ ያየው ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህስ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መክድ ፡ አይዶለምን ።

፲፩ደኛ ።

ሐረርጌ ፡ የእስላሙን ፡ ቃዲ ፡ ጠላና ፡ ጠጅ ፡ ትጠጣለህ ፡ እሉ ፡ ስለምን ፡ የስላም ፡ መጽሐፍ ፡ የማያዘውን ፡ ትሠራለህ ፡ ብለው ፡ ከሳሽ ፡ ሳይነሣበት ፡ በደበበይ ፡ ፍረዱ ፡ ብለው ፡ ክርስቲያኑንም ፡ እስላሙንም ፡ አስፈርደው ፡ አሰሩት ። እስላሙስ ፡ ይፍርድ ፡ ክርስቲያኑን ፡ በማያውቀው ፡ ሕግ ፡ ቀላቅለው ፡ በፍርሐት ፡ ማስፈረዳቸው ፡ የምን ፡ ማድረግ ፡ ይመስላል ።



— ፲ —

፲፪ተኛ ።

አሁን ፡ ጅጅጋ ፡ ከወረዱ ፡ የሱማሌን ፡ ውጋዝና ፡ ባላገር ፡ ሰብስበው ፡ ሙሉ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ ሸልመው ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ባለ ፡ ግርማ ፡ ሰንደቅ፡ ዓላማችንን ፡ እዚህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ቆንሲል ፡ የተሰጠው ፡ አንሶ ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ላኢላ ፡ ሐኢላላ ፡ መሐመድ ፡ ረሱል ፡ አላህ ። የሚል ፡ ተጽፎበት ፡ ምስሌ ፡ የሚሆን ፡ ክር ፡ እሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ይህንኑ ፡ ክር ፡ የሚበጥስ ፡ ፋስ ፡ የያዘ ፡ ጠርቡሽ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ሥዕል ፡ ተሥሎበት ። ለሱማሊዎች ፡ ሰጥተዋቸው ፡ በደበበይ ፡ ይዘውት ፡ መጥተው ፡ ፈከሩበት ። ይህስ ፡ በክርስቲያኑ ፡ በኢትዮጵያው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ መነሣት ፡ አይዶለምን ።

፲፫ተኛ ።

የኢትዮጵያን ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ መሔዱን ፡ ዕያየና ፡ እያወቀ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ትእግሥት ፡ ቢያበዛ ። ፈረንጆች ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ተመልተው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ጃሂድ ፡ የማጠስጉና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርስቲያን ፡ አጥፍቶ ፡ በመጨረሻው ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የሚከፋ ፡ ነገር ፡ ለማምጣት ፡ ነውና ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለመንግሥት ፡ እናመልከትና ፡ ለራሱ ፡ ብላሃት ፡ ቢያበጅ ፡ ያብጅ ፡ በተቀረ ፡ እኛ ፡ የምንሠራውን ፡ ሥራ ፡ እናውቃለን ፡ ብለው ፡ በንደንት ፡ ሆነው ፡ በግልጽ ፡ አስታወቁ ። ይህንን ፡ ነገር ፡ አስቀድመው ፡ ለመንግሥት ፡ ማመልከታቸው ፡ ብናውቅበት ፡ ለኛ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ክፋት ፡ አስበው ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ፡ ልጅ ፡ ኢያሱም ፡ አሳባቸውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ባገራችን ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ ለመነሣት ፡ ይመቻቸው ፡ ነበር ። ጃንሆይ ፡ የመሠረቱትን ፡ ውል ፡ ጠብቀን ፡ ተጠንቅቀን ፡ ከኛ ፡ ርን ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚነካት ፡ ሰው ፡ የለም ። ባንድ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ውል ፡ ማፍረስ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ሳይጠሉ ። እንዴት ፡ ለምስም ፡ አገራችንን ፡ እናስወስዳለን ። ሃይማኖትስ ፡ ሲፈርስ ፡ ምን ፡ እናስተውላለን ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ጃሂድ ፡ እያሉ ፡ የጃንሆይን ፡ አሽከሮችና ፡ የክርስቲያን ፡ ደም ፡ ያፈሰሱትን ፡ እስላሞች ፡ ሼኽ ፡ ጦለሃን ። ያሰን ፡ እንጃዋ፡ን ፡ ልጅ ፡ ያብ ፡ ጅፋርን ፡ ልጅ ። ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ ብዙዎች ፡ እንደነዚሁ ፡ ያሉትን ፡ ይዘው ፡ እጥናው ፡ እስላም ፡ አገር ፡ ጅጅጋ ፡ ተቀምጠው ፡ ውጋዴን ፡ ውስጥ ፡ ሽፍታ ፡ ሆኖ ፡ እያስቸገረ ፡ ከሚኖረው ፡ ጅጅጋም ፡ ድረስ ፡

— ፲፮ —

መጥቶ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊፈጅ ፡ ከነበረው ፡ ከከቢራው ፡ ጋራ ፡ እየተላላኩ ፡ ብዙ ፡ ጠበንጃና ፡ ጥይት ፡ መትረየስም ፡ ሰደዱለት ። ዶግሞ ፡ የእንግሊዝንና ፡ የኢጣልያንን ፡ ዜጎች ፡ በየወሩ ፡ እየሰበሰቡ ፡ ጂሃድ ፡ እንበል ፡ እያሉ ፡ መከረዋል ።

ዛሬ ፡ ጅጅጋ ፡ ወርደው ፡ መምከራቸው ፡ የእስላም ፡ መከከለኛ ፡ አገር ፡ ነውና ፡ ጂሃድ ፡ በሚሉበት ፡ ጊዜ ፡ ኀይላቸው ፡ እንዲበረታላቸው ፡ ነው ።

እሳቸው ፡ ግን ፡ እስላም ፡ ያረደውን ፡ እየበሉ ፡ አገር ፡ ለማስፋትና ፡ ሰው ፡ ለማባበል ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ የሚያታልሉት ፡ ይህ ፡ ሱማሌና ፡ እስላም ፡ ከዚህም ፡ በፊት ፡ በጃንሆይ ፡ የገበረ ፡ የቀቀለ ፡ ዜጋቸው ፡ ነው ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ግን ፡ ከእስላሙ ፡ ጋራ ፡ ኡብረው ፡ በመብላታቸው ፡ የራሳቸውን ፡ እስላምነት ፡ ለማጽናት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በማባበሉስ ፡ ፊት ፡ ከቀናው ፡ አገር ፡ በተቀረ ፡ ስንዝር ፡ መሬት ፡ የጨመሩት ፡ ነገር ፡ የለም ። አሁንም ፡ ጃንሆይ ፡ ያሸከሮቻቸውን ፡ ደም ፡ አፍስሰው ፡ ያቀኑት ፡ አገር ፡ የስላም ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ሊሰቀልበት ፡ ክርስቲያንም ፡ የሰሩት ፡ ሠብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የእስላም ፡ መስገጃ ፡ ሊሆኑ ፡ ነውና ፡ ሃይማኖት ፡ መፍረሱን ፡ መንግሥት ፡ መጥፋቱን ፡ እስበን ፡ እንቻልህ ፡ እንታገሥህም ፡ ብንለው ፡ የማይቻለን ፡ ሆን ፡ ስለዚህ ፡ ከርቻ ፡ በፊት ፡ በወንጌል ፡ ተሰብክ ፡ ህክርስትና ፡ ጸንቶ ፡ እስከሁን ፡ የኖረውን ፡ መንግሥት ። አሁን ፡ የእስላሞች ፡ ዋና ፡ ገጋር ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ሊወድቅ ፡ በደረሰበት ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ እስላምነት ፡ ሲመለስና ፡ የክርስቲያን ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ የፈሰሰበት ፡ አገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእስላም ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ሲሰቀልበት ፡ ከማየት ፡ አስቀድሞ ፡ የሃይማኖት ፡ አምላክ ፡ ይርዳን ፡ ብለን ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ደማችንን ፡ ለማፍሰስ ፡ ቈርጠናል ። እንግዴህ ፡ መንግሥት ፡ ያለ ፡ ሃይማኖት ። ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ መንግሥት ፡ እንዳይጠና ፡ የታወቀ ፡ ነውና ፡ ለዚሁም ፡ መንግሥትና ፡ ሃይማኖት ፡ ጃንሆይ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ከዋሉ ፡ ዠምረው ፡ እስከሁንም ፡ የደከሙበት ፡ አባታችን ፡ ነዎ ። ሃይማኖቱ ፡ ይጥና ፡ መንግሥታችን ፡ ይርጋ ፡ ያሉ ፡ እንደሆን ፡ የማርቆስ ፡ ሃይማኖት ፡ አምላክ ፡ ለዳዊት ፡ እርዳታ ፡ ያወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይለያችሁ ፡ ብለው ። አባታችን ፡ መስቀልዎን ፡ አፈታችን ፡ ይዘው ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ያጥኑልን ።



— ፲፯ —

እስላም ፡ ጂሃድ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡ ለማብረድ ፡ የሰደድ ፡ እሳት ፡ ለማጥፋት ፡ እንዲያስቸግር ፡ እንደዚሁ ፡ ያስቸግራልና ፡ በቶሎ ፡ ካልነቃንበትና ፡ በቶሎ ፡ ካላጠፋነው ፡ ስር ፡ ከሰደደ ፡ በኋላ ፡ ይልቁን ፡ ብዙ ፡ የክርስቲያን ፡ ደም ፡ ይፈስብናል ፡ ይኸም ፡ የተነሣንበት ፡ ሁሉ ፡ በሹመት ፡ በሽረት ፡ በማግኘት ፡ በማጣት ፡ አይደለም ፡ ለሃይማኖታችንና ፡ ለመንግሥታችን ፡ ስንል ፡ ነው ፡ ለዚሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ይመስክርብን ።

8

ስለ ልጅ ኢያሱ አሟሟት ሁኔታ የሚገልጹ ሦስት ዓይነት አባባሎች አሉ። አንደኛው እንደ ልጅ መስፍን ኢያሱ አገላለጽ "ጃንሆይ በ1928 ዓ.ም. ወደ ማይጨው ሲዘምቱ ሲሉ ያስመጡትና "እኛ ያስመጣንዎ ስለ ማይጨው ጦርነት እንዲያማክሩን ነው" ሲሉት "አንተ ያስመጣኸኝ ልትገለኝ ነው። ቀኑ ይረዝማል እንጅ አንተም ትገደላለህ" ብሎ መለሰና ወደ ማይጨው ሊሄዱ ሦስት ቀን ሲቀራቸው ተገደለ" ብለዋል።

ሁለተኛው አባባል ማይጨው ሊዘመት ሲል አባ ሃና ራስ አደፍርሰውና ደጃች መኮንን እንዳልኳቸው ቀደም ብለው በመኪና ሄደው ልክ ግራዋ ሲደርሱ ልጅ ኢያሱ ተጠርቶ ሲወጣ እንደሚገድሉት አውቆ ሲወተውት አብሮት የታሠረው አባ ሻንቆ መሣሪያ ነጥቆ ሲታከስ ሲሞክር ተገደለ። አስከትሎም ልጅ ኢያሱ ተገደለና ሁለቱም እዚያው ተቀበሩ የሚል ነው።

[8] ከዶክተር ብርሃኑ አበበ ANNALES D'ETHIOPIE መጽሐፍ የተወሰደ

ሦስተኛው ገለጻ ደግሞ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሚለው መጽሐፍ የገለጹት ሲሆን እሳቸውም መጋቢት 7 ቀን 1927 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ መሞታቸው በቤተ መንግሥት ተነግሮ ሃዘን ተቀምጠው ነበር ብለው አትተዋል። ይህንኑ ሁኔታ የሚያጠናክር ከአንድ ታሪኩን በደንብ አውቃለሁ ከሚሉ አዛውንት ሴት እንደሰማሁት "ልጅ ኢያሱ ከወልወል ግጭት በኋላ በ1927 ዓ.ም መሞቱ ተነግሮ ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ ቤት ሃዘን ተቀምጠው እቴጌ ልቅሶ መድረሳቸውን አውቃለሁ" ማለታቸውን ነው። ቀጥለውም "የአሟሟቱን ሁኔታ ግን አላውቅም" ብለዋል። ስለሆነም ይህ አባባል አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከጠቀሱት ወቅት ጋር ይገጥማል። ስለ ልጅ ኢያሱ አሟሟት ሕዝቡ በይፋ ሊገለጽለት ስላልቻለ እንዲህ ዓይነት ብዙ ሃሜት ቢነገር አይደንቅም።

ሥልጣን ከልጅ ኢያሱ ወደ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ቀጥሎም ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዞር፣ የነበረው ሁኔታ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። በመሠረቱ የመንግሥት ግልበጣ ነው ለማለት ይቻላል። አንድ የመንግሥት አመራር ላይ ያለን ሰው በኃይል አውርዶ በምትኩ ሌላ ካስቀመጡ የመንግሥት ግልበጣ መባሉ ተገቢ ነው። ግልበጣው የተደረገበትም ምክንያት የብዙ ጉዳዮች ውጤት ነው። የሃይማኖቱ ጉዳይ ዕውነትነቱ ቢያጠራጥርም ዕውቀት ባልተስፋፋበት አገር ውስጥ የሃይማኖት ነገር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ልጅ ኢያሱም በዘዴ ችግሮችን መወጣት ሲችል በልጅነት ምክንያትና የሚሰማቸው የበሰሉ አማካሪዎች በጎኑ ስላላሰለፈ ውድቀቱ ተፋጠነበት። በተጨማሪም የአያቱን መኳንንቶች ማክበር ሲገባው ጭራሽ ከማወረዱም በላይ አባቱ የቆረቆሩትን ከተማም ትቶ የአገሪቱን መናገሻ ከተማ ወደ ደሴም ለማዛወር መከጀሉ የሸዌን መኳንንቶች በማሳዘኑ ብዙ የሚወዱትም ቢኖሩ ከግልበጣው እንዳያድኑት ራሱ በሩን ዘጋ።

አፄ ምኒልክ ገና እንደታመሙ አልጋቸውን ስለሚወርሰው የልጅ ልጃቸው በማሰብ ከመኳንንቶቻቸው መካከል በውልደት የማይመኩትን ራስ ተሰማን ሞግዚት አድርገው ሾመውለት እያለ ታመው የአልጋ ቁራኛ ሲሆኑ የመንግሥት ሥራው በእቴጌ ጣይቱ መካሄድ ጀመረ። የአልጋቸው ወራሽ ልጅ ኢያሱ መሆኑን አውጀው ነበርና ራስ ተሰማ ከሌሎች መኳንንቶች ጋር በመደማደም የእቴጌን ሥልጣን በልጅ ኢያሱ ስም ይዘው ማስተዳደር ሲጀምሩ ብዙ



ነገሮችን ማበላሸት ጀመሩ። ልጅ ኢያሱ የሚኖረውም እሳቸው ቤት ስለነበረ ቤታቸው ውስጥ ሥነ ሥርዓት የተጓደለ ከመሆኑም በላይ ይህ ትንሽ ልጅ በወጣት ሴቶች የተከበበ አኗኗር ውስጥ ተዘፈቀ። ራስ ተሰማ ራሳቸው የሥልጣን ጥመኛ ስለነበሩ ለመንግሥም ሃሳብ ስለነበራቸው ገና ሥልጣን እንደጨበጡ ለንግሥናው ቅርበት የነበረባቸውን ልጅ ታየ ጉልላቴን አጋዙዋቸው። ዓመት ያህል እንዳስተዳደሩ ሽማግሌም ስለነበሩ በደም ብዛት ድንገት ወድቀው ወዲያው ሞቱ። ይህ ወጣት ልጅ ምናልባት ሌሎች መኳንንቶችን ያላስጠጋበት ምክንያት አንድም ራስ ተሰማ ጥላቻ አሳድረውበት ይሆናል። በተጨማሪም በአካባቢው የነበሩ ወጣት ምሁሮች ምናልባትም መኳንንቶቹን እናንቀውበትም ሊሆን ይችላል።



አቤቶ ኢያሱ በእስር ቤት

ይሁንና ልጅ ኢያሱ ከአንደኛ የዓለም ጦርነት በፊት የወገነው ከጀርመንና ከቱርክ ጋር ስለነበረ እነሱ በተሸነፉ ጊዜ የኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ ምን ይሆን ነበር ብሎ ለገመተ ሰው 'እንኳን በጊዜው ልጅ

ኢያሱ ወረደ' ብሎ መደምደም ይችላል። ባይወርድስ ኖሮ ከማይጨው ጦርነት የባሰ ነገር ኢትዮጵያ ላይ ይደርስባት ኖሯል? ምዕራባውያኖች የራሳቸውን ጥቅም እንጂ ወዳጅ የማያውቁ ስለሆኑ ምናልባት ልጅ ኢያሱ የወሰደው እርምጃ የተለየ ሁኔታ ሊፈጥር ይችል ነበር ማለትም ሌላ አማራጭ ነው። ልጅ ኢያሱ ተሽሮ ሌላ ሰው ሥልጣን ስለያዘ ኢትዮጵያ ወደቦችዋን እንደ አጣች ቀረች እንጂ ያገኘችው የተለየ ጥቅም አልነበረም።

## የልጅ ኢያሱ ትውልድ

ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን ላይ የወጣን ሰው ክርስቲያን ከሆነ ከንጉሥ ሰሎሞን ለማዛመድ እንደሚሞከረው ሁሉ ሙስሊምም ከሆነ ከነቢዩ ሙሐመድ እንዲዛመድ ጥረት ይደረጋል። ልጅ ኢያሱ የነቢዩ ሙሐመድ ተወላጅነት አለው ተብሎ ተወስዷል።

## የነቢዩ ሞሐመድ ትውልድ በልጅ ኢያሱ መስመር

1 ነቢዩ ሞሐመድ 519 ዓ.ም
2 ፋጡማ (የአሳብ አሊይ ሚስት)
3 ሁሴን (አንገቱን የተቀላው)
4 ዛና ላባዲን
5 ሞሐመድ አልባጂር
6 አብደላህ
7 ሙሳ አልካዲን
8 ዑመር
9 ታጅ አላህ
10 ያህያ
11 ኢስማኤል
12 ኑር አህመድ
13 ከሊል
14 ኢብራሂም
15 ሞሐመድ
16 ታማም
17 ታጅ አዲን
18 ሞሐመድ
19 ያጉት
20 ያኩብ
21 ኢማም ኑር
22 ላኒ አላህ
23 ኢሳ
24 አይሻ
25 ዛኒ ኤል ኬር
26 ኑር ሁሴን
27 ሻምስ አዲን
28 ኑር አዲን
29 ዲዋ አዲን
30 ጋፑ
31 ኢማም ዓሊ(ወደ ኢትዮጵያ መጡ)
32 ኢማም ሙሐመድ
33 ኢማም አህመድ
34 ኢማም ሙሐመድ
35 ኢማም ሊሃን
36 ኢማም ዓሊ (የንጉሥ ሚካኤል አባት)
37 ሞሐመድ ዓሊ (ንጉሥ ሚካኤል)
38 አቤቶ ኢያሱ[9]

[9] ከአምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ጽሑፍ የተወሰደ



የልጅ ኢያሱ አባት ንጉሥ ሚካኤል ወይም ሞሐመድ ዓሊ በእናታቸው በወይዘሮ ስሂን 1ኛ በኩል የአፄ ፋሲል 6ኛ ትውልድ ናቸው ተብሎ ተጽፏል። ነገር ግን እናታቸው ወይዘሮ ጌቴ ነበሩ እንጂ ወይዘሮ ስሂን 1ኛ አልነበሩም። የንጉሥ ሚካኤል አባት ኢማም ዓሊ የነቢዩ ሞሐመድ 36ኛ ትውልድ በመሆናቸው ልጅ ኢያሱ የነቢዩ ሞሐመድ 38ኛ ትውልድ ኾኖ ይቆጠራል።

ንግሥና እንደ ንግሥተ ሳባ ሕገ ደንብ መሠረት በአባት እንጂ በእናት ስለማይቆጠር ከዳግማዊ ምኒልክ በኋላ የነበረው ውስብስብ ችግር አቤቶ ኢያሱንም ጠልፎታል።

## የአቤቶ ኢያሱ ልጆች

አቤቶ ኢያሱ ብዙ ዕቁባቶች በማስቀመጥና ከየጎሣው በመውለድ አንድነትን አመጣለሁ ብሎ የሚያስብ በመሆኑ ብዙ ልጆች በየቦታው ወልዷል እየተባለ ይነገራል። እርግጥ መጀመሪያ ላይ ያሳይ የነበረው ባሕርይ ሥርዓት ያጣ መሆኑን ብዙ ሰው ታዝቧል። በሌላ መልኩ ይህንን ወጣት በርካታ ሰዎች እንዳካለቡት ይታወቃል። አንድ ቦታ ለጉዳይ በሄደ ቁጥር ሁሉም ወጣት ሴቶች ልጆች እያቀረቡ ይህችን አግባ ያችን አግባ እያሉ አስቸግረውታል። ከዚህም ሌላ ያረገዘች ወጣት ሴት ሁሉ የጸነሰኩት ከልጅ ኢያሱ ነው ስለምትል እውነተኛ ልጆቹ የትኞቹ እንደሆኑ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ተፈጥሯል። ይሁንና በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የአቤቶ ኢያሱ ልጆች ከየቦታው ብቅ እያሉ እነሱን በየምክንያቱ ማሰርና መቆጣጠር ራሱን የቻለ ችግር ፈጥሯል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው በመሳሳት የአቤቶ ኢያሱ ልጅነታቸው ተደብቆ የቀሩም ልጆች እንደሚኖሩ ይገመታል። ይሁንና ከዚህ በታች ልጅነታቸው የተደረሰበትን ሰዎች ስምና ታሪካቸውን ለመዘርዘር ተሞክሯል።

## ልጅ ግርማ ኢያሱ

ልጅ ግርማ ኢያሱ በጣሊያን ወረራ ጊዜ በስደት ኬኒያ ይኖር ነበር። በዚያ ቆይታው ወቅት የኬንያ የበላይ አስተዳዳሪ የነበሩት እንግሊዞች ለቁጥጥር ሲሉ በቀን ሁለት ጊዜ በአቅራቢያው ፖሊስ ጣቢያ እንዲፈርም አደረጉት። በዚህም ቁጥጥር ማብዛት የተነሳ በመሰላቸትና

በሰዎች ማበረታታት ምክንያት ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ውስጥ መፍረክረክ ሲጀምሩ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ሲሸሽ እዚያው ኬኒያ ውስጥ ተይዞ እስር ቤት ገባ። መጨረሻ ላይ ታቤት በሚባል እስር ቤት እያለ ታሞ ሆስፒታል ከገባ በኋላ በህክምና ላይ እያለ ሞቷል። ሆኖም ከሞተ በኋላ ሰው መርዝ ተደርጎበት እንደተገደለ ያወራል።

## ሚናስ ኢያሱ (ወልዱ)

ልጅ ሚናስ ኢያሱን ጎጃሜዋ እናቱ ለአንድ ባሕታዊ አደራ ብላ ሰጥታ ወደ ወሎ አብረው ሲጓዙ ዓባይ ሞልቶ ነበርና ሲያቋርጡ እርሷን ውኃ ወሰዷት ስትሞት ልጁና መነኩሴው ዳኑ። ሚናስም ወሎ ግሼን ማርያም አጠገብ በምትገኘው ሙፋ ኪዳነ ምሕረት እየተማረ ባህታዊ መስሎ አደገ። ጣሊያን በገባ ጊዜ ዝናውን ሰምቶ ያስረውና ቢመረምረው በጣም ሠላማዊና ዝንባሌው መንፈሳዊ መሆኑን ተረድቶ ፈታውና ቤትም ሰጥቶት አስቀመጠው። ከጠላት ወረራ በኋላ ከወሎዬ እናት የተወለደው ወንድሙ ልጅ ጌዲዮን ኢያሱ ፈረሱን አስጭኖ መሸፈቱ ሲሰማ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ሚናስን ይዘው ለጃንሆይ ላኩትና አልጋ ወራሽ ቤት ተቀማጭ ሆነ። በዚህን ጊዜ ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበና ልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን ይንከባከቡት ነበር።

ጃንሆይ ግን ወደ ወህኒ ቤት እንዲገባና ራስ አንዳርጋቸው መሳይ እንዲከታተሉት አድርገው ነበር። ራስ አንዳርጋቸውም ቢመለከቱት ሠላማዊና ጸሎተኛ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ በኃላፊነታቸው እንዲለቀቅ አደረጉ። ራስ አንዳርጋቸው መሳይ የፍርድ ሚኒስትር ስለነበሩ አሁን ግብረ ማርያም ትምሕርት ቤት የሆነው የፍርድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ውስጥ ሥራ እንዲጀምርና እዚያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ቤት ተሰጥቶት ተቀመጠ። የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤቱ አሁን የመከላከያ ሚኒስቴር ፎቅ ውስጥ ሲዛወር ግሚሱ የጦር ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ሆቴል ፊት ለፊት ያለው ደግሞ የፍርድ ሚኒስቴር ስለሆነ አብሮ ከነቤተሰቡ እዚሁ ግቢ ውስጥ መኖር ጀመረ። ከዚያም ደጃች ሰሎሞን አብርሃ የአባቱን ስም እንዲለውጥ መከሩትና ወልዱ ይሁን በማለቱ ልጅ ሚናስ ወልዱ ተባለ። በመጨረሻ የፍርድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በዋናው ፖስታ ቤት ፊት ለፊት ካሉት ሁለት ሕንጻዎች በአንዱ ውስጥ ሲዛወር፣ እሱም ጎላ ሠፈር ቤት ተከራይቶ እዚሁ መሥሪያ ቤት ሥራውን እየሠራ በመኖር ላይ እያለ



በ1957 ዓ.ም ምሽት ላይ ከሚሠራበት ፎቅ ላይ ወድቆ ሞተ። በዚህን ጊዜ የሶማሌ ሬዲዮ "የአቤቶ ኢያሱን ልጅ ሚናስን የኢትዮጵያ መንግሥት ከፎቅ ወርውሮ ገደለው" ሲል ተናገረ። ሚች ሰባት ልጆች ወልዶ እነሱም ወልደው ከብደው ተበራክተዋል። ሰባት ልጆቹም

1ኛ ጌታቸው ሚናስ — 2ኛ የሺ ሚናስ
3ኛ ልዑል ሰገድ ሚናስ — 4ኛ ብርሃኑ ሚናስ
5ኛ ሸዋዬ ሚናስ — 6ኛ ገነት ሚናስ
7ኛ ኤፍሬም ሚናስ

እንዲሁም የሰባት ልጆቹ እናት ወይዘሮ ፈለቀች ታደሰ ዛሬ በሕይወት ይገኛሉ።

## ጌዲዮን ኢያሱ

ጌዲዮን ኢያሱ የተባለ ከልጅ ኢያሱ የተወለደ ኃይለኛ ልጅ ነበረ። ከጠላት ወረራ በኋላ ብዙ ፈረስ አስጭኖ ለመሸፈት ወሎ ጠቅላይ ግዛት ወስጥ በርሃ ገባ። ከዚያ በኋላ ተይዞ ጋሞ ጎፋ ታስሮ ነበር። ከጌዲዮን ኢያሱ የተወለዱ ልጆች የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ እስጢፋኖስ ጌዲዮን
2ኛ በቃሉ ጌዲዮን (የአየር ኃይል ባልደረባ የነበሩ)

## ጎሹ ኢያሱ

ጎሹ ኢያሱ በግዞት ሲዳሞ ይኖር በነበረ ጊዜ የሚከተሉትን ልጆች አፍርቷል። 1ኛ ቱናን ጎሹ የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው
2ኛ ሉሊት ጎሹ ሲዳሞ ውስጥ ነዋሪ ናቸው።

## መልዓክ ፀሐይ ኢያሱ

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ከአቤቶ ኢያሱ ልጆች መካከል ሁለቱ በአርበኝነት ይታወቃሉ። ከመንዜዋ ባላባት የተወለደው እንግዳሸትን እቴጌ መነን ወደ ስደት ሲሄዱ ለባዕታ ገዳም አለቃ ለነበሩት አባ ይርዳው በአደራ ሰጡት። አባ ይርዳውም ጣሊያን ሲገባ ልጁን ይዘውት ቡልጋ ወስጥ ወደሚገኘው ገደራ አብዬ ገዳም ገቡ። ሻቃ በልሁ በኢጣሊያን ሲገደሉ አጋፋሪያቸው የነበሩት አለቃ ወልደ ጻድቅ ዘውዴ ጦራቸውን ይዘው ቡልጋ ሲገቡ እንግዳእሸትን አዩና የንጉሥ ልጅ እመሃከላችን እያለ እንዴት ዝም እንላለን? እንሸመውና ያስተባብረናል በማለታቸው እምቡር ገበያ ላይ ነጋሪት

እየመቱ እንግዳእሽት ኢያሱን መልዓከ ፀሐይ ንጉሠ ነገሥት አሰኝተው አወጁ። ከዚህ በኋላ ከያለበት አርበኛው ሁሉ ተሰበሰበና ሹመት ተካሄደ። በርከት ያለ ጦር አስከትለው የመጡት ባላንባራስ አበበ አረጋይ ስለነበሩ ራስ ተብለው የጦር አበጋዝ ኾነው ተሾሙ። አለቃ ወልደ ጻድቅም ፊታውራሪ ተባሉ። ራስ አበበ የራስ ጎበና ዳጬ የልጅ ልጅ ከመሆናቸው ሌላ ከባሊያን ወረራ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ በሻለቃነት ማዕረግ የአራዳ ዘበኞች አለቃ ነበሩ።

'ቀሪን ገረመው የአርበኞች ታሪክ' የሚለው መጽሐፍ ገጽ 146 ላይ "መልዓከ ፀሐይ ኢያሱ መስከረም 16 ቀንና 17 ቀን 1931 ዓ.ም የደመራንና የመስቀልን በዓል ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት የጥንቱን የኢትዮጵያ ባህል አክብረው ወታደራዊ ሠልፍም ተመለከቱ። ከሠራዊቱም ብዛት የተነሳ ሠልፉ ከስምንት ሰዓት የጀመረ እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ቆይቶ ነበር። የጥንቱንም የወታደር ልምድ ላለማስቀረት ሲባል በተገኘው ግብር ተደርጎ ነበር። በዚሁ ዕለት ልጅ መልዓከ ፀሐይ በድንገት ታመው ለሕመማቸው መፍትሔ ስላልተገኘ በቃሬዛ ወደ ገና መምቻ ወሰዷቸው። መስከረም 27 ቀን ሌሊቱን አረፉና አርበኞቹና መኳንንት በቃሬዛ ወስደው ቆቦ ማርያም በታላቅ ኀዘን በስውር ቀበሯቸው" ሲል ተዘግቧል። ልጅ መልዓከ ፀሐይ በነገሡ በስምንተኛው ወር ተመርዘው ሞቱ። ጥርጣሬው ከጅቡቲ የመጡ መነኩሴ መርዝ አቅምሰዋቸዋል ይባላል። በምን ምክንያት መነኩሴው እንደመረዟቸው ግን አልታወቀም።

## ደጃች ዮሐንስ ኢያሱ

ደጃች ዮሐንስ ኢያሱ በጎንደርና በጐጃም በአርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው ጃንሆይ ሲመለሱ በሥራቸው ያሉትን አርበኞች አሠልፈው እንደሌሎቹ አርበኞች ንጉሡን ተቀበሉ። ጎንደሬዎች ከራስ ጉግሣ ወሌ መገደል በኋላና በአጎታቸው በደጃዝማች አያሌው አለመሾም ምክንያት ቅሬታ ስለነበራቸው ጃንሆይ ከስደት ሲመለሱ የጎንደር አርበኞች "የሸሸ ንጉሥ አይነግሥም፤ ያፈረሰ ቄስ አይቀድስም" በማለት ንጉሡን አናስገባም ከማለታቸው በተጨማሪ ደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱን የማንገሥ ፍላጎትም አሳይተው ነበር። ጃንሆይ ደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱን ከአምስት ዓመት አርበኝነት በኋላ በእስር ወደ ከፋ ልከዋቸዋል። ደጃዝማች ዮሐንስ በርካታ ልጆች ወልደው በ1966 ዓ.ም ከመንግሥት ለውጥ በኋላ ተፈተው ከወንድማቸው ከልጅ ምኒልክ ኢያሱ ጋር ተገናኝተው



ተወያይተዋል። መጨረሻ ላይ ጅማ ሄደው ታመሙና ሞቱ። ደጃች ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ላይ በነበሩበት ወቅት ደብዳቤ በሚጽፉላቸው ጊዜ አክባሪዎ እያሉ እንጂ እንደሌሎቹ ባሪያዎ ባለማለታቸው ጃንሆይ ቅሬታ ነበረባቸው። ከልጆቻቸው መካከል ጀርመን አገር ነዋሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ግርማ ዮሐንስ በየጊዜው እስተያየታቸውን በተደጋጋሚ ይገልጻሉ።

## ቴዎድሮስ ኢያሱ

ስለ ቴዎድሮስ ኢያሱ ለማወቅ የቻልኩት ጋምቤላ ውስጥ ሽፍቶ ሲዋጋ ኖሮ በኋላ ናዝሬት ውስጥ ታስሮ እንደነበረ ነው።

## ልጅ ምኒልክ ኢያሱ

ምኒልክ ኢያሱ አዳል ውስጥ ተወልደው ፖለቲካ ውስጥ ሳይገቡ ከኢያሱ በመወለዳቸው ብቻ አፍንሬ በር እስር ቤት ከ25 ዓመት በላይ ታስረው በነጻ የተለቀቁ ናቸው። እሳቸውም የኢሳ ተወላጅ የኾኑትን ወይዘሮ መሪማ አብዱርሂማንን አግብተው ድሬዳዋ በሶማሊ መንደር ሲኖሩ ቆይተው ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ። ልጅ ምኒልክ ኢያሱ በጣም ብዙ ሰው የሚቆረቆርላቸው ነበሩ። አንደኛ ልጅ ለመውለድ ያልቻሉበትን ምክንያት ብዙ ሰዎች በተለያየ መልክ ይናገራሉ። ሁለተኛ ደግሞ ያለምንም ጥፋት በመወለድ ብቻ መጉላላታቸውን ማንንም ያሳዘነ ነው።

ምንም እንኳን ልጅ ምኒልክ ኢያሱ ፖለቲካ ውስጥ መግባት ባይፈልጉም አገራቸውን ለመርዳት በተጠየቁ ቁጥር የተቻላቸውን ለመፈጸም ወደኋላ አላሉም። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ የጅቡቲ ነፃነት ጉዳይ የተፋፋመበት ወቅት ነበረና የጅቡቲም የበላይ ባላባት አልአሪፍ ከልጅ ምኒልክ ጋር የአንድ አያት ልጆች ስለነበሩ ለማግባባት የተቻላቸውን ሞረዋል። አልአሪፍ ጃንሆይን የአክስቴን ባል የገደለ ነው እያለ ይጠላቸው ስለነበረ ለማየትና ለማነጋገር አይፈልግም ነበር። በደርግ ላይ ግን የግል ቂም ስላልነበረው ልጅ ምኒልክ ኢያሱ



ልጅ ምኒልክ ኢያሱ

በትቻላቸው የጅቡቲን መሪዎች ለማግባባት ጠቅመዋል።

## ልጅ መስፍን ኢያሱ

የልጅ ኢያሱ ልጅ ነኝ ዋልድባ ገዳም ውስጥ ተደብቄ ነው የኖርኩት የሚሉት ልጅ መስፍን ኢያሱ በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ታዋቂ ሆነው ነበር። ልጅ መስፍን ቀደም ብሎ ስማቸው መኮንን እንዳልካቸው የነበረ ሲሆን በ1983 ዓ.ም በጋዜጣ ስማቸው መስፍን ኢያሱ መባሉን ማስታወቂያ ካወጡ በኋላ በሕዝብ መካከል በይፋ ይጠሩበት ጀመር። ልጅ መስፍን የቤተክህነት ሰው በመሆናቸው ከፓትርያርኩ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እርዳታ ተደርጎላቸው ከብቶች በማርባት ይኖሩ ነበር። በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አዲስ አበባ ውስጥ ክብረ በዓል ሲኖር አባ ምርጥዋ ከሚባሉ ቀልደኛ አዝማሪ ጋር በመሆን ጎራዴያቸውን ይዘው አብረው ይንጎራደዱ ነበር።

ኢሕአዴግ ሲገባ ደርግ ዘግቶት የነበረውንና ወደ መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሚወስደውን መንገድ ያስከፈቱና ከማዘጋጃ ቤቱ ፈቃድ ውጭ የአፄ ምኒልክን ሐውልት ብርማ ቀለም ያስቀቡ ናቸው። ይኸ ሐውልት የተሠራው በነሃስ ነው። ስለሆነም መወልወል እንጂ የብር ቀለም መቀባት አልነበረበትም። ቀደም ብሎ ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ ከንቲባ በነበሩበት ወቅት የወርቅ ቀለም መቀባቱ ይታወሳል። በተጨማሪም በእሳት አደጋ በኩል ያለውና በብረት ሠንሰለት የተዘጋውን የአራዳ ጊዮርጊስ ቅጥር ግቢ በር ከባሕታዊ ገብረ መስቀል ጋር በመጋዝ ቆርጠው አስከፍተዋል። በዚህም ተከሰው ነበር።

የልጅ መስፍንን ልጅነት በከፊል ሰዉ አልተቀበለውም። እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱም ተጠይቀው "እኛ አናውቀውም" በማለት መልስ ሰጥተዋል።

## አባ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ

የአቤቶ ኢያሱ ልጅ እንደኾኑ የሚነገርላቸው አባ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ የሚባሉ የካቶሊክ መነኩሴ ሐረርጌ ውስጥ ይኖሩ ነበር። መልከ ቀና ስለሆኑና የልጅ ኢያሱ ልጅ ናቸው ተብሎ ስለሚነገር የአባታቸውን ስም ወልደ ነጎድጓድ አሰኝተው ቆዩ። በይበልጥ ሰው ስላስቸገራቸው



መልካቸውን ለማሳሳት ቅንድባቸውን እየላጩ ለመለወጥ ሞክረዋል። በወቅቱ እሳቸው ያስተምሯቸው ከነበሩት ዲያቆኖች መካከል አንዱ የአባታቸውን የልጅ ኢያሱን ፎቶግራፍ አውጥተው እንደ አሳዩዋቸው አጫውተውኛል። አባ ዮሐንስ መነኩሴ ስለነበሩ ልጅ ሳይተኩ ሞቱ።

## ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ

ስለ ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ ታሪክ በጥልቀት የሚያውቅ ሰው ስለታጣ ለማተት አልተቻለም። ይሁንና ትልቋ ሴት ልጅ እሳቸው እንደነበሩና ልጅ ኢያሱም ሞቱ በተባለ ጊዜ ልቅሶ ይደረስ የነበረው እሳቸው ዘንድ ነበረ። እንዲያውም እቴጌ መነን ልቅሶ የደረሱት ሸዋ ፀሐይ ኢያሱ ዘንድ ነው ይባላል።

## እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱ

የወንዶቹ ልጆቻቸው ሁኔታ እንደተጠቀሰው ሲሆን ከሴት ልጆቻቸውም መካከል በይፋ የሚታወቁት ከራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ከወይዘሮ ሰብለ ወንጌል የተወለዱት እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱ የሚባሉ እስከ ቅርብ ጊዜ በሕይወት ነበሩ። ልጃቸውም አቶ ዓለም ሰገድ አበበ ወይም ማሞ በመባል ይታወቃል።



እመቤት ዓለም ፀሐይ ኢያሱ (በግራ)
እናታቸው እመቤት ሰብለ ወንጌል ኃይሉ (በቀኝ)



# ምዕራፍ ፰

# ምስኪንዋ ንግሥት ነገሥት ዘውዲቱ

ዘውዲቱ ሚያዝያ 22 ቀን 1866 ዓ.ም ከአባቷ ከአፄ ምኒልክና ከእናቷ ከወ/ሮ አብችው በእነዋሪ ከተማ ጅሩ ተወለደች። ስመ ክርስትናዋም አስካለ ማርያም ነው።

የዘወዲቱን እናት ወይዘሮ አብችው በያንን አፄ ምኒልክ ከወሎ ግዛት ከወረኢሉ አውራጃ ዶሉ ከሚባል አካባቢ ያመጧቸው ሴት ናቸው። የኚሁ ሴትዮ ወንድሞች ደጃች ሺበሺ፣ ራስ ሃብተ ማርያምና ደጃች ቡስሪ በያን ናቸው።

ዘውዲቱ ምኒልክ በስድስት ዓመት ከመንፈቅ ዕድሜዋ የአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜ ላለው ለአፄ ዮሐንስ ልጅ ለራስ አርአያ ሥላሴ ተዳረች። ይኸም የሆነበት ምክንያት በጽዮኑ መንበር በተቀመጡት አፄ ዮሐንስና በይሁዳ አንበሳ ሥርወ መንግሥት መንበር ላይ ለመቀመጥ በሚጠባበቁት ዳግማዊ ምኒልክ መካከል መግባባትን ለመፍጠር ተብሎ ነው። ራስ አርአያ ሥላሴም ሲሞት የአዲስ አበባውን ፊታውራሪ ውቤ አጥናፍ ሰገድን አግብታ አራዳ ባለው አሁን ደጃች ውቤ ቤት ወይም የአዲስ አበባ የባህል ምግብ ቤት የሚባለው ውስጥ ትኖር ነበር።

አንድ ቀን ወይዘሮ ዘውዲቱ ባለቤትዋ ፊታውራሪ ውቤ በጥፊ ስለመቷት ተናዳ በማግስቱ ጧት አዘናግታ ጠፍታ ሄዳ ለአባቷ ተናገረች። አፄ ምኒልክ ፊታውራሪ ውቤን ጠርተው ወደ ጓዳ አስገቡና "ምነው መታኸኝ!" ብለው ጠየቋቸው። ፊታውራሪ ውቤ ደንግጠው



መልስ ባያገኙም አፄ ምኒልክ በትልቁ እጃቸው በጥፊ ብለው ወደ ቤታቸው ላኩዋቸው። ሆኖም ወይዘሮ ዘውዲቱ ወደ ቤቷ ለመመለስ ስላልፈለገች ተፋቱ። ቀጥሎም የጎንደርን ገዥና የእቴጌ ጣይቱን የወንድም ልጅ ራስ ጉግሣ ወሌን አግብታ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያንን አለፍ ብሎ አሁን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ጥበቃ ቢሮ ያለበት ቦታ ላይ ይኖሩ ነበር። በዚሁም ምክንያት ሠፈሩ የንግሥት ሠፈር ይባላል። ባለመታደል ወይዘሮ ዘውዲቱ ከሦስቱም ባሎችዋ ልጅ አልወለደችም።

አባትዋ አፄ ምኒልክ እንደታመሙ እርሳቸውን ለማስታመም ቤተ መንግሥት መጥታ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ትኖር ነበር። አፄ ምኒልክ ታህሣሥ 3 ቀን 1906 ቢሞቱም የመሞታቸው ሁኔታ ይፋ ስላልኾነ ቤተ መንግሥት ቆይታ በጥር ወር 1908 ዓ.ም አቤቶ ኢያሱ እቴጌ ጣይቱን ከቤተ መንግሥት በግዞት ወደ እንጦጦ ሲልካቸው እሷንም ርስቷ ወደ አለበት ወደ ሸዋ ፋሌ ላካት።

አቤቶ ኢያሱን ከመንግሥት ሥልጣን ለማውረድ በመኳንንቱ በኩል ስምምነት ቢደረስም ሆኖም እርምጃ ለመውሰድ ሕዝቡ የእምዬ ምኒልክ ተወላጅ ከሥልጣን መውረዱን ይቃወማል ተብሎ ስለተፈራ ወ/ሮ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥት እንዲኾኑ ታጩ። ታዲያ ሹመቱ ሊሰጣቸው መኾኑን የወይዘሮ ኢያሀሉሽም ግህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ወይዘሮ አማረች (በኋላ እማሆይ) እንደሰሙ "ይቅርብዎት ተያይዞን ኢየናሳሊም እንሂድ፣ ይህ ቀይ ሰይጣን አያኖረንም" ብለው ወይዘሮ ዘውዲቱን ቢመክሩዋቸውም አልመሰላቸውምና ሹመቱን ተቀብለው በ43 ዓመት ዕድሜያቸው ዙፋን ላይ ተቀመጡ።

ሹመቱ በሕዝብ ምርጫ ነው እየተባለ ተነገረ። በመሠረቱ ሕዝቡ በዚህ ሹም ሽር ምንም ተካፋይነት እንደሌለውና እንዲያውም በልጅ ኢያሱ መሻር ብዙ ሰዎች ደስተኛ እንዳልነበሩ የታወቀ ነው።

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ መንፈሳዊነት የሚያጠቃቸው ስለሆኑ ባለቤታቸውን ራስ ጉግሣ ወሌን ትተው በብህትውና ለመኖር መርጠዋል ተባለ። በጾም ጊዜ የቤተ መንግሥት ግብር በጣም ይዘገይ ስለነበረ ምናልባት ሃይማኖተኛነታቸው ዕውነት ይሆናል ለሚሉት ወገኖች ማረጋገጫ ይሆናል። ለማንኛውም ራስ ጉግሣ ጎንደርን እንደገና ተሹመው ከቤተ መንግሥት እንዲርቁ ተደረገ።



ቀዳማዊ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ

ደጃች ተፈሪ መኮንን ራስ ተብለውና አልጋ ወራሽ ኾነው በንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ መሾም ሲችሉ በሕዝብ ምርጫ ተሾሙ መባሉ ትክክል አሠራር አልነበረም።



ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ከነገሡ በኋላ የከፋ አገረ ገዥ የነበሩትን ራስ ወልደ ጊዮርጊስን የጎንደር ንጉሥ ብለው ዘውድ ደፉላቸው። ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ የአክስታቸው የወይዘሮ አያህሉሽም ማህለ ሥላሴ ልጅ ሲሆኑ ባለቤታቸው ወይዘሮ የሺ እመቤት ተሰማ የእቴጌ ጣይቱ አክስት ልጅ ነበሩ። ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ለአፄ ምኒልክ የአክስታቸው ልጅ ኾነው እያሉ በትዕዛዝ በደጃች ጎበና ዳጬ ሥር በተራ ባለሟልነት እንዲያገለግሉ ከተላኩ በኋላ ባሳዩት ጀግንነት ከአቶነት እስከ ራስ ማዕረግ በጥረታቸው ከፍ ያሉ ነበሩ። ሆኖም ከነገሡ በኋላ አንድ ዓመት ያህል እንደቆዩ ሞቱ።



ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ

ፖለቲካውን ለመምራትና ዘመናዊ ሥልጣኔን ለማስፋፋት ተፈሪ ለሚያደርጉት ጥረት ሁሉ ንግሥት ዘውዲቱ እንቅፋት አልሆኑም። ንግሥቲቷም በበኩላቸው ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ በተጨማሪ የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምሕርት ቤትንና የንግሥት ዘውዲቱ ማዋለጃ ሆስፒታልን ከፈቱ። ካሠሩዋቸው ቤተ ክርስቲያኖች መካከል

አዲስ አበባ ውስጥ...

- የታዕካ ነገሥት ባዕታ ለማርያም፣
- ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት፣
- ደብረ ነገሥት ቁስቋም፣
- ቅዱስ ዑራኤል ናቸው።
- ጴጥሮስ ወጳውሎስ፣
- ቂርቆስ፣
- ቅዱስ ዮሴፍ፡ ወኒቆዲሞስ፣

ከአዲስ አበባ ውጭ

- ፉሌ መድኃኔዓለም፣
- የረር ቅድስት ሥላሴ፣
- አዋሽ ቅድስት ማርያም፣
- ሜታ የወረብ ቅድስት ማርያም ናቸው።
- መናገሻ ማርያም፣
- ጀርሳለፎ ቅዱስ ገብርኤል፣
- አድአዘርጋ አዙነ ተክለሃይማኖት፣

ሊሎችም በማርጀታቸው ያሳደሱዋቸው
የአዲስ አበባው ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም፣
የእንጦጦ ቅድስት ማርያም፣
አቃቂ ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ናቸው።

ከዛጌ ሥርወ መንግሥት ነገሥታት መካከል ሀርቤይ ጳጳሱ ከእኛው ወገን መሆን አለበት የሚል ጥያቄ አቅርቦ ግብጾች በሽብልቅ ባስገቡት በአንቀጽ 42 መሠረት በጉባኤ ኒቅያ ቀኖና "ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው ጳጳስ አይሹሙ" ስለሚል አይቻልም በማለት ሲኖሩ ጉዳዩ በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ተቀስቅሶ ሳይሳካ ቀርቶ በንግሥተ ነገሥት ዘመን ግንቦት 18 ቀን 1919 ዓ.ም አራት ኢትዮጵያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ግብጽ አገር ሄደው ጳጳስ ሆነው ተመለሱ።
ኢትዮጵያ ውስጥ የምዕራባውያን ሥልጣኔን ለማምጣት አባታቸው አፄ ምኒልክ የቀየሱትን በሚገባ የተገነዘቡ ነበሩና በበኩላቸውም ትምሕርት እንዲስፋፋ አዋጅ አውጥተዋል። ዕድሜው ከ፯ እስከ ፳፩ ዓመት ድረስ የሆነ ልጅ ያለው ሁሉ

1ኛ የንባብና የጽሕፈት ትምሕርት
2ኛ በአገራችን ካለው የእጅ ሥራ ልቡ የሚወደውን


ለልጁ እንዲያስተምር የሚል ነው። ካላስተማረ ግን ፶ ብር ቅጣት ተጥሎበታል። ለዚህም የማስተማሩና የመቆጣጠሩ ኃላፊነት

1ኛ የንስሐ አባት
2ኛ የገጠር መሪጌታ
3ኛ የደብር አለቃ ሁሉ ግዴታ አለባቸው።

የቅጣቱም ገንዘብ ተሰብስቦ መልሶ ለድሃ ልጆች ማስተማሪያ እንዲውል ያዛል።

ንግሥቲቱ ሥልጣኔን ልጠቀም ብለው ሳያስቸግሩ ለ12 ዓመት ከመንፈቅ አልጋው ላይ ቢቀመጡም አልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ የንግሥት ዘውዲቱን ደጋፊዎች በማግለልና የራሳቸውን ደጋፊዎች በየቦታው በመሾም ኃይላቸውን አጠናክረው የመንግሥቱን ሥልጣን ለመውሰድ እንደጎለበቱ ይታይ ጀመር።





የምኒልክ ቤተ መንግሥት (ታላቁ ቤተ መንግሥት)

በመሃሉ ተፈሪን እናንግሥ የሚል አድማ መኖሩን የንግሥተ ነገሥት የግቢ ዘበኛ አለቃ ደጃዝማች አባ ውቃው ብሩ ስለሰሙ ተፈሪን ወደቤተ መንግሥቱ ሲገቡ ለመግደል ሲጠባበቁ እያለ በሊላ በር ሾልከው ገቡ። ከዚህ በኋላ ለንግሥት ዘውዲቱ ደጃዝማች አባ ውቃው የናቀኝ ንጉሥ ባለመባሊ እኮ ነው ብለው ተናገሩ። በዚህም የተነሳ ደጃዝማች አባ ውቃው ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ባለው የዕንቁላል ቤት ሮቅ ላይ ሸፍተው ግርግር ተነስቶ ነበር። ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱም ነገሩን ሳያጤኑ "እጅህን ስጥ!" ስላሉዋቸው ተይዘው በተፈሪ ችሎት የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው።

ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ተፈሪን "ምን አስቸኮልዎ? መንገዱን እየጠረግንና እያስተካከልን አይደለሞይ? እኔስ አርጅቻለሁ ኢትዮጵያን አላያትም! እባክዎ እንዳያፈራርሷት አደራ!" ብለው በክበሬታ ተናገሩ።

የወንጀለኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዴንት የነበሩት ዳኛ ደጃዝማች መስፍን ገመች በችሎት ላይ አልተገኙም። በኋላ ለምን እንደዚህ እንዳደረጉም ሲጠየቁ "በፍትሐ ነገሥቱ ባንዱ አንቀጽ ጌታውን የከዳና የወጋ ይሙት ሲል ደግሞ በሌላው አንቀጽ በጌታው የደረሰውን አደጋ ለመከላከል ሲል ቢገድል ሞት የለበትም ይላል፤ ስለዚህ የዚህ ሰው ጥፋት ማንኛው ነው"[10] አሉ። ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ግን የሞት ፍርዱን ሳያጸድቁ ቀሩና አባ ውቃው በእስር ተቀጡ። ከዚያ ወዲህ

---

[10] የታሪክ ማስታወሻ ገጽ 87

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ራስ ተፈሪ ተከራርፈው የሚነጋገሩት በሽማግሌ አማካኝነት ብቻ ኾነ።

በመሠረቱ ደጃዝማች አባውቃው ለንግሥት ተቆርቁረውና የሚደረገውን ደባ ስለደረሱበት ኃላፊነታቸውን በሥርዓት ቢወጡም ጉዳዩ ሁሉ የሥልጣን ሽሚያ ስለነበረ ደጃች አባውቃው በመቃወማቸው የተነሳ ተቀጡ። ግን በወር ውስጥ የተባለው ነገር በገሃድ ወጥቶ ቀኛዝማች ባንትይዋሉና ግራዝማች ይገዙ የሚመሩት ቡድን ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱን "ራስ ተፈሪን ያንግሡልን" ብለው ሲጠይቁ "እስቲ ልዋል ልደርና መከሬ መልሱን እሰጣችኋለሁ" ሲሉ ቢመልሱላቸውም "አይሆንም አሁኑኑ መልሱን ካልሰጡን ብለው ሰቅዘው ያዙዋቸው"። ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ነገሩ ስለገባቸው የነበራቸው ምርጫ መስማማት ብቻ ኾነና እሺ አሉ። ስለሆነም ራስ ተፈሪ ንጉሥ ተፈሪ ተብለው መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም ዘውድ ደፉ።

ከዚህ ሹመት በኋላ ግብር ሁለት ቦታ እየተበላ ሰው እየተከፈለ ንግሥቲቱና አዲሱ ንጉሥ ውስጥ ውስጡን አለመግባባት እየፈጠሩ ከመሄዳቸውም በላይ ቅሬታ ያላቸውን የንግሥቲቱን የበፊት ባልና የጎንደሩን ገዥ ራስ ጉግሣ ወሌን ማስወገድ አስፈላጊ ኾነ። ራስ ጉግሣ ወሌ ወደ አዲስ አበባ ሲጠሩ አኩርፈው ለመምጣት ስላልፈለጉ በነደጃች ሙሉጌታ የሚመራ ጦር ዘምቶባቸው ቋና አንቺም ላይ በውጊያ ላይ እንዳሉ ራሳቸውን በጎራዴ ተመተው ተገደሉ። በዚሁ ጦርነት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር በአይሮፕላን ቦንብ ተጣለ። ደጃች ሙሉጌታ የራስ ጉግሣ ወሌን ጭንቅላት አስቆርጠው በጆኒያ ይዘው መጥተው ለአዲሱ ንጉሠ ነገሥት ግዳይ አቀረቡ። ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱም ከባላቸው ሞት በኋላ በሁለተኛው ቀን መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞቱ ተለዩ። ልጅ ስላልነበራቸው መሬታቸውንና ንብረታቸውን ልዕልት ተናኘ ወርቅ እንዲወርሱ ተደረገ።





# ምዕራፍ ፱

# የተፈሪ ውልደትና ዕድገት

ከሐረር ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ኤጀርሳ ጎሮ፣ ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም ከወይዘሮ የሺ እመቤት የሰባት ወር ልጅ ተወለደ። ወ/ሮ የሺ እመቤት ስድስት ልጅ ወልደው የሞቱባቸው ስለኾነ ቤተዘመድ ሁሉ እሳቸው ልጅ ሊወልዱ ሲሉ ይጨነቃሉ። ሰባተኛው አዲሱ ሕፃን እንደ ተወለደ ቤተዘመድ እናቱ ካዩት ይሞታል ብለው ስላመኑ ግድግዳ ቀደው ከቤት አወጡት። እንዲህ ዓይነት ክስተት በሚፈጠርበት ጊዜ ወላጅ ሾተላይ[11] አለባቸው ተብሎ ይታመናል። ሾተላይ በባህል የሚታመነው ሰው ላይ ሊኖር የሚችል ኃይለኛ የዓይን ጨረር ሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ተደርጎ ነው።

ሕጻኑ በተወለደበት ቀን ከእናቱ መለየት ስለነበረበት፣ ከእናትና አባቱ ቤት ወጥቶ ዘመድ ቤት ማደግ ጀመረ። ወላጅ እናቱም የልጃቸውን ቁመት በገመድ ላይ ምልክት እያስደረጉ በማስመጣት ዕድገቱን በርቀት ይከታተሉና ልብስም እያሰፉ ይልኩለት ነበር። ያለመታደል ሆኖ የሕጻኑ ወላጅ እናት ወይዘሮ የሺ እመቤት ዓሊ እንደገና አርግዘው ስለነበረ ከ20 ወር በኋላ መጋቢት 6 ቀን 1886 ዓ.ም በወሊድ ምክንያት ሞቱ። ስለኾነም ሕጻኑ የእናት ጣዕም ምን እንደኾነ ሳያውቅ የአጎቱ የደጃች ብሩ ኃይለ ማርያም ባለቤት ወይዘሮ ትስሜ አባይርጋ ከእምሩና ከልጃቸው ከደስታ ብሩ ጋር አሳደጉት።

[11] የእናት ወይም የአባት የደም ዓይነት RH Negative ሲሆን የሌላኛው RH Positive ይሆንና የሁለቱ ወላጆች ደም ባለመጣጣሙ የሚከሰት ችግር ነው።

ከዚህ በተረፈ አብሮት ያላደገና ከጋብቻ ውጭ ከአባቱ የተወለደ ይልማ ከሚባል ታላቅ ወንድም በስተቀር ከሁለቱ ወላጆቹ የተወለደ ወንድም ወይም እህት ስላልነበረው የእህትና ወንድምን ጣዕም የማወቅ ዕድል አልገጠመውም። ራስ መኮንን የሐረር ገዥ ከመሆናቸውም በላይ፣ በጦር አዛዥነት በየጊዜው እየዘመቱ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጉዳይ ለማስፈጸም በአገር ውስጥም ኾነ በውጭ አገር በብዛት ይጓዙ ስለነበረ፣ ይህ ሕጻን ከወላጆቹ ጋር የማደግ ዕድል አልነበረውም። በዚህ ምክንያት የተፈሪ ብቸኛ አማራጭ እኩዮቹ ከኾኑት ከአባቱ አክስት ልጅ ከወይዘሮ መዝለቂያሽ ከተወለደው እምሩና ከእናቱ ታናሽ እህት ማሚት ገብሩ ጋር ማደግ ነበር።



ተፈሪ በልጅነት

ይህ ሕጻን የወጣለት የዓለም ስም ተፈሪ ሲሆን የክርስትና ስሙም ኃይለ ሥላሴ ነበር። ተፈሪ ሰውነቱ ቀጨጭ ያለ፣ መልከ መልካም፣ ብልህነት የሚታይበት፣ ቀይ ልጅ ነበር። ምንም እንኳን አባትየው ራስ መኮንን



ቆቀይ ዳማ ቢሆኑም፣ ቅላቱንና የሰውነቱን ቀጫጫነት የተመለከቱ አንዳንድ ሰዎች፣ ልጁ እንደሱ ቀጨጭ ያለ ሰውነት ካለውና ቤተኛ ከኾነው መሐመድ ዓሊ ከሚባለው ሕንዳዊ አረብ (ፓኪስታናዊ) ነው የተወለደው በማለት ያሙታል።



ተፈሪ በልጅነት ከአብሮ አደጎቹ እምሩና ማሚት ጋር

በጣሊያን ወረራ ጊዜ ‘ኃይለ ሥላሴን አልወድም’ የሚል ጋዜጠኛ ‘ጃንሆይ ከራስ መኮንን አይወለዱም’ ብሎ በቄሳር መልዕክተኛ የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ ጋዜጣ ላይ ቢጽፍም፣ በጊዜው የጣሊያን ፕሮፓጋንዳ የአማርኛ የበላይ ሹም የነበሩት ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ይኽንን ሃሳብ በመቃወም ጽፈዋል። እንዲያውም ይኽ ሃሜት ነበር ከበላይ ዘለቀ ጋር የተከሰሰው የራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት የልጅ ልጅ ማሞ ሃብተ ሚካኤል በዙፋን ችሎት ሞት ሲፈረድበት፣ “አንተ አረብ!” ብሎ ንጉሡ ነገሥቱን ለመስደብ ምክንያት የኾነው።

ተፈሪ የራስ መኮንን ልጅ መሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች አሉ። በራስ መኮንን በኩል ያሉት የሥጋ ዘመዶቹ ሁሉ እንደተፈሪ አጫጭር ናቸው። በወላጅ አባትና ልጅ መካከል ይታይ የነበረው ፍቅር ሌላው ምልክት ሲሆን ደግሞ የተፈሪ ብልህነትና ንቁነት ያመሳስላቸዋል። ምንም እንኳን ተፈሪ መልኩ የእናቱ ቢሆንም ራስ መኮንን ታላቁ ልጃቸው ይልማ እያለ ተፈሪን ገና በ13 ዓመቱ

ደጃዝማች ብለው መሾማቸውና ሊሞቱም ሲሉ ለፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ አደራ መስጠታቸው ለተፈሪ ልጅነት ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

በአባትነት የሚጠረጠረው መሐመድ ዓሊ ከበርቴ ነጋዴና ለየመኳንንቱ ገጸ በረከት መስጠት የሚያዘወትር ሰው እንደነበረና ተፈሪም ትልቅ ከሆኑ በኋላ እሳቸውም ዘንድ ቤተኛ የነበረ ነው። ድሬ ዳዋ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የከፈቱትም ዘመዶቹ ናቸው ይባላል። አዲስ አበባ ውስጥ አራዳ ፖስታ ቤት በመባል የሚታወቀው የዘመኑ ትልቅ ሕንጻ ባለቤትም የነበረ ሲሆን መቃብሩም በዚሁ ቤት ጓሮ ይገኛል። የተፈሪ ቅላት የውጭ ደም የተቀላቀለበት ዓይነት ነው ብለው የሚጠራጠሩም አሉ። ተፈሪ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ቅንድቡ በርካታ ቢሆንም ጢሙ ግን ዞማ እንጂ ሉጫ አልነበረም።



ተፈሪ በልጅነት ዕድሜ

አባትየው ራስ መኮንን በአንድ ወቅት ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ስለ ተፈሪ ሲናገሩ "የሰውነቱን ደቃቃነት ዓይታችሁ አትናቁት፣ አንድ ቀን ትልቅ ሰው ይወጣዋል" አሉ። በተፈጥሮው ሰውነቱ ደቀቅ ያለ ስለነበረ ሌሎች የመሳፍንትና ልዑላን ወጣቶች የአካል እንቅስቃሴ እያደረጉ



በፈረስ ጉግስም ኾነ ሌሎች የአካል እንቅስቃሴ ችሎታቸውን ሲያሳዩ፣ ተፈሪ ከትልልቅ ሰዎች ጋር ቁጭ ብሎ ይመለከታል። አንድ ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ "ምነው አንተስ ሄደህ ችሎታህን አታሳይም እንዴ?" ብለው ቢጠይቁት "ማን ይመልከታቸው?" ብሎ በመመለሱ ዳግማዊ ምኒልክ አነጋገሩ ሁለት ትርጉም ስለሰጣቸው በመገረም ተመልክተውት ዝም አሉ። ተፈሪ እስከ እርጅና ዘመን ድረስ ፈረስ ይወድዱ ስለነበረ ጃንሜዳ ውድድር ሲኖር ይገኛሉ።



መሐመድ ዓሊ ዘለዕል በስተቀኝ በነጩ ቀስት የተመለከተው ነው

በወጣትነት ዘመንም ራሳቸው ከልጅ ኢያሱ ጋር አዲስ ከተማ በሚገኘው በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በነበረው ክፍት ቦታ ላይ የፈረስ ጉግስ ይጫወቱ ነበር። በዚህ ጉግስ ጨዋታ መካከል ልጅ ኢያሱ የያዘው ዘንግ ጫፉ ላይ የብረት ጅንፎ

እንዳለውና የልጆቹን መከረር ስላዩ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ "እናንተ ልጆች ተው ይቅርባችሁ" ብለው ውድድሩን አስቁመዋል።

ተፈሪ ዕድሜው ለትምሕርት በደረሰ ጊዜ፣ በሰባት ዓመቱ፣ አባ ወልደ ኪዳን የሚባሉ አስተማሪ እቤት ውስጥ ተቀጥረው ከአብሮ አደጉ እምሩና ማሚት ጋር እስከ አሥር ዓመቱ በጥሩ ሁኔታ አማርኛና ግዕዝ የማንበብና የመጻፍ ትምሕርት አጠናቋል። ልዑል ራስ መኮንን የውጭውን ዓለምና የአገርንም ሁኔታ በደንብ የተመለከቱ ስለነበሩ፣ ልጃቸው ከአማርኛና ከግዕዝ በተጨማሪ የውጭ አገር ትምሕርት እንዲማርላቸው ፈለጉ። በዚህ የተነሳ በሐረር ከተማ ያሠሩት ሆስፒታል ውስጥ ዶክተር ቪታሊያ የተባለ ሃኪም በትርፍ ጊዜው በቀን አንድ ሰዓት ፈረንሳይኛ ልጃቸውን እንዲያስተምርላቸው አደረጉ። በተጨማሪም፣ አባ ሳሙኤል ወልደ ካህን የሚባሉ ኢትዮጵያዊ በካቶሊክ ሚስዮን ያደጉና ራሳቸውም የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የነበሩ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ተፈሪን አስተምረዋል።




ተፈሪና አባታቸው ራስ መኮንን

ተፈሪን ገና በ 13 ዓመቱ ራስ መኮንን መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ደጃዝማች ብለው በሐረርጌ ግዛት ውስጥ የጋራ ሙለታ አውራጃ ገዥ አድርገው ጥቅምት 21 ቀን 1898 ዓ.ም ከሾሙት በኋላ፣ "ልጄን ተፈሪን አደራ፣ ለዓይናችሁ እንዳትጠሉት ነው እንጂ ዕድሉ በፈጣሪ እጅ ነው" ብለው በመናገራቸው ሁሉም ሰው አዘነ። ራስ መኮንን በዚያው ዓመት



ለሥራ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ መንገድ ላይ እያሉ በጠና ታመሙና ጉዟቸውን አቋርጠው በመመለስ ቁልቢ ኾነው በህክምና ሲረዱ ቆይተው መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም አረፉ።

አስከሬናቸው ሐረር ጥምቀተ ባሕር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከባለቤታቸው ከወይዘሮ የሺ እመቤት ዓሊ አስከሬን ጎን አረፈ። ሆኖም



ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ብዙ ሰዎች ራስ መኮንን መሞታቸውንና መቀበራቸውን ቢያምኑም ከፊሉ ሕዝብ ደግሞ መነኑ እንጂ ሞቱ መባሉን አልተቀበለም።

# ምዕራፍ ፲


# ድብቋ ወ/ሮ የሺ. እመቤት

ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ የሚለው መጽሐፍ ላይም ይሁን በማንኛውም አጋጣሚ ልጃቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእናታቸውን ፎቶግራፍ አሳይተውም ኾነ የአባት ስም ተናግረው አያውቁም። ታሪክ ጸሐፊዎችም፣ በመፍራት ሊሆን ይችላል፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የአባት ወላጆች ሲዘረዝሩ የእናታቸውን አባት ስም ግን አይጠቅሱም። የሚገርመው ደግሞ፣ ከልጅየው ህልፈተ ሕይወትም በኋላ የእናታቸውን አባት ስም በጽሑፍ ወይም በይፋ ለመጥቀስ ብዙዎቹ እስከ አሁን አልደፈሩም። ስለኾነም በምንም ይፋ ነገር ላይ የወይዘሮ የሺ. እመቤት ምስል ለሕዝብ አልተናኘም።

ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ወይም ወይዘሮ ቂቶ የወይዘሮ የሺ. እመቤት እናት ቁመታቸው አጭር ሲሆን ብስል ቀይና በጣም ውብ የሆኑ ሴት ነበሩ። ትውልዳቸውም የስልጤ ጉራጌ ናቸው ይባላል። 'ከአንዲት ጉራጌ ሴት የሚወለድ ልጅ ትልቅ ንጉሥ ይሆናል' የሚል ትንቢት ስለነበረ የሸዋ መኳንንት ሁሉ የጉራጌ ሚስት እየፈለገ ያገባ ነበር። በተለይ የወለኔ ሴቶች ቆንጆዎች ስለነበሩ ብዙ መኳንንቶች ተረባርበውባቸዋል። ወለኔ ወሊሶ ከተማ አጠገብ ያለ አገር ሲሆን ነዋሪዎቹ ጉራጌዎች መልካቸው ቀያይና ቆንጆዎች ስለሆኑ ይመረጡ ነበር። የመኳንንቶቹ አማራ ሚስቶች በቅናት ጉራጌዎቹን ሴቶች "ምርኮኞች" ይሏቸው ነበር። ራስ ዳርጌ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን በይፋ ሚስትነት ሳይሆን በዕቁባትነት አስቀመጠው ሦስት ልጆች ወልደዋል። ይሁንና ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ሌሎች ልጆችም ከተለያዩ ሰዎች ወልደዋል።



ራስ ዳርጌ በምርኮ ጎንደር ሄደው በእስር ብዙ ዓመት ከቆዩ በኋላ ተለቀው ሸዋ ላይ ለመሾም በደጅ ጥናት ላይ እንዳሉ አንዱ ወንድማቸው አቤቶ ሠይፉ ሣህለ ሥላሴ ከእስር ቤት አመለጠ። እርሳቸውም ከዚሁ ሁኔታ ጋር በተያያዘ መልኩ ስለተጠረጠሩ መቅደላ ላይ ታስረው ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ሸዋ ላይ ራስ ዳርጌን ለመሾም አስበው አንድ ቀን አስጠርተዋቸው "ልፈታህ ነበረ፣ ግን ፈራሁህ!" አሏቸው ይባላል። አፄ ቴዎድሮስ የሸዋ እስረኞችን ብቸኝነት ተመልክተው አዘኑና ሚስቶቻቸው እንዲጠይቋቸው ስለፈቀዱ ራስ ዳርጌ ወለተ ጊዮርጊስ ትምጣልኝ አሉ።



ድብቋ ወ/ሮ የሺ.እመቤት

ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ራስ ዳርጌን ለመጠየቅ ወደ መቅደላ ለመሄድ በወረኢሉ በኩል ሲጓዙ በእንግድነት ዘመድ ቤት ያርፋሉ። በዚህ መሃል ደጃዝማች ዓሊ ጋምቦ የሚባል የወረኢሉ ተወላጅ የነድድና የካቤ ወረዳ ባላባት የሙስሊም ሃይማኖት ተከታይ የኾነና በጠገራ ብሩ ብዙት እጅግ የታወቀ ሃብታም የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን ቁንጅና በመመልከት እንደሚስት ያስቀምጣቸዋል። እሳቸውም የሺ.እመቤትንና ልክምየለሽን ከዓሊ ጋምቦ ወለዱ። ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ካስቀመጣቸው ዓሊ ጋምቦ ኮብልለው ወደ ሸዋ ተመለሱና ሸዋን

በወቅቱ ያስተዳድሩ የነበሩት በዛብህ አባድክር ስለነበሩ እሳቸውም የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን ቁንጅና በመመልከት እንደ ዕቁባት አስቀመጧቸው። በመሃሉ ከደጃች በዛብህ ሌላ ወንድ ልጅ ወለዱና ስሙም ማሞ ተባለ። ምኒልክ ወደ ሸዋ ሲመጡ በሸዋ የአፄ ቴዎድሮስ እንደራሴ የነበሩት በዛብህ አባድክር አላስገባም ብለው ተዋግተው ድል ሆኑና ተማረኩ። አፄ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ሲሆኑ ደጃች በዛብህ ከእስር አምልጠው በድጋሚ ተዋጉና ተይዘው ተገደሉ። በዚህን ጊዜ የተቀመጡበት አልጋ በጥይት እሳት ተያይዞ ሬሳቸው ጭምር ነደደ። ይህን አስመልክቶ ሕዝቡ የሚከተለውን ገጠመ።

አንተም ክፉ ነበርክ ጨካኝ አበዛብህ
እንደገና ዳቦ እሳት ነደደብህ።

ራስ ዳርጌም አፄ ቴዎድሮስ ሲሞቱ ከታሰሩበት ከመቅደላ ተለቀው ይመለሱና ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን አግኝተው እንደገና አብረው መኖር ጀመሩ። ይሁንና ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ከተለያዩ ሰዎች ልጆች ወልደው ስለጠበቋቸው መኖሪያቸው ከመጀመሪያው አጥር ጊቢ መሆኑ ቀርቶ በሁለተኛው አጥር ግቢ ቤት ሠርተው አስቀመጧቸው።

ከወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ የተወለዱት ሴት ልጆች አድገው ልክምየለሽ ግራዝማች ባንተ አይምጣን አግብታ ሦስት ወንዶች ልጆች ወለደች። እነሱም ላይ፣ ተፈሪና ከበደ ናቸው። የሺ እመቤት ደግሞ ለራስ መኮንን ተዳረች። የራስ መኮንን ባለቤት ወይዘሮ የሺ እመቤት እንደ እናትዋ ቀይ፣ ጠጉርዋ ሉጫና መልከ ቀና ነበረች። የሺ እመቤት ዓሊ ከራስ መኮንን በተደጋጋሚ ልጅ እየወለደች ሲሞትባትና ስትሰቃይ ቆይታ መጨረሻ ላይ ተፈሪን ወለደች። ቀጥሎም ለስምንተኛ ጊዜ ነፍሰጡር ሆና በወሊድ ምክንያት ሞተች።

ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ቀደም ብለው ከራስ ዳርጌ ወይዘሮ ትሰሜን፣ ወይዘሮ ፀሐይ ወርቅንና ደጃዝማች አስፋውን ወልደው ነበር። በመጨረሻም ከመንዜው ፊታውራሪ ገብሩ ደግሞ የመጨረሻዋን ሴት ልጅ ማሚትን ወልደዋል።

ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ከስልጤ የመጡ የጉራጌ ሴት እንደሆኑ ቢነገርም ትክክለኛ የውልደታቸው ታሪክ እንደሚከተለው ነው።



እናታቸው ወይዘሮ ይብረሁልሽ የስልጤ ጉራጌ ሲሆኑ ባላቸው ከፍተኛ የሲራራ ነጋዴ በመሆን ከስልጤ እስከ ትግራይ ድረስ ሸቀጣ ሸቀጥ በማመላለስ ሥራ የተሰማራ ከበርቴ ነበር። በአንድ ወቅት በወሎ በኩል ሚስቱን ወይዘሮ ይብረሁልሽን ይዞ ሲጓዝ የጁ ላይ ታመመችበትና በመቸገሩ በአካባቢው ላሉ ትልቅ ሰው አደራ ትቷት ሄደ። እኚህ ትልቅ ሰው ሼህ ሁሴን ጅብሪል ይባላሉ። ወይዘሮ ይብረሁልሽ ሼህ ሁሴን ዘንድ ኾና ስትታከም ትቆይና ሻል ሲላት ከባለአደራዋ ጋር ወዳጅነት ጀምረች። ነጋዴው ባሏ ሥራውን ጨርሶ ሲመለስ 'ተነሽ! እንግዲህ እንሂድ' ቢላት 'አልዳንኩም ገና ነኝ። አንተ ከፈለገህ ሂድ' ስላለች ሰውዬውም በሁኔታው ተናዶና አዝኖ ወደ አገሩ ተመለሰ። ወይዘሮ ይብረሁልሽ ከሼህ ሁሴን ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ላይ እያለች አንዲት ሴት ልጅ ወለደችና በአገሯ አጠራር ቂቶ ብላ ሰየመቻት። ይህች ቂቶ አድጋ ቆንጆ ስለነበረች ራስ ዳርጌ በወዳጅነት ያስቀመጧት ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ መሆንዋ ነው።

ሼህ ሁሴን ጂብሪል በይፋ የምትታወቅ አንዲት ሌላ ሴት ልጅ እንዳለቻቸው ብዙ ሰው ቢያውቅም የቂቶን መወለድ የሚያውቁ ግን በጣም የተወሰኑ ብቻ ስለነበሩ ጉዳዩ ምስጢር ሆኖ ቀርቷል። ይኸንን ታሪክ እንደ ደረስኩበት ለማመን ተቸግሬ መጨረሻ ላይ ትክክለኝነቱን የተረዳሁት ከተወላጅ በመስማቴ ነው። ቂቶ ወይም ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ በእርጅና ዕድሜያቸው የራስ ተፈሪን ቤት ማስተዳደርና መቆጣጠር አንዱ ሥራቸው የነበረ ቢሆንም የልጃቸውን የማሚት ገብሩን ልጅ የወይዘሮ የሺሃረግ ባልቻን ሴት ልጅ ወይዘሮ ሙሉሸዋ አድማሴን ከልጅነት ጀምረው አሳድገዋል። ወይዘሮ ሙሉሸዋ በአሁኑ ጊዜ ከመቶ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ቢሆኑም ነገር በጭራሽ አያሳስቱም። እሳቸውም በተራቸው የወይዘሮ የሴም ወርቅ እናት ሲሆኑ የአቶ ዳንኤል ታደሰም ሴት አያት ናቸው። ስለሆነም ወይዘሮ ሙሉሸዋ አድማሴ ዱባለ ይኸንኑ ታሪክ በተደጋጋሚ ለተወላጆቻቸው ያስረዱትና አሁንም ቢሆን የሚደግሙት ሃቅ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ አቶ በሪሁን ከበደ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ በሚለው መጽሐፋቸው ላይ የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ አባት አቶ የምሩ ይባሉ እንደነበረ ገልጸዋል። አቶ የምሩንም የአፄ ፋሲል 10ኛ ትውልድ ናቸው ብለዋል።



ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ (ቂቶ)

የወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ የሕይወት መጨረሻ ደግሞ ራሱን የቻለ ታሪክ አለው። ታሪኩ "የአፄ ምኒልክ የቀድሞ ባለቤታቸው ወይዘሮ ባፌና እሳቸውን ትተው ሌላ ስላገቡ አፄ ምኒልክን በመርዝ ለማስገደል ፈልገው በቤተ መንግሥት ወጣ ገባ የሚልና የሚታመን ሰው ሲፈልጉ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን ያገኛሉ። ወይዘሮ ባፌና ኃይለኛና የሚፈሩ ሴት ስለነበሩ ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስን "ይኸንን መርዝ ምግብ ውስጥ ጨምረሽ ለአጼ ምኒልክ እንድታቀርቢ በማለት አግባቡዋቸው። በዚሁ መሠረት ምግብ ሠርተው ሊያበሉ ሲሉ ለአፄ ምኒልክ ሰው አስቀድሞ ሹክ ብሏቸው ነበርና የቀረበውን ምግብ ለውሻ ቢሰጡት ውሻው ወዲያው ሞተ። ስለኾነም ወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ ተይዘው ፍርድ ላይ ቀርበው በችሎት ስለተበየነባቸው ባሶ ገቢያ ላይ በስቅላት ተቀጡ። የልጅ ልጃቸው ተፈሪም አፄ ምኒልክን የሚጠሉበት ምክንያት ከዚህ ሁኔታ ተነስተው ይመስላል ብለው የሚናገሩ አሉ። ከተወላጅ ያገኘሁት ማረጋገጫ ግን በመርዝ መገደላቸውን ሲሆን ምክንያቱ ግን አልተብራራልኝም።



የተፈሪ እናት ወይዘሮ የሺ. እመቤት በአንድ ወገን ከጉራጌና አማራ የተወለዱ ሲሆኑ በሌላ ወገን ከወረይሉ ተወላጅ ከደጃዝማች ዓሊ ጋምሶ እንደኾነ ቢነገርም ጃንሆይ ግን ስለ እናታቸው አባት ዝምታን መርጠው የወላጅ እናታቸውን ታሪክ እንዲታወቅ አላደረጉም። ዓሊ የምትለውን ስም ጃንሆይ ለመጥቀስ ያልደፈሩበት ምክንያት ልጅ ኢያሱን የወነጀሉበት ጉዳይ ራሳቸውንም እንዳይመለከታቸው በመፍራት ይኾናል። እንዲያውም ጃንሆይን ይኸ ሁኔታ ከልጅ ኢያሱ በላይ የከበባቸው ይመስላል። ይኸውም የሴት አያታቸው አባት ስም ሁሴን፣ የእናታቸው አባት ስም ዓሊ፣ የባለቤታቸው አያት ስም ዓሊ ሲሆን እንዲሁም በአባታቸው እናትም በኩል ወይዘሮ ይመኙሻል ቡንኝ የአፋር ተወላጅ በመኾናቸው ነው።


ተፈሪ መኮንን ገጽታቸው እናታቸውን ይመስላል የሚሉ ሰዎች ነበሩ። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ጃንሆይ የእናታቸውን ፎቶግራፍ ከየዘመዶቻቸው ያፈላልጉ እንደነበረና ለሚያቀርብላቸውም ሰው የገንዘብ ወሮታ ለማድረግ ሞክረው ነበር ይባላል። የወይዘሮ የሺ. እመቤት ፎቶግራፍ ይኑር አይኑር በእርግጠኛነት ባይታቅም የተወሰኑ ሰዎች እጅ እንደሚገኝ አንዳንድ ፍንጭ ተሰመቶ ቢጠየቁም ሰዎቹ ግን ፎቶግራፉን ለማሳየትም ኾነ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ፈቃደኛ አልሆኑም።



# ምዕራፍ ፲፩

## ተፈሪ በደጃዝማችነት

ተፈሪን በ13 ዓመት ዕድሜያቸው አባታቸው ራስ መኰንን ደጃዝማች ብለው ሐረርጌ ውስጥ የጋራ ሙለታ አውራጃ ገዥ አድርገው ሾሙዋቸው። አገሩን ፊታውራሪ ቆለዬ ተመድበው ሲያስተዳድሩት ተፈሪ ግን የደጃዝማችነት ማዕረግን ይዘው ሹመቱን እየተለማመዱ እንዲቆዩ ኾነ። ወዲያውም ራስ መኰንን ስላረፉ አፄ ምኒልክ የራስ መኰንን አርባ የሚወጣው አዲስ አበባ እኔ ዘንድ ስለኾነ ልጁን ተፈሪን ይዛችሁ በቶሎ እንድትመጡ ብለው አዘዙ። ተፈሪም ራስ መኰንን ለአፄ ምኒልክ ያስቀመጡትን ስጦታ ይዘው ከነሠራዊታቸው አዲስ አበባ ደርሰው የአርባ ቀን መታሰቢያው ሚያዝያ 22 ቀን 1898 ዓ.ም በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተዘከረ።




ደጃዝማች ይልማ መኰንን

ተፈሪ የአባታቸውን ግዛት ሐረርጌን ለመሾም ሲጠባበቁ፣ አፄ ምኒልክ በእቴጌ ጣይቱ ግፊት የራስ መኰንን ትልቁ ልጅ ደጃዝማች ይልማን ሐረርጌ ላይ ሾሙና ሰላሌን ደግሞ ለትንሹ ልጅ ለደጃዝማች ተፈሪ ሰጥቻለሁ ብለው አወጁ። ተፈሪ በልጅነት ዕድሜያቸው የሰላሌ አገረ ገዥ ኾነው በነበሩበት ጊዜ፣ አገሩን በእንደራሴ እያስተዳደሩ አዲስ አበባ ደጅ እየጠኑ፣ በዳግማዊ ምኒልክ ትምሕርት ቤት መማር እንደሚፈልጉ አፄ ምኒልክን አስፈቅደው፣ ትምሕርት ጀመሩ። ነገር ግን፣ ተማሪዎቹ ገና ጀማሪ ስለነበሩና ቀደም ብለው ተፈሪ የተማሩትን ሊሎቹ ያልደረሱበት



ስለኾነ ለብቻቸው እየተማሩ ቆዩ። የደጃች ተፈሪ ትልቅ ወንድም ደጃዝማች ይልማ ሐረር ላይ በተሾሙ በዓመት ከአምስት ወራቸው ሞቱ። ከወንድማቸው ከደጃዝማች ይልማ ሞት በኋላ ሐረርን ደጃች ተፈሪ ይሾማሉ ተብሎ ሲጠበቅ ሹመቱ ለደጃዝማች ባልቻ ተሰጠ። ደጃች ተፈሪም እንደገና ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛትን ተሾመው ሄዱ።

በዘመኑ አንድ አገረ ገዥ ከግዛቱ የሚያገኘው ጥቅም ሁሉ በፊናው ለንጉሠ ነገሥቱ ከሚገብረው ሌላ የራሱ ጥቅም ስለኾነ ከአንዱ ግዛት ሌላው ስለሚሻል እንደ ሐረርጌ ያሉ ግዛቶች በጣም ይመረጣሉ። በተለይ ሐረርጌ የውጭ ዕቃዎች በጅቡቲ በኩል የሚገቡበት በር ስለነበረ ጥቅሙ ቀላል ስላልኾነ ሐረርጌን መሾም ማለት መታደል ነበር።



ደጃች ተፈሪ መኰንን በለጋ ዕድሜ

ተፈሪ ሲዳሞ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላ እዚያው እንዳሉ አፄ ምኒልክ መታመማቸውን ሲሰሙ ወደ አዲስ አበባ አስፈቅደው መጡ። አዲስ አበባ ሲመጡም ቤተ መንግሥት ውስጥ የሥልጣን ውዝግብ ስለነበረ ደጃች ተፈሪ ድምጻቸውን አጥፍተው ተቀመጡ። እቴጌ ጣይቱ በሚኒስትሮቹና በመኳንንቶቹ ውዝግብ ውስጥ ደጃች ተፈሪ አልገቡም ብለው በማመን ሐረርጌን ሾመዋቸው ወደ አዲሱ ግዛታቸው በደስታ ሄደው ያስተዳድሩ ጀመር።

አንድ ወቅት የሐረርጌ ገዥ ኾነው ሲኖሩ የሚስታቸው የወይዘሮ መነን አጎት ደጅአዝማች ኃይለ ማርያም ሚካኤል ሞተው ስለነበር ወይዘሮ መነን ለልቅሶ ወደ አዲስ አበባ ተሸኙ። ደጃች ተፈሪ እቴጌ መነንን ሸኝተው ሲመለሱ ዓለማያ ሃይቁ ዳር እረፍት ተድርጎ በጀልባ ከሌሎች መኳንንቶች ጋር ለሽርሽር

ሃይቁን አቋርጠው ሲመለሱ ሃይቁ መካከል ጀልባው መስመጥ ጀመረ። ተሳፋሪዎቹ በባርኔጣቸውና በተገኘው ነገር ሁሉ ውኃውን እየጨለፉ ወደ ውጭ ቢረጩም የሚገባው ውኃ እየበዛ ሲሄድ ጀልባዋ እየሰመጠች ሄደች። በዚሁ አደጋ ሰባት ሰው ሲሞት ተፈሪና ሌሎች ሁለት ሰዎች በዋናተኞች ዕርዳታ ሕይወታቸው ሊተርፍ ችሏል። ደጃዝማች ተፈሪን በተለይ ዋኝተው ያዳኗቸው የፈረንሳይኛ አስተማሪያቸው የነበሩት አባ ሳሙኤል ሲሆኑ እሳቸውን ካወጡ በኋላ ሌላ ሰው ለማውጣት ሲታገሉ ስለደከሙ ሰምጠው ሞተዋል።



ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን

አንዳንድ ሰዎች ይኸንን አደጋ ደጃች ተፈሪን ለማጥፋት የተደረገ የልጅ ኢያሱ ተንኮል አድርገው ቆጥረውታል። እነሱም ሊመለሱ ሲሉ ተሳፋሪዎቹ ሳያውቁት ሆን ተብሎ ጀልባው ከሥሩ ተቆርቁሮ ውኃ እንዲያስገባ ተደርጎ ስለነበረ ሃይቁ መካከል ሲደርሱ እየሰመጠ ስለሄደ ዋና የማይችሉት ሰመጡና ሞቱ። ሆኖም አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች "ጀልባው አሮጌ ስለነበረ ነው" ብለው ያትታሉ። ሌሎች ደግሞ ጀልባው ላይ የተሳፋሪ መብዛት ያመጣው አደጋ ነውም ይላሉ።

ልጅ ኢያሱ የመንግሥቱን ሥልጣን ከተረከቡ ከአምስት ዓመት በኋላ ደጃች ተፈሪ ሐረርን በማስተዳደር ላይ እያሉ ወደ አዲስ አበባ ጠርተው ራሳቸው ልጅ ኢያሱ ድንገት ተነስተው በባቡር ወደ ሐረር ሄዱ። ሐረር ላይም ኾነው ተፈሪን ከሐረር ገዥነታቸው አንስተው ከፋ ላይ ሾሙዋቸው። በዚህን ጊዜ ደጃች ተፈሪና ልጅ ኢያሱ በቃለ መሃላ ሲተሳሰሩ ልጅ ኢያሱ ተፈሪን ከአባታቸው ግዛት ሐረርጌ እንዳይሽሯቸው ደጃች ተፈሪም የልጅ ኢያሱን ሥልጣን እንዳይቀናቀኑ የተስማሙትን ልጅ



ኢያሱ ሻሩ። ደጃች ተፈሪም ስምምነቱ መሻሩን ተገንዝበው በራሳቸው በኩል ማድረግ ያለባቸውን ለመፈጸም ውስጥ ውስጡን መዘጋጀት ጀመሩ። ደጃች ተፈሪን ወደ አዲሱ ሹመት አገራቸው እንዲሄዱ ልጅ ኢያሱ ቢወተውቱም ተፈሪ ከአዲስ አበባ ሳይንቃነቁ ልጅ ኢያሱ ተሻሩና ደጃች ተፈሪ ራስ ተብለው አልጋ ወራሽ ሆኑ።

መሳፍንቶችና መኳንንቶች ልጅ ኢያሱን ከመንግሥት ሥልጣን አውርደው ተፈሪን ለመሾም ሲዘጋጁ ደጃች ተፈሪ ደግሞ ጢት ጢት በየመኳንንቱ ቤት ደጅ እየጠኑ ውስጥ ውስጡን ይገፋፉ ነበር። ከፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ጋር እንዲያማልዷቸው ነጋድራስ ተሰማ እሸቴን ደጅ በሚጠኑበት ጊዜ ተኝቷል እያሰኙ አጉላልተዋቸዋል። ምክንያቱም ነጋድራስ ተሰማ የልጅ ኢያሱ ወጣት ምሁር አማካሪ ከመኾናቸውም በላይ ልጅ ኢያሱን በጣም የሚወዱ ሰው ስለነበሩ ነው።

የውጭ አገር ሌጋሲዮኖች በቀጥታ በአንድ አገር ውስጥ ጉዳይ ላይ አይገቡ እንጂ ልጅ ኢያሱ ተሽሮ ተፈሪ እንዲሾሙ የበኩላቸውን ማግባባት በምስጢር አድርገዋል። ይህንንም ያደረጉበት ምክንያት ልጅ ኢያሱ በሶማሊና በአፋር ያሉትን ባላባቶች የአገር ፍቅር ከፍ እንዲልና በዚያውም ጦር እንዲያዘጋጁ ሲያሰናዳቸው ሌሎቹንም ደጃዝማቾች ቅኝ ገዥዎችን ለማባረር ጦር እንዲያዘጋጁ በማዘዙ በጉዳዩ ሌጋሲዮኖቹ ተጨንቀውበት ስለነበረ ነው። ስለኾነም ልጅ ኢያሱን ከሥልጣን አውርደው ተፈሪን ያሾሙዋቸው በተባባሪነት የውጭ አገር በተለይ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ሌጋሲዮን ሚኒስትሮች ጭምር ነበሩ።

ባሽከሮቹ ከፋት ደግሞ ባጋፋሪ
ዘውዱ ቷሆር ዓየን ወደ ልጅ ተፈሪ


ሼህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፲፪

# ድንግተኛው የተፈሪ ጋብቻ

ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ከወ/ሮ መነን አስፋው ጋር ሐምሌ 23 ቀን 1903 ዓ.ም ተጋቡ። ወይዘሮ መነን የወሎው ራስ ሚካኤል የልጅ ልጅ ናቸው። ስለሆነም ልጅ ኢያሱ አጎታቸው ነው። በዘጠኝ ዓመት ዕድሜያቸው ወሎ ውስጥ ለሊጋምቦ ባላባት ለደጃዝማች አመዴ ዓሊ ካቦ ሽንቁር ተድረው ሁለት ልጆች ወልደዋል። እነሱም



እቴጌ መነን አስፋው ዓሊ

ጀንጥራር ገብረ እግዚአብሔር አመዴና ወ/ሮ ዘነበች አመዴ ናቸው።

ጀንጥራር ገብረ እግዚአብሔር የልዑል አሥራተ ካሣ ባለቤት የነበሩትን ልዕልት ዙሪያሽ ወርቅን ወለዱ። ሁለተኛዋ ልጃቸው ወይዘሮ ዘነበች ፊታውራሪ ዓሊ ፋሪስን ወልደዋል።

ወይዘሮ መነን ለሁለተኛው ጊዜ የተዳሩት ለጭሬቻ ባላባት ለፊታውራሪ ዓሊ መሐመድ ሲሆን ልጅ አልወለዱላቸውም። ከዚያም ከሦስተኛው ባላቸው ከራስ ልዑል ሰገድ ምንም ልጅ ሳይወልዱ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ፣ ራስ ቢትወደድ ተሰማና ልጅ ኢያሱ አፋተዋቸው ለደጃዝማች ተፈሪ ዳሩዋቸው። ምክንያቱም ደጃች ተፈሪና ልጅ ኢያሱ ለአልጋው ተቀናቃኝ ስለሆኑ በሁለቱ መካከል ዝምድናን ለማጥበቅ ነበር። እነ ራስ ቢትወደድ ተሰማ በልጅ ኢያሱና በደጃች ተፈሪ መካከል ያለው ተፎካካሪነት ስላሰጋቸው ቀደም ብለው ሁለቱንም እንዳይጠፋፉ አስምለዋቸው ነበር። አሁን ደግሞ የሁለቱን ወዳጅነት ለማጥበቅ ሲሉ ይህንኑ ጋብቻ አሳክተዋል።



ደጃዝማች ተፈሪ ለወ/ሮ መነን አራተኛ ባል ናቸው። ወ/ሮ መነን ምንም ፈት ቢሆኑም ከደጃዝማች ተፈሪ ጋር የተጋቡት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው። ሁለቱ በተጋቡ ጊዜ ዕድሜያቸው የተፈሪ 19 ሲሆን የመነን 20 ዓመት ነበር።



እቴጌ መነን አስፋው ከአጎታቸው ከልጅ ኢያሱ ጋር

ወ/ሮ መነን የተወለዱት መጋቢት 25 ቀን 1883 ዓ.ም ወሎ በአምባሰል አውራጃ ልዩ ስሙ እጓ በሚባል ስፍራ ከእናታቸው ከወ/ሮ ስሂንና ከአባታቸው ከጀንጥራር አስፋው ዓሊ ቡሩ ነው። እናታቸው ወ/ሮ ስሂን ሚካኤል የተወለዱት ከጎንደሬዋ ከወ/ሮ ፋንታዬ ነው።

የደጃች ተፈሪ እጮኛ በጣም ውብ የኾኑና በኋላ የራስ ጌታቸው አባተ ቧ ያለው ባለቤት የነበሩት ወ/ሮ አስቴር ሲሆኑ ራስ ጌታቸውና ደጃች ተፈሪ አለመግባባት ላይ የደረሱት በእሳቸው ምክንያት ነበር ይባላል።

አገር በጠላት ሲወረር የአንድ እቴጌ ድርሻና ኃላፊነት ምን እንደሆነ በግልጽ ተዘርዝሮ የተለየ ኃላፊነት በታሪክ ባይወሳም በተለምዶ ጦርነት የወንድ ግዳጅ እንጂ የሴት እንዳልነበረ ይታወቃል። እቴጌ ጣይቱ ግን በዚህ ላይ የተለዩ እንደነበሩ በአድዋ ጦርነት የግላቸውን ሦስት ሺህ ጦር ከመምራት ሌላ በስንቅ ዝግጅት ላይና ጠቅላላውን ጦር በማበረታታት ብዙ ተሳትፈዋል። አስቀድሞም ለባለቤታቸው የፖለቲካ አማካሪ ስለነበሩ በውጫሌ ውል መሰረዝ የራሳቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል። እቴጌ መነን ግን ቀድሞውንም ቢሆን በፖለቲካው ወስጥ ለመሳተፍ ዕድሉ አልተሰጣቸውም። በሹመት እቴጌ ቢሆኑም እቤት ቁጭ ብለው ልጅ መውለድ እንጂ ሌላ ግዳጅ ውስጥ ባይገቡም ጣሊያን ወረራውን ሲጀምር ንፋስ ስልክ ሄደው የሬዲዮ መልዕክት ከማስተላለፍ በተጨማሪ ለቁስለኞች የሚያገለግል የህክምና ጥብጣብ (ፋሻ) በሚዘጋጅበት ስፍራ ሄደው ከማበረታታት ሌላ የፈጸሙት ጉልህ ነገር አልነበረም።

በአንድ ትዳር ውስጥ ብዙውን ጊዜ ሁለት ኃይለኛ ሊኖር ስለማይችል ወንዱ በጣም ኃይለኛ ሲሆን ሴቲቱ ዝምተኛ፣ በተቃራኒው ደግሞ ሴቲቱ በጣም ኃይለኛ ስትሆን ወንዱ ለስላሳ፣ ካልሆኑ አብሮ መኖር ያስቸግራል። አንዳንዴ ሁለቱ ጾታዎች በአንድ ትዳር ውስጥ እኩል ተሳትፎ ያላቸው እንደነበሩ ይታወቃል። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ናቸው። የኢትዮጵያ ታሪክ የሚያወሳቸው ኃይለኛና ዘዴኞች እቴጌዎች ነበሩ። እነዚህም እቴጌ እሌኒ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ባለቤት፣ እቴጌ ምንትዋብና እቴጌ ጣይቱ ነበሩ።



እቴጌ መነን አስፋው

እቴጌ መነን በማይጨው ጦርነት ጣሊያን ኢትዮጵያን ወርሮ ሲሰደዱ ለእንጦጦ ራጉኤል ስዕለት ገብተው ነበር። ስዕለታቸውም ለቅዱስ ራጉኤል "ከአገራችን ጣሊያን ተባርሮ ባንዲራችን እንደገና ከተመለሰች ቤተ ክርስቲያንህን አሠራለሁ" የሚል ነበር። በዚህም የተነሳ ከስደት መልስ የእንጦጦ ራጉኤልን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደስ ሲነሱ ጃንሆይ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ብታሠሪለት ይሻላል ብለው አዲስ አበባ ውስጥ አዲስ ከተማ አንዋር መስጊድ አጠገብ የፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ መኖሪያ ቤት ጎን የሚገኘውን ቦታ ሰጧቸው። በዚህ የተነሳ የራጉኤል ቤተ ክርስቲያንን አሠርተው ታቦቱን ከእንጦጦ አስመጥተው አስገቡት። በፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ዳግማዊ ምኒልክ ከአሠሩት ቤተ ክርስቲያን መወሰዱን የሚጠሉ ሰዎች አቡኑን ሌላ የቅዱስ ራጉኤል ታቦት ተክቶ የምኒልክን ታቦት ወደ ነበረበት እንጦጦ እንዲመለስ አስፈቀዱ። በዘመኑ ደርግ የሃይማኖትን ነገር ይጫኑን ስለነበረ በአካባቢ ያሉ ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች በሃይማኖት በኩል አንድ ዓይነት አቋም ስለነበራቸው ታቦቱን እንደማያስነኩ ይታወቅ ነበር። ስለሆነም ጥቂት ቀሳውስት ሌሊት ታቦቱን በሌላ ተክተው ሊወስዱ ሲሉ ደወል ተደወለና ሕዝብ ተሰብስቦ አለመግባባት ተፈጠረ። በዚህም ጊዜ አንድ ቄስ ሲገደሉ ሌሎችም ቆስለው ታቦቱ እዚያው እንዳለ ቀረ። የእንጦጦ ራጉኤል



እምዬ ምኒልክ ያሠሩት ስለነበረ የቤተ ክርስቲያኑ መታደስ ቅርሰነት ሊኖረው ሲገባ በአሁኑ ወቅት የራጉኤል ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ቀርቶ የእንጦጦ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን በመባል ይታወቃል።

ለኢትዮጵያ ሴቶች ምሳሌ ለመሆን እቴጌ መነን የተለያዩ የአገር ልብሶችን በየጊዜው ይለብሱ ነበር። ዙሪያ ጥበብ ለመጀመሪያ ጊዜ የለበሱ እቴጌ መነን ነበሩ። ለዚህ አድራጎታቸው የአገር ፍቅር አርቲስቶች ዘፈን ዘፍነውላቸዋል።

ፈትላለች መነን ፈትላለች መነን
የጥበብ ኩታ ልታላብሰን" የሚል ነበር።

እቴጌ መነን ብዙ መሬት ያላቸው ባለጸጋ ሲሆኑ ጠባያቸው ጨዋና እርጋታ ያላቸው ምንም ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ያልገቡ ቁጥብ ልዕልት ነበሩ። ባለቤታቸውን ምንም እንኳን በአንድ ዓመት ቢበልጧቸውም እርስዎ ብለው ነበር የሚጠሯቸው። ከሰውም ጋር ሲያወሩ ጌቶቼ! ብለው ነበር የሚያነሱዋቸው። ትንሽም ገንዘብ ውጭ አገር ስለነበራቸው የልጅ ልጆቻቸው በስደት ላይ በነበሩበት ወቅት ለችግራቸው ደረሶላቸዋል ይባላል።

እቴጌ መነን ትምሕርታቸው ከአማርኛ ማንበብና መጻፍ የዘለለ መሆኑ አይታወቅም። ንጉሠ ነገሥቱ ከ1916 ዓ.ም አንስቶ እስከ 1954 ዓ.ም ድረስ የውጭ ጉብኝት ሲያደርጉ እቴጌይቱ ግን እሥራኤልንና ግብጽን ከመጎብኘት በስተቀር ወደ ሌላ አገር አብረው አልሄዱም። ጋብቻው ለ51 ዓመት ጸንቶ ስድስት ልጆች ወልደው በ1954 ዓ.ም እቴጌ መነን በ71 ዓመት ዕድሜ በሞት ሲለዩ ከስድስቱ ልጆቻቸው መካከል በሕይወት የነበሩት ልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰንና ልዑል ሣህለ ሥላሴ ብቻ ነበሩ። ሆኖም ልዑል ሣህለ ሥላሴ ከሁለት ወር በኋላ በህመም ምክንያት አርፈዋል። ከእቴጌ ሞት በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀረውን ዕድሜያቸውን በብቸኝነት ጨርሰውታል።



# ምዕራፍ ፲፫

## ራስ ተፈሪ በአልጋ ወራሽነት

የራስ ተፈሪ አልጋ ወራሽነት ከንግሥተ ነገሥት ዘወዲቱ ንግሥና ጋር አብሮ የተፈጸመ ስለነበረ ምንም በልጅ ኢያሱ መሻር ምክንያት ቅሬታና ጠርነት ቢኖርም በደጋፊና በኃይል ሚዛን ተሳክቷል። ሆኖም ሹመቱን የመንግሥት ግልበጣ አድርገው የሚያዩትና የልጅ ኢያሱ መሻር የሚቆጠቁጣቸውና ጉዳትም የደረሰባቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ። አልጋ ወራሽነትም ቢሆን ከመኳንንቶቹ መካከል ለአልጋው የሚቀርቡትና ልዑል እንኳን ሳይባሉ የቀሩት የንጉሥ ሚካኤል ሥላሴ በወንድ ልጅነት ቀጥታ መስመር ላይ የነበሩት እነ ልጅ ታዬ ጉልላቴና ደጃዝማች ማሞ ሥዩም በሕይወት ነበሩ። በተጨማሪም ሌሎች የልጅ ልጆችም በብዛት እንዳሉ ይታወቅ ነበር።

በራስ ተፈሪና በንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ሹመት ላይ ከመኳንንቶቹ መካከል ግምባር ቀደሙና የመንግሥት ግልበጣውን የመሩት ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ነበሩ። ከዚህም ሌላ ደጃች ተፈሪ የፈረንሳይኛ ቋንቋ በማወቃቸው ከውጭ አገር ዲፕሎማቶች ጋር መግባባት ፈጥረው ስለነበረ ውስጥ ውስጡን ብዙ ድጋፍ አግኝተውበታል።

መጨረሻ ላይ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ደጃች ተፈሪን ካደላደሉ በኋላ እያደር አንዳንድ ሰዎች ላይ የሚፈጸመውን ድርጊት ስላልወደዱት ደስተኛ አልነበሩም። ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ አንድ ቀን ሊጋባ በየነ እንዲገረፍ መበየኑን ሰምተው ፈረሳቸውን አስጭነው ቢሄዱ ሊጋባ በየነ ተገርፈው ደረሱ። የዚህን ጊዜ “ወይ ጉድ ቁጭ ብለን የሰቀልነውን ቆመን ማውረድ አቃተን“ ብለው ተረቱ።





ራስ ተፈሪ መኮንን

ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ብልህና ዘዴኛ በመሆናቸው አባ መላ በሚል ቅጽል ስም ይታወቃሉ። ዕድሜያቸው ገፍቶ በ1919 ዓ.ም ሲሞቱ የሳቸውን 15,000 ጦር ራስ ተፈሪ ተረክበው ኃይላቸውን አጠናከሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ አከራካሪ ሆኖ የቆየው “ራስ ተፈሪ ዕውነት በአዋጅ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ተብለው ተሹመዋል ወይስ በጉልበት ነው ሥልጣኑን የወረሱት?” የሚለው ጉዳይ ነው። የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ “የኢትዮጵያ ታሪክ” በሚለው መጽሐፋቸው ላይ “ሰነድ መርምረን ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መባላቸውን ልናገኝ አልቻልንም” ብለዋል። ነገሩን እንዲሁ ሲመለከቱት በአገር አስተዳደር ልምድ የሌላትን ንግሥተ ነገሥት ብለው ሲሾሙ ልምድና ትምህርት ያለውን አልጋ ወራሽ ብሎ መሾም በውስጠ ታዋቂነት ባለሙሉ ሥልጣን እንደማለት ይቆጠራል ቢባል ያወዛግባል። ሆኖም የነበረው ችግር ሹመቱ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ሰዎች ቀደም ሲልም የልጅ ኢያሱን መሻር እንዲሁም አዲሱን ሹመት አለመቀበልና ንግሥቲቷ እያሉ ከአልጋወራሹ ትዕዛዝ መቀበል ያልተለመደ አሠራር መሆኑም ጭምር

ነበር። በዚህም የተነሳ ጥቂት መኳንንቶች ሹመቱን ባለመቀበል የተገረፉና የታሰሩ ነበሩ።

ራስ ተፈሪ አስተዋይ ስለነበሩ ችግር እንዳይፈጠር አንዳንድ ትልቅ ጉዳይ ሲኖር ንግሥቲቱን አስፈቅደውና አስረድተው ሥራቸውን ይሠሩ ነበር። ይሁንና አንዳንድ መኳንንቶች ንግሥቲቱን እየመከሩና ልባቸውን እያሸፈቱ በአንዳንድ ሃሳብ ላይ ችግር እየተፈጠረ ራስ ተፈሪ የማስረዳትና የማሳመን ተጨማሪ ሥራ ነበረባቸው።


በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ የልጅ ኢያሱን መሻር አልቀበልም ብለው የተቃወሚቸው የንጉሥ ሚካኤል ጦር መስበቅ በሸዋ ሲሰማ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ በፍጥነት እቴጌ ጣይቱን ለማማከር ወደ እንጦጦ ሄዱ። እቴጌ ጣይቱም ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስን ሲመክሩ "ሚካኤል ችኩል ነው፣ እዚሁ ይመጣል፣ ጠብቁት፣ ወታደሩን መንገድ አታስመቱት" ብለው መከሯቸውና እንደተባሉት አደረጉ። በራስ ልዑል ሰገድ የሚመራ ቀዳሚ ጦር ንጉሥ ሚካኤልን ለመከላከል ተልኮ በወሎ ጦር ተደመሰሰ። በመሃሉ ሙሉ ዝግጅት ተደርጎ ሲጠበቁ ንጉሥ ሚካኤል እንደተባለው ወደ ሸዋ ስለገፉ ሰገሌ ላይ በፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ዘዴኛነት ተሸንፈው አንኮበር እስር ላይ እንዳሉ በዓመቱ አረፉ።

ይሁንና ብዙ ወጣት ምሁሮች የልጅ ኢያሱን መሻር ባለመቀበላቸው የተገረፉም፣ ወደ ዳር የተገፉም ነበሩ ከመኳንንቶችም መካከል ያኮረፉ ቢኖሩም ምንም ለማድረግ አልተቻለም። ቀጥሎም ልጅ ኢያሱን ፈልጎ ማሰር፣ የልጅ ኢያሱን ባለሚሎች ቅስም መስበርና ከሥልጣን ማባረር ሲሆን በእነሱም ምትክ አዳዲስ ሰዎች መተካት ቀዳሚ ሥራቸው ነበር።

አቤቶ ኢያሱን ከሹመት አውርዶ ወይዘሮ ዘውዲቱንና ደጃዝማች ተፈሪን ለማሾም በተደረገው ሽኩቻ ለመኳንንቶቹ መሣሪያ ኾነው የነበሩት መሃል ሰፋሪ ወይም የመንግሥት ጦር በ1910 ዓ.ም ሌላ አድማ መቱ። ይኸውም በ1889 ዓ.ም በአፄ ምኒልክ የተሰየሙትንና በአቤቶ ኢያሱ ጊዜ በተጨማሪ የተሾሙትን ወይም የተዛወሩትን ሚኒስትሮች ከጦር ሚኒስትሩ ከፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ በስተቀር ወንጅለው ይሻሩልን አሉ። ራስ ተፈሪ ይህንን ሤራ ቢጠሉትም በፊት የተሠራውን ሥራ ስለሚያውቁ ሚኒስትሮቹን ሻሩና ለጥቂት ጊዜ ሹሞች መድበው ራሳቸውም በሥራ ተጠመዱ።



በመጨረሻ ሕግና ደንብ አውጥተው ለእያንዳንዱም ሚኒስትር ቢሮና አማካሪ አድርገው አዳዲስ ሚኒስትሮች ሾሙ። ዳኞች እንደፈለጉ መፍረዳቸው ቀርቶ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በማውጣትና ፍርድ ቤት በማቋቋም በደንቡ መሠረት ሥራው ሁሉ እንዲሠራ አደረጉ። አስከትሎም የባሪያን ንግድ የሚከለክል ሕግ ከማወጃቸው በተጨማሪ ነፃ የወጡ የባሮች ልጆች በወታደርነት ትምሕርት ቤት እንዲገቡ ተደረገ። አገሪቱ ሕገ መንግሥት ስላልነበራት ይኸው እንዲረቀቅ ተደርጎ በ1922 ዓ.ም እንዲጸድቅ ኾነ።



ማተሚያ መኪና ( በሰው ጉልበት የሚሠራ )

በምባኔ ሃብት በኩል ምንም እንኳን የሕትመት ሥራ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ቢጀመርም ራስ ተፈሪ አዲስ የማተሚያ መኪናዎች ከጀርመን አገር አስመጥተው በግዕዝና በአማርኛ መጽሐፍት ማሳተም ጀመሩ። በተከታታይም ጋዜጦች ታተሙ። በዘመኑ የማተሚያው መሣሪያ በኤሌክትሪክ ሳይሆን በሰው ጉልበት ይንቀሳቀስ ነበር። ይህ ማተሚያ ቤት ጣሊያንን ለማስወጣት እናግዛለን ብለው የመጡት እንግሊዞች አወላልቀው ሊወስዱት ሲሉ አርበኞች ራስ መኮንን ድልድይ ሥር አድፍጠው በኃይል ከመወሰድ አድነውታል። ማተሚያ ቤቱም የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት በመባል እስከ አሁን ያገለግላል። በ1916 ዓ.ም

ራስ ተፈሪ በአልጋ ወራሽነታቸው አውሮፓን በጎበኙበት ወቅት የሕትመት ሥራ በማስፋፋታቸው የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ዕውቅና ሰጥቶ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አበርክቶላቸዋል።



ራስ ተፈሪና ቤኒቶ ሙሶሊኒ

በዲፕሎማሲው በኩል በ1916 ዓ.ም አውሮፓን ለመጎብኘት ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት፣ ራስ ሥዩምና ሌሎች ችግር ይፈጥራሉ ብለው የሚጠራጥሩዋቸውን መሳፍንቶችና መኳንንቶች በማስከተል በጅቡቲ በኩል ወደ አውሮፓ ተጉዘዋል። የጎበኙዋቸውም አገሮች ግብጽ፣ ኢየሩሣሌም፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ስዊዘርላንድ፣ እንግሊዝ፣ ግሪክ፣ ቤልጅየምና ስዊድን ሲሆን ጀርመንን ግን ለመጎብኘት ቢፈልጉም የመመለሻቸው ጊዜ በመድረሱ ሳይጎበኙ ቀርተዋል። አንዱ የሄዱበት



ምክንያት ለኢትዮጵያ የባሕር በር ለመጠየቅ ነበር። ጥያቄያቸው ግን ጥሩ ምላሽ አላገኘም። ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር በተደረገው ጦርነት በምርኮ የተወሰዱትን ቅርሳ ቅርሶች እንዲመለሱላቸው ጠይቀው ነበር። ሊመለሱ ሲሉ በስንብት ጊዜ የእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ 6ኛ የአፄ ቴዎድሮስን ትልቁን ዘውድ ለመመለስ የእንግሊዝ መንግሥት ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸላቸው። በተረፈ አንዳንድ የጽሕፈት ማተሚያ መኪና፣ አቶሞቢሎች፣ የውኃ ቧንቧዎች፣ አይሮፕላንና መጽሐፎች እንዲላክላቸው ግዥውን ፈጽመው ተመልሰዋል።



# ምዕራፍ ፲፩

## የራስ ተፈሪ አነጋገሥ

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱና ራስ ተፈሪ በመግባባት አብረው ለመሥራት ቢፈቅዱም በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች የማያግባባ ሁኔታ እየፈጠሩ ለማጋጨት ይጥሩ ነበር። ሆኖም ራስ ተፈሪ ንግሥትን እያስፈቀዱ በመስማማት ማንኛውንም ነገር እየሠሩ አብረው ቆዩ። ንግሥተ ነገሥትም ወሬኞች መጥተው ሹክ ሲሏቸው እስቲ ራስ ተፈሪን አማክረዋለሁ እያሉ በጥንቃቄ ኖረዋል። ወደ መጨረሻ ግን ንግሥቲቱ እየከፋቸው የሄደው ራስ ተፈሪን እንዲያነግሡ በተጠየቁበት ወቅት ነው። "እስቲ ላስብበት ጊዜ ስጡኝ" ብለው እንኳን ቢጠይቁም "ዛሬውኑ እሺ ካላሉን አይሆንም" ብለው አስገደዷቸውና ምርጫ ስለሌላቸው ተስማሙ። ከዚህም ሌላ የንግሥናው ሥነ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን መሆን አለበት የሚለው ክርክር ሲነሳ በንግሥቲቱ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

በመጨረሻ ተፈሪን ለማንገሥ ሲስማሙ "ዘውድ የምጭንለት እኔ ንግሥቲቱ ነኝ እንጂ እኔ እያለሁ ሌላ ንጉሥ በቤተ ክርስቲያን አይነግሥም፣ ደንቡም ሥርዓቱም አይፈቅድም" ብለው አሻፈረኝ አሉ። ተጨማሪ ችግር ሆኖ ያገኙት ደግሞ ራሳቸው ንግሥተ ነገሥት ቢሆኑም ያው የሸዋ ንግሥት ስለሆኑ ራስ ተፈሪን የሸዋ ንጉሥ ብለው ለመሾም የማይቻል ስለኾነና የሌላ ግዛት ንጉሥ ብለው ቢሾሙዋቸው ተፈሪ ሥራቸውን ትተው የሚሄዱ ስለመሰላቸው ነበር። በኋላ ግን የሌላ ግዛት ንጉሥ ብለው ቢሾሙዋቸውም አዲስ አበባን ጥለው ለመሄድ እንደማይገደዱ ታወቀ። ራስ ተፈሪ ንጉሥ ተብለው ለመሾም የሥልጣን መረባቸውን ዘርግተውና ኃይል ተሰምቷቸው ስለነበረ በንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ላይ አድማ አስነስተው በማስጨነቅ



እንዲሾሟቸው ለማስገደድ ችለዋል። በመሆኑም በመጨረሻ ላይ የጎንደር ንጉሥ ተብለው መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም ራስ ተፈሪ ዘውድ ተጫነላቸው።

የንግሥናው ሥነ ሥርዓት በቤተ ክርስቲያን ሳይሆን መሆን ያለበት በቤተ መንግሥት ነው ብለው ንግሥቲቱ ቢያሳምኑም በሕዝብ ፊት መታየትንና መከበርን ስለፈለጉ ልክ ንጉሥ ሲባሉ ሠረገላ አስቀርበው ወደ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ጸሎት ካደረሱ በኋላ ወደ ላይ ግቢ ሄደው ግብር አበሉ።



ንጉሥ ተፈሪ መኮንን

ተፈሪ ንጉሥ ተብለው ዘውድ ሲደፉ የአባታቸውን የራስ መኮንንን ግቢ ለቤተ መንግሥትነት ስለመረጡ የምኒልክ ቤተ መንግሥት የታች ግቢ

ወይም ትልቁ ግቢ ሲባል የንጉሥ ተፈሪ ቤተ መንግሥት ደግሞ የላይ ግቢ ወይም ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ተብሎ ተጠራ። በመሠረቱ ይህ ግቢ ንጉሥ ተፈሪ ከአባታቸው የወረሱት እንደመሆኑ መጠን የግል ሃብት እንጂ የመንግሥቱ ርዕሰ ብሔር መቀመጫ ቤተ መንግሥት አልነበረም። ስለኾነም ምንም ንጉሥ ቢሆኑም መቀመጫቸውን የግላቸው ቤት ውስጥ አድርገው የመንግሥቱን ሥራ ትልቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ ማድረግ ይችሉ ነበር። ዋናው ቤተ መንግሥት ውስጥ ርዕሰ ብሔርዋ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ስለሚኖሩ ሁለተኛ ቤተ መንግሥት በአንድ ከተማ ውስጥ ተመሠረተ። በተለይ ደግሞ ንጉሥ ተፈሪ ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ የአባታቸውን ቤት ቤተ መንግሥት አድርገው ቢቀሩም ዋናውን የምኒልክ ቤተ መንግሥት እንደ ጽሕፈት ቤትና የዙፋን ችሎት አድርገው እንደቀጠሉበት የታወቀ ነው። ከታህሣሥ 1953 ዓ.ም የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በኋላ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ውስጥ ብዙ ደም በመፍሰሱ ወደእዚያ ለመግባት ስለተጠየፉና በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት መኖር ስለጀመሩ የአባታቸውን ቦታ ከዓመት በኋላ በፈቃዳቸው ለዩኒቨርስቲ ሰጡ።



ራስ ጉግሣ ወሌ

ንግሥቲቱ በፊትም ሥልጣናቸው የተወሰነ ስለነበረ ይባስ ብሎ ተፈሪ ንጉሥ ከተባሉ በኋላ ንግሥቲቱን ደጅ የሚጠናና ግብርም የሚበላው የሰው ቁጥር ቀነሰ። ለሥላምታም የሚጠይቋቸው እንደ ተቆርቋሪዎች ስለሚታዩ በይበልጥ ደግሞ ሹመት ፈላጊ ከሆኑ ብቅ ለማለትም ተቸገሩ።

ተፈሪ ንጉሥ ተብለው የተሾሙት መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ.ም ሲሆን ሥራቸውን እየሠሩ እያለ ንጉሠ ነገሥት የሚሆኑበት ጊዜ መድረሱ ይታወቅ ጀመር። ጥቅም ፈላጊ ሁሉ አሁን አትኩሮቱ ወደ ተፈሪ ስለኾነ ዕውነትም የመንግሥቱ ሥልጣን እጃቸው እንደገባ ተገነዘቡ። ሆኖም የሥልጣን አወሳሰዳቸውን የሚጠሉ ብዙ ሰዎች መኖራቸው ቢታወቅም



በይበልጥ ዋንኛው አኩራፊ የንግሥት ዘውዲቱ ባለቤት የነበሩትና የጎንደር አገረ ገዥ ራስ ጉግሣ ወሌ ነበሩ።



ደጃች አያሌው ብሩ

በወቅቱ የጥብቅና ትምሕርት የነበረው የኢጣልያ ቆንሲል ራፋኤል ዲ ላውሮ የሚባል ጎንደር ውስጥ ተቀማጭ ሆኖ ራስ ጉግሣን ወዳጅ ለማድረግ መሬት ተከራይቷቸው እያለ የተፈሪን ወደ አውሮፓ ሥልጣኔ ማዘንበል እየጥላላ ያጫውታቸው ነበር። በመሃሉ የራስ ጉግሣን አጎት ደጃች አያሌውን ንጉሥ ተፈሪ በሹመት በማባበል ራስ ጉግሣን አብረዋቸው እንዲወጉና ጎንደርንም ከግዛታቸው ጋር እንዲደርቡ ቃል ገብተው አሳመኗቸው። ራስ ጉግሣ ወደ አዲስ አበባ ሲጠሩ አልመጣም በማለታቸው ራስ ሙሉጌታ ጦር ይዘው ሊወጉዋቸው ሄዱ። ንጉሥ ተፈሪ የጎንደርን ሕዝብ 'ራስ ጉግሣን ከረዳህ ከመሬትህ ትነቀላለህ' ብለው ስላወጁ ጦርነቱ ሲጀመር ራስ ጉግሣ ብቻቸውን ቀሩና ተገደሉ። ደጃች አያሌውም ከራስ ጉግሣ ሞት በኋላ እሾማለሁ ብለው ሲጠብቁ ሌላ ሰው ተሹሞ መሳቂያ ሆኑ። የጎንደር ሰውም

"አያሌው ሞኙ፣
ሰው አማኙ፣ ሰው አማኙ"

ብሎ ዘፈነባቸው።



ራስ ሙሉጌታ ይገዙ

በዚህ ጦርነት የደበዘዘ ጎንደር ሕዝብ ራስ ጉግሣን ባለመርዳቱ እያዘነና ሲሞቱ ረግመውናል በማለት እስከ አሁን እየተጸጸተበት ነው። በዚህም ምክንያት በቅርቡ ገንዘብ አዋጥቶ በ1987 ዓ.ም ደብረ ታቦር ላይ ተዝካራቸውን አውጥቷል።

መጋቢት 22 ቀን 1922 ዓ.ም ራስ ጉግሳ ተገድለው ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ከሁለት ቀን በኋላ መጋቢት 24 ቀን 1922 ዓ.ም አነር በሚባል ስዊድናዊ የቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ሃኪም መርዝ በመርፌ ወግቷቸው ተገደሉ እየተባለ ተወራ። ሕዝቡ ይኸንን ሁኔታ ለመግለጽ የሚከተለውን ግጥም ገጠመ።

ድሮም በቢታቸው ድመት ነው አጥፊያቸው
ዛሬም ንግሥቲቱን አነር ገደላቸው



ሐኪም አነር

ስለሞታቸው የሚወራ ሌላ አባባልም አለ። ይኸውም "ንግሥቲቱ የስኳር በሽታ ታማሚ ስለነበሩ የተወዳጅ ባላቸውን መገደል እንደሰሙ ይወድቃሉ። ሃኪም አነር ሁኔታቸውን ተመልክቶ 'በቀዝቃዛ ውሃ እንዳታጥቧቸው' ብሎ ከሄደ በኋላ ተፈሪ መጥተው በቀዝቃዛ ወሃ እንዲታጠቡ ሰላዘዙ ታጠቡና ወዲያው ሞቱ" ተብሎ ከንቲባ ገብሩ ደስታ በሚባለው መጽሐፍ ገጽ 223 ላይ ሄንሪ ደ ሞንፍሬድ የሚባለውን ፈረንሳዊ ደራሲ በመጥቀስ ጽፏል።

በንግሥቲቱ አሟሟት ዙሪያ የተሰጡት አስተያየቶች የተለያዩ ቢሆኑም ንግሥቲቱ የስኳር በሽታ እንደነበረባቸው የታወቀ ነው። ከዚህም በላይ በጊዜው የነበሩበት ሁኔታ ጭንቀት ወሰጥ ሊጥላቸው የቻለ እንደነበረ ግልጽ ነው።

በንግሥቲቱ ሞት ማግሥት መጋቢት 25 ቀን 1922 ዓ.ም ንጉሥ ተፈሪ ንጉሠ ነገሥት መባላቸው ታወጀ።

የሴቲቱ ንጉሥ ዳዊን ትታነሳ
ይማክሩባታል ተፈሪና ካሣ
ሼህ ሁሴን ጅብሪል





# ምዕራፍ ፲፰

# ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ንጉሥ ተፈሪ በአዋጅ ንጉሠ ነገሥት የተባሉት ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በሞቱ ማግሥት መጋቢት 25 ቀን 1922 ዓ.ም ነው። የንጉሠ ነገሥትነቱ ክብረ በዓል የተከናወነው ግን ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም ሲሆን የኸወም የውጭ አገርና የአገር ውስጥ እንግዶች በተገኙበት አዲስ አበባ በሚገኘው በመናገሻ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ንግሣቸው ተከብሮ ነው።

አፄ ምኒልክም ሊሞቱ ሲሉ መኳንንቱን በመሃላ አስረው ሥልጣኑን ለልጅ ልጃቸው ቢያወርሱም ተፈሪ እንደሚወስድበት ጥርጣሬ ነበራቸው። አንድ ቀን ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ስለዚሁ ጉዳይ ሲወያዩ እቴጌ ጣይቱ "ተፈሪ ሳይወስድበት አይቀርም" ሲሉ አፄ ምኒልክ "እግዚአብሔር የሰጠውን ማንም አይወስድበትም" ብለው ተናግረው ነበር ይባላል። እንዲያውም የፈረስ ስም ለሁለቱም ሲያወጡ ልጅ ኢያሱን 'አባ ጤና' ሲሉ ተፈሪን 'አባ ጠቅል' ብለው ሰየሙ ይባላል። እንደተባለውም መጨረሻ ላይ ተፈሪ ንጉሠ ነገሥት ተብለው አልጋውን ወረሱ።

ቀደም ባሉት ዘመናት ይኖሩ የነበሩት ንጉሦች ራሳቸው የንጉሦች የበላይ ኾነው በሥራቸው በየክፍለ አገሩ እንደአካባቢው ትውፊት ንጉሥ፣ የበላይ ባላባት፣ ቆሮ በመሾም ይገብርላቸዋል። እምቢም ካሉ በምትካቸው ሌሎች ይሾሙ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ጀምሮ ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ሌላ ንጉሥ አልተሾመም። እንዲያውም የነበሩትን ባላባቶች በተቻለ ሥልጣናቸው እየተሸረሸረ እንዲጠፉ ተደረጉ። ለምሳሌ የንጉሥ አገሮች ሸዋ፣ ጎንደር፣ ስሜን፣ ትግራይ፣ ከፋ፣ ወላይታ ሲሆኑ

የባላባት አገሮች ደግሞ ጎጃም፣ አፋር፣ ሱማሌ፣ ወሎ፣ ሊሙ ወዘተ.. ናቸው።



ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ



ልጅ ኢያሱ አባቱን ንጉሥ ብሎ በወሎ ቢሾምም በባላባት የሚተዳደር አገር ነበር። ጎጃም ላይም አፄ ዮሐንስ ራስ አዳልን ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ብለው ሾሙዋቸው። ከዚያ በፊት ግን በባላባት የሚተዳደር አገር ነበር። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም ልጅ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ንጉሥ ባይባሉም ጎጃምን ሲገዙ ኖሩ። ራስ ኃይሉም ንጉሥ ባለመባላቸው ተቀይመው ይመስላል ዕድል ባገኙ ቁጥር ንጉሠ ነገሥቱን እየከዱ ለኢያሊ ዘመን ጎጃምን አስተዳድረዋል። ሆኖም ጥፋት ተገኝቶባቸው ተሽረው መጨረሻ ላይ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ በግዞት ቆዩ።

በኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ ላይ ከባላባቶችም ኾነ ከጎሣ መሪዎች ከነሥልጣናቸው የቀሩት የአፋሩ የበላይ ባላባት ቢትወደድ አሊሚራህ ሃንፍሬ ብቻ ነበሩ። ሌሎቹ ግን በሙሉ በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ ሥር የሚተዳደሩ ኾኑ። ስለኾነም ብዙ አኩራፊ በየአገሩ ቢኖርም ያንኑ ያህል ደግሞ ሹመት ፈላጊና አረባጅ ተፈጠረ። ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውጋት ሲያስብ "ጊዜው አሁን ነው ምክንያቱም ብዙ አኩራፊ ስላለ ለንጉሠ ነገሥቱ ሕዝቡ በአንድ ልብ አይተባበርለትም" ብሎ ገምቶ ነበር።



# ምዕራፍ ፲፩

# ጃንሆይ እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ

ተፈሪ ከ1909 ዓ.ም እስከ 1921 ዓ.ም ለአሥራ ሁለት ዓመት በአልጋ ወራሽነት፣ ለአንድ ዓመት በንጉሥነት፣ ቀጥሎም ከ1922 ዓ.ም እስከ ማይጨው ጦርነት ድረስ በንጉሠ ነገሥትነት ለስድስት ዓመት በድምሩ ለአሥራ ዘጠኝ ዓመት፣ አያሌ መልካም ሥራዎችን ለመሥራት ሞክረዋል። ከነዚህም መካከል ቀዋሚ ሠራዊት ለማቋቋም የገነት ጦር ትምሕርት ቤትን ከፍተው ኦሥልጣኞችን ከቤልጅግ በማስመጣት ዘመናዊ የወታደር ሥልጠና በማስጀመርና በመንግሥት ሥራ አካሄድም ዘመናዊነትን የተላበሰ አሠራር እንዲመሠረት አድርገዋል።


አርግጥ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት የመጀመሪያውን ጥረት ያደረጉት አፄ ምኒልክ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም። ምናልባት እንደ ተፈሪ በልጅነታቸው የውጭ አገር ትምሕርት ቀስመውና የተደላደለ ሥልጣን ይዘው ለብዙ ዘመን የማስተዳደር ዕድል አግኝተው ቢሆን ኖሮ በሳቸው ቀናነትና ብልህነት አገሪቱን ምን ያህል እንደሚያራመዷት ለመገመት አያስቸግርም። ተፈሪም የሥልጣን አያያዛቸው ሁኔታ ባይወደድም ከአራት ዓመት ውጣ ውረድ በኋላ ለሥልጣን መብቃታቸውን የሚያውከውን ሁሉ በዘዴ ተወጥተውታል። ኋላ ቀር በሆኑ ሰዎች የተከበቡ ስለነበሩም አሠራሩ ላይ አንዳንድ ችግሮች ገጥሟቸው ነበር። ይሁንና በአሥራ ዘጠኝ ዓመት ውስጥ በአጠቃላይ ሲታይ መልካም ሥራ ሠርተዋል።

በ1890 ዓ.ም አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት አባል መሆኗን በማጎተማቸው ቢያረጋግጡም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ የዓለም ማኅበርተኛ እንድትሆን ደጃዝማች ናደው ተሰማን በመሪነት፣ አቶ



ኅሩይንና አቶ ፋሲካን በረዳት መልዕክተኛነት ተልከው ነሐሴ 1 ቀን 1914 ዓ.ም ጄኔቫ በሚገኘው የዓለም ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) ዋና ጽሕፈት ቤት ተገኝተዋል።

## የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባልነት



የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ማኅበርን ራስ ተፈሪ ሲጎበኙ (1916 ዓ.ም.)

መልዕክተኞቹ ሲመለሱ አባል ለመሆን አገር ውስጥ መሻሻል ያለባቸው ነገሮች እንዳሉ ተነገራቸው። እነዚህም የሕገ መንግሥት አለመኖርና እንደ ባርያ ንግድ የመሳሰሉ የሰብዓዊ መብት አለመጠበቅ ጉዳዮች ነበሩ። ይሄንኑ ለማስተካከል ተቀዳሚ ሥራ አድርገው የተነሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ማውጣትና የዳኞች አመዳደብ አስከትሎም የሕገ መንግሥት መረቀቅንና የመንግሥት ሥራ አካሄድን መልክ ማስያዝ

ነበር። ሌላው ደግሞ ምክር ቤት ማቋቋምና የሚኒስትሮችን ሥራ መመሪያ ማውጣትና ጽሕፈት ቤት መስጠት ነበር። ስለኾነም ምንም እንኳን ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ አዋጆች ቢወጡም በመጨረሻ የባሪያን ሽያጭ የሚያግድ ሕግ ወጣ። ሆኖም የባርያ ንግድ እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ እንደነበረ ሰዎች ይናገራሉ። እነዚህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ካስተካከሉ በኋላ በሚያዝያ ወር 1915 ዓ.ም በይፋ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል ኾነች።

*አንበሳው ታረርጌ ጊደራቱ ተኛ (ከወሎ)*
*ታለም መንግሥታት ጋር ኾነ ማበርተኛ*
*ሼህ ሁሴን ጅብሪል*

## ትምህርት

ኢትዮጵያ ውስጥ የቀለም ትምህርት አሰጣጥ ጥንታዊ ሲሆን ክርስቲያኑ በገዳማት፣ በቤተ ክርስቲያን ጥግና በአንዳንድ ባለጸጋ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሃይማኖት መምህሮች ዙሪያቸው ተማሪዎችን አስቀምጠው እያንዳንዱ ተማሪ ከደረሰበት እየተማረ አስተማሪው እያዳመጠ ያርመዋል። ለአንድ ተመልካች በዚያ መሰሉ ጫጫታ መካከል አስተማሪው ተማሪዎቹን ለይቶ መምራቱ ያስገርማል። ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ተማሪዎችም ትምህርት ቤቱን ሳይሆን የታወቁ አስተማሪዎችን ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ። ኑሯቸውንም የሚገፉት ከአካባቢ ነዋሪ እየቀፈፉ ወይም እየለመኑ ነው። ስለዚህም የቆሎ ተማሪ ተብለው ይታወቃሉ። ሙስሊሙም በመሠረቱ በዚሁ ዓይነት ጫጫታ በተሞላ ትምህርት ቤት ወይም መድረሳ ወይም የቁርዐን ትምህርት ቤት ልጆቹን ያስተምራሉ።

ይሁንና አንዳንድ ሚስዮናውያን ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመክፈታቸው በክፍል ውስጥ እያንዳንዱ ተማሪ መቀመጫና የሚጽፍበት ጠረጴዛ ተደርጎለት በዘመናዊ መልኩ ይማር ጀመር። አጼ ምኒልክ አዲስ አበባ ላይ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤትን በ1897 ዓ.ም ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተው ቀጥሎ ጃንሜዳ አጠገብ ንጉሥ ሚካኤል መኖሪያ ቤት አስከትለውም ሙሴ ኤልግ መኖሪያ ቤት የነበረውና እሪ በከንቱ አሁን የቀይ ባሕር ሆቴል የሆነው ቦታ ላይ ተዛውሮ እንደቆየ በ1905 ዓ.ም አሁን በሚገኝበት አባታችን ሠፈር አራት ኪሎ ተመሠረተ። ሕዝቡ ልጆቻችን የሚሲዮናውያኑን ሃይማኖት ይከተላሉ (ይኮተልካሉ)



ብሎ እንዳይፈራ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ አሥራ አምስት ግብጻዊ መምህሮች አስመጥተው ችግሩን አቃለሉ።



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪዎችን ሲጎበኙ

ከሚታወሱት ነገሮች አንዱ ይማሩ ለነበሩ ተማሪዎችም ምግብ ተሠርቶ ከቤተ መንግሥት ይመጣላቸው ነበር። ከምግቡም ጋር ለማወራረጃ ብርዝ አብሮ ይቀርብላቸዋል። ንግሥት ዘውዲቱ የአባታቸውን አርአያ በመከተል የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት የሚባለውን አሁን የአራዳው ቴሌ መሥሪያ ቤት የኾነውን ከፈቱ። ልጅ ኢያሱ ንጉሥ ሚካኤል ሠፈር ወይም ጊሚራ ሠፈር ውስጥ አሠርተውት ሳይጨርሱት የቀረውን ትምህርት ቤት በ1917 ዓ.ም ራስ ተፈሪ አስጨርሰው በስማቸው የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ብለው ከፈቱት። አከታትለውም የእቴጌ መነን፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ሌሎችም ትምህርት ቤቶችን አሠሩ። ቤተሰብ ልጁን ወደ ፈረንጅ ትምህርት ቤት አልልክም እያለ ባስቸገረበትም ወቅት ራስ ተፈሪ

ለወላጆች እስከ ወርቅ ሽልማት ድረስ በመስጠት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ አድርገዋል።

በንግሥት ዘውዲቱ ዘመን የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከግብጽ የመጡትን አስተማሪዎች ደበደቡና ችግር ተፈጠረ። የጠቡ መንስዔ ግብጻቹ አስተማሪዎች ስድባቸውና ቅጣታቸው ያልተለመደ ዓይነት ስለነበረ ተማሪዎቹን አስቆጥቷቸው የወሰዱት እርምጃ ነበር። ንግሥት ዘውዲቱ ከውጭ አገር የመጡ አስተማሪዎችን መደብደቡ ብልግና ስለመሰላቸውና ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስን በማክበር ጭምር ተማሪዎቹን ከትምህርት ቤት እንዲወገዱ ቢፈልጉም በራስ ተፈሪ ዘዴኛነት ተማሪዎቹ ትምህርት ከሚያቆሙ ይልቅ ወደ ውጭ አገር ሄደው የጀመሩትን ትምህርት እንዲጨርሱ ተከራክረው በማሸነፋቸው ብዙዎች ተማሪዎች ውጭ አገር ተላኩና ነገሩ እልባት አገኘ። በዚያን ወቅት ከሄዱት ተምረውና ተመልሰው አገራቸውን በከፍተኛ ደረጃካገለገሉት መካከል ለመጥቀስ ያህል ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ፣ ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታዕዛዝ፣ ራስ ቢትወደድ እንዳርጋቸው መሳይ፣ አርቲስት አገኘሁ እንግዳና ወዘተ.. የመሳሰሉ ነበሩ።

ከጠላት ወረራ በኋላም ተማሪዎች ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ሲላኩ ለስንብት ቤተ መንግሥት ሄደው ንጉሣዊ ምክር ይሰጡቸው ነበር። እንዲሁም ሲመለሱ ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው እያንዳንዳቸውን ምን እንደተማሩ ይጠይቋቸውና ያበረታቷቸዋል። እስከ 1955 ዓ.ም ድረስ ማንኛውም ምሁር ትምህርቱን ጨርሶ አገሩ እንደተመለሰ ቤት ፈልጎ እስኪያገኝ ድረስ ሙሉ ወጭው በመንግሥት ተሸፍኖ እቴጌ ሆቴል እንዲቀመጥ ይደረግ ነበር። ቤትም ፈልጎ ሲያገኝ አርማ ጋራዥ ከሚገኘው የመንግሥት ንብረት ሙሉ የቤት ዕቃ ይታዘዝለታል። ተማሪው እየበዛና በዚህ ሁኔታ ለመቀጠል ባልተቻለበት ጊዜ የሦስት ወር ደመወዙ ያለ ወለድ በብድር መልክ ተሰጥቶት ቤቱን አሟልቶ ብድሩን በሦስት ዓመት ከፍሎ ይጨርሳል። አገር ውስጥ የ8ኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ተፈትነው ለሁለተኛ ጊዜ ለማለፍ ያልቻሉ ተማሪዎችን በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና በግብርና ሚኒስቴር ከእሥራኤል መንግሥት ጋር በተቋቋመ የእርሻ ልማት ላይ እንዲሠማሩ ይደረግ ነበር። ሌሎቹን ደግሞ በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ጀርባ በሚገኘው አሁን



የትምህርት ሚኒስቴር ማስ ሚድያ የሆነው የሙያ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት (Vocational School) ልዩ ሥልጠና ይሰጣቸው ነበር። በተጨማሪም አንዳንዶቹን በእቴጌ መነን የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት በማስገባት ልዩ ትምህርት ተምረው ሲመረቁ በየትምህርት ቤቱ የእጅ ሥራ መምህር ሆነው እንዲሠማሩ ይደረግ ነበር።


እንደዚሁም በሁለተኛ ደረጃ ፈተና ጥሩ ውጤት ያላመጡትን ተማሪዎች በኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤት በሚስተር ካርማይክል ዲሬክተርነት የአንድ ዓመት የመምህራን ኮርስ እየተሰጠ በየክፍለ አገሩ በአስተማሪነት ይላኩ ነበር። በዚህ ሁኔታ ተማሪ በፈተና ወድቆ ሥራ ፈት እንዳይሆን ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ከ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እንደዚህ ዓይነት ጥረት ባለመቀጠሉ ከ1960ዎቹ መጀመሪያ አንስቶ በተለይ የሁለተኛ ደረጃ ፈተና ወዳቂ በዝቶ ሥራ ፈትነት በመብዛቱ ለነበረው የሕዝብ አመጽ ዓይነተኛ መንስዔ ሆኗል።

ጃንሆይ ለትምህርት የሰጡትን ተቀዳሚነት የተመለከቱት ራስ ካሣ "ይኸንን የድሃ ልጅ አስተምረህ! አስተምረህ! በኋላ አይገዛልህም" ብለው ቢመክሯቸውም ራስ ተፈሪ አልሰሟቸውም። ይሁንና መንግሥታቸውን መጨረሻ ላይ ያናጋው የተማሪ ንቅናቄ መሆኑ ታይቷል።

ሰማንያው ያልቅና ቲሆን ሦስት ዓመት
ተማሪ አፈረሰው የተፈሪን ቤት
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

## የመንግሥት ወታደር

አፄ ቴዎድሮስ መደበኛ ወታደር ለመመሥረት ባሰቡ ጊዜ ተጨማሪ ግብር ለመሰብሰብና ሳያርስ በየቤተ ክርስቲያኑ እያሸረገደ የሚበላውን ለመቀነስ ስላሰቡ ከካህናት ተጣሉ። ይኸ ሕልማቸው በአፄ ምኒልክ ዘመን ለማዕከላዊ መንግሥት የሚታዘዝ በመላው ኢትዮጵያ የተሰራጨ የመንግሥት ወታደር ቢቋቋምም፣ በሠለጠነ ሁኔታ እንደ አውሮፓ ሥርዓት የተደራጀ የጦር ኃይል ግን ሊቋቋም የቻለው ጊዜውን ጠብቆ በተፈሪ ዘመነ መንግሥት ሥራ ላይ ሊውል ችሏል።



የክብር ዘበኛ የመንግሥት ወታደር

ራስ ተፈሪ ከቤልጅግ ጥቂት መኮንኖች አስመጥተው በሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት አቋቁመው ዘመናዊ ሠልፍና የወታደር ሥነ ሥርዓት ማስተማር ጀመሩ። የቤልጅግ መኮንኖቹም በትምህርት አሰጣጣቸው ደህና ቢሆኑም በሙሉ ሰላይ እንደነበሩ ተደርሶበት ነበር። ምክንያቱም የቤልጅግ መንግሥት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ምኞት የነበራት ስለሆነ ነው። በጠላት ዘመን የፈረሰውን የወታደር ተቋም እንደገና ገንብተው እስከ ጦር አካዳሚ ድረስ በመክፈት ኢትዮጵያን በጠራ የጦር ኃይሏ በመላው አፍሪካ እንድትታወቅ ያበቁት ጃንሆይ ናቸው።

ሕዝቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ በዓል ጊዜ በደንብ ልብስ የተሽቆጠቆጠ የወታደር ሠልፍ በማየቱ ተደሰተ። ወታደሮቹ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ በማይጨው ጦርነት ባሳዩት ተሳትፎ ተመስግነዋል። የሚለብሱት የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) ከራስ ቆብ አንስቶ የእግር ገምባሌ ላይ ያልቃል። ስለኾነም አንዳንድ ጫማ ያላቸው ይጫሙ እንጂ አብዛኛው ባዶ እግር ነበር። ጣሊያን የማይጨው ምሽጉን ካጠረበት ዘዴ አንዱ የወይን ጠጅ ጠርሙስ ሰባብሮ የኢትዮጵያኖችን እግር



ለመቆራረጥና ለማስቀረት ብሎም ምሽጉን ለመከላከል ነበር። ታዲያ መደበኛውም ኾነ ወዶዘማቹ ወታደር ጫማ ባይኖረውም ያሳየውን ጥንካሬ የተመለከተ ጣሊያን "የአበሻ እግር ከትሬንታ ኳትሮ ጎማ ይጠነክራል" አለ ይባላል። ከ25 ዓመት በኋላ በወሬ የሰሙትን የአበሻን እግር ጥንካሬ የጣሊያን ሰዎች ሮም ከተማ ላይ አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮጦ ማራቶን ሲያሸንፍ ተመልክተዋል።

ተፈሪ ታትሞት ታለች በሕይወት
አገሯን ወሰደው የጦር ሠራዊት
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

## ሕግና ደንብ


ራስ ተፈሪ ከአልጋ ወራሽነት አንስቶ እስከ ጣሊያን ወረራ ጊዜ ድረስ መሻሻልን ለማምጣት ብዙ ጥረዋል። ዳኞች የሚፈርዱት እንደፈለጋቸውና መጥቀስም ከፈለጉ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከፍትሐ ነገሥት ከመሆኑ የተነሳ አሠራሩ ጥንታዊ የሆነ እጅ መቁረጥን የመሳሰሉ የግፍ ብይኖች በሰው ልጅ ላይ ይፈጸም ነበር። ይህንን ለማስቀረት ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አጽፈው ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል። በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያትና ደጃዝማች ይገዙ በሃብቴ ያረቀቁት ሕገ መንግሥት ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም ታወጀ። በተጨማሪም የሕግ መምሪያንና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቶችን ጥቅምት 23 ቀን 1924 ዓ.ም ከፈቱ።

በጊዜው ሚኒስትሮች ሥራቸውን የሚሠሩት በገዛ ቤታቸው ስለሆነ የአሠራሩ ሁኔታ መልክ አልነበረውም። በዚህ የተነሳ ጽሕፈት ቤት ከፍተውላቸውና አማካሪዎች ቀጥረውላቸው በቀለጠፈ መልኩ የመንግሥት ሥራ ሁሉ መሥራት ተጀመረ።

## ሌሎች ሥራዎች

ራስ ተፈሪ በምኒልክ ዘመን የተጀመረውን የአውሮፓን ዕውቀት በስፋት ወደ አገር ለማስገባት ጥረት አድርገዋል። ራስ መኮንን ሐረር ላይ፣ እቴ ምኒልክ አዲስ አበባ ላይ ካሠሯቸው ሁለት ሆስፒታሎች በተጨማሪ ራስ ተፈሪ ቤተ ሳይዳ ሆስፒታልን አዲስ አበባ ውስጥ

አሠሩ። የዚህ ሆስፒታል ስም ከተፈሪ መንገሥ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል እየተባለ ይጠራ ጀመር። ከዚያም ደርግ ሥልጣን እንደያዘ የካቲት 12 ሆስፒታል ብሎ ቀይሮታል።



ጃንሆይ በ1924 ዓ.ም ፓርላማ ሲከፈት

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ፍልውሃ የሚገኘውን የንግሥት ዘውዲቱ የማዋለጃ ሆስፒታልን አስቀድመው አሠርተው ነበር። ምንም እንኳን ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ዙፋኑ ላይ ለአሥራ ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ቢቀመጡም አብዛኛው ሥራ ይሠራ የነበረው በአልጋ



ወራሹ ራስ ተፈሪ መኮንን ነበረ ማለት ይቻላል። ቢሆንም አንዳንዱ ሥራ የሚሠራው ንግሥተ ነገሥት ራስ ተፈሪን ትዕዛዝ እየሰጡ ነበረ የሚሉም አልታጡም። በተለይ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ አሠሩት ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው በ1917 ዓ.ም የተሠራውና ዘመናዊ የሆነው ሴትና ወንድ በአንድነት ይማሩበት የነበረው ትምህርት ቤት ሲሆን ይኸውም በስሜ ሳይሆን በቅዱስ ጊዮርጊስ ይሰየም ያሉት አሁን የአራዳ የቴሌኮሙኒኬሽን መሥሪያ ቤት ያለበት ቤት ውስጥ ነው። ከጠላት ወረራ በኋላ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ተመልሰው ሲከፈቱ ይህ ትምህርት ቤት ባለመከፈቱ አንዳንድ ሰዎች ቅሬታቸውን ሲገልጹ መጀመሪያውኑ ጃንሆይ ያልከፈቱት ስለነበረ ነው ይላሉ።





በ1937 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ብር

በተጨማሪም ንግሥቲቱ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችንና የአፄ ምኒልክን ሓውልት አሠርተዋል። እንዲሁም ንግሥት ዘውዲቱ በምስላቸው ገንዘብ እንዲታተም እንዲያዙ ሲጠየቁ "የአባቴ ምስል ያለበትን በእኔ ምስል አልተካም" በማለታቸው የአፄ ምኒልክ ብር በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምስል በ1937 ዓ.ም እስከተተካ ድረስ ቆይቷል።

ጃንሆይ ንፋስ ስልክ እየተባለ የሚታወቀውን የስልክ ማዞሪያ ከማሠራታቸውም ሌላ የአርመን ሙዚቀኞችን አስመጥተው የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር፣ ተፈሪ ማርሽና ሚሊተሪ ማርሽ እንዲዘመር አደረጉ። በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርን

አውሮፓዊ ዜማ ያቀነባበሩት አርመናዊው ካቮቴን ናልባንዲያን ሲሆኑ የአማርኛው ግጥም ደራሲም በዚያን ዘመን የነበሩ ቀኛዝማች ዮፍታሔ ንጉሤ መሆናቸው ይታወቃል። ዮፍታሔ ንጉሤ በተጨማሪ የሚታወቁት "የኛማ ሙሽራ" እና "ሙሽራዬ" እየተባሉ የሚዘመሩትን የሠርግ ዘፈኖች በማውጣታቸው ጭምር ነው። በተጨማሪም የብዙ ተውኔት አፍላቂም ነበሩ።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር


ሙሴ ናልባንዲያን

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ
በአምላክሽ ኃይል በንጉሥሽ
ተባብረዋልና አርበኞችሽ
አይነካም ከቶ ነፃነትሽ
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ
አትፈሪም ከጠላቶችሽ
ድል አድራጊው ንጉሣችን
ይኑርልን ለክብራችን!

በእንግሊዝኛ የተተረጎመውም እንደሚከተለው ነው
Oh, Ethiopia be Happy;
By God's Power and your Emperor
Your Freedom Fighters are united.
Your Freedom will never be in trouble;
Your mountains are so great you must
not be afraid of your enemies.
The winner is your Emperor;
He lives for our Glory.


ዮፍታሔ ንጉሤ

በተጨማሪም "ደሙን ያፈሰሰ" የሚለው ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) ሲወጣና ሲወርድ የሚዘመረውና "ተፈሪ ማርሽ" ተዘጋጅቷል።

ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ
ደሙን ያፈሰሰ ልቡ የነደደ
በአርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ
ንጉሡን አገሩን ክብሩን የወደደ



ነፃነቱን ይዞ መልካም ተራመደ
ገናናው ክብራችን ሰንደቅ ዓላማችን
ያኮራሻል አርበኝነታችን

ሰንደቅ ዓላማ ሲወርድ
ተጠማጅ አርበኛ ባገር መውደድ ቀንበር
ገዳይ ድል አድራጊው ደም መላሽ ወታደር
አንቺን እያሰበ ይጓዛል ሲፎክር
ሰንደቅ ዓላማችን የነፃነት አገር
ገናናው ክብራችን ሰንደቅ ዓላማችን
ያኮራሻል አርበኝነታችን

ተፈሪ ማርሽ
መንግሥትን ለዳዊት ቡራኬን ለሴም
እንዳንተ የተሰጠው ማንም ሰው የለም
እንደ ማቱ ሳላ እንደኑ አብርሃም
ዕድሜህን ያርዝምው እመላክ በለንለም
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ቤዛ
ክብራችን ጌታችን ይዞ ሰንደቅ ዓላማ
ይዞ ሰንደቅ ዓላማ ያገራችን ቤዛ
ተነሳታ ብትቆም እሱን ተመርኩዛ
ሕዝቡንም ደስ እለው አገኘ ሰላም
ከዚህ የበለጠ ምን አለን ዓለም
የዘውዱ ምልክት ያገራችን ግርማ
ክብራችን ጌታችን ይዞ ሰንደቅ ዓላማ

ቀደም ብለው ዳግማዊ ምኒልክ ያደርጉት እንደነበረው በሐምሌ ወር 1942 ዓ.ም በየትምህርት ቤቱ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ለወጡ ተማሪዎች ቤተ መንግሥት ውስጥ በሚሸለሙበት ወቅት የሥነ ሥርዓቱ ማብቂያ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ሊሰማ ሲል ንጉሠ ነገሥቱና በበዓሉ ላይ የነበሩ ሁሉ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ቆሙ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ምትክ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ሙዚቃ ጓድ መሪ የነበሩት ፈረንሳዊው ሚስተር ኮምሳ በስህተት ተፈሪ ማርሽን ሲያሰማ ንጉሠ ነገሥቱ ተናደው እንዲቋርጥ በቁጣ አዘዙ። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘምሮ ሥነ ሥርዓቱ አበቃ። የጓዱ መሪ ግን በ48 ሰዓት ውስጥ ጓዙን ጠቅልሎ ከአገር ለቅቆ እንዲወጣ ተደርጎ በምትኩ

ሚስተር ዱዙዛ የሚባል ህንዳዊ ተተኩ። እንግዲህ ይህን መሰሉ እርምጃ ጃንሆይ ምን ያህል ንቁ እንደነበሩ ከማሳየቱም በላይ በዘመኑ ሥነ ሥርዓት እንዴት ይከበር እንደነበረ ያሳያል። በተጨማሪም ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣም ኾነ ሲወርድ ሰው ሁሉ ተሽከርካሪም ጡምር ባለበት ቀጥ ብሎ መቆም ግዴታው ነበር። ባርኔጣም ያደረገ ሁሉ አውልቆ በደረቱ ላይ ይይዛል።

## አስተዳደር

የመንግሥት ቀረጥ በየአካባቢው ላሉ ገዥዎች ገቢ መሆኑ ቀርቶ ለማዕከላዊ መንግሥት መግባት እንዲጀምር በማድረጋቸው ብዙ መኳንንቶች እያኮረፉ ቢያስቸግሩም ራስ ተፈሪ ችግሩን ማደሪያ መሬትና የማዕረግ ስም በመስጠት መቋቋም ችለዋል።

ዘመኑ የሚያመጣው የአውሮፓ ሥልጣኔ ያለ ችግር መግባት ጀመረ። ግሩንዲንግ ሬዲዮና መኪና በብዛት ጨመረ። አይሮፕላንም መጣ፣ መብራትም በአውራ ጎዳናዎች ተተከሉ፣ በየመንግሥት መሥሪያ ቤትና በየመኳንንቱ ቤት በሰፋት የኤሌክትሪክ መብራት ገባ። የሥልጣኔ ጭላንጭል እየታየ ሄደ። በየመንገድ ዳር ያለውን መብራት በመመልከት የአዲስ አበባ ነዋሪ

"አበራ ፋኖስ አበራ ፋኖስ
ከፊት በር አንስቶ ለገሃር ድረስ" ብሎ ገጠመ።

በነዚህ በ19 ዓመት ውስጥ የተሠራው ኢትዮጵያን ከአንድ ጥንታዊ ከኾነ የመንግሥት አስተዳደር ወደ ዘመናዊ ቅርጽ ያለው አስተዳደር ለመሸጋገሯ ግልጽ የኾነ ማስረጃ ነው። እርግጥ ከተሠራው መካከል ምኒልክ ያልጀመሩት ነገር ቢኖር ዘመናዊ ወታደር ማደራጀትና አይሮፕላን ማስመጣት እንጅ ሁሉንም ነገር ጀማምረውታል።

መኪና ለመንዳት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ አፄ ምኒልክ ሲሆኑ በብስክሌት ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ ይንሸራሸሩ የነበሩት ሴት ደግሞ በዚያ ግዙፍ ሰውነት እቴጌ ጣይቱ ነበሩ። እንዲሁም ራስ ተፈሪ ሐረር በነበሩ ጊዜ ጫማ በማድረግና ቢስኪሌት በማሽከርከር ይታወቁ ነበር። አፄ ምኒልክ በተፈጥሮ ብልህና የሜካኒክ ችሎታ



ዝንባሌ ስለነበራቸው በዘመናቸው አይሮፕላን መጥቶ ቢሆን ኖሮ ለመንዳት እንደሚሞክሩ አያጠራጥርም።



ፋርማሲ ከጠላት ወረራ በፊት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዞች ተጋብዘው የመን ውስጥ የእንግሊዝ ወታደር ልምምድ ሲመለከቱ እሳቸውና ራስ እምሩ በጦር አይሮፕላን እንዲበሩ ስለተደረገ በአይሮፕላን የበረሩ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ሁለቱ መሆናቸው ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጃንሆይ አይሮፕላን አገር ውስጥ እንዲገባ ፥ ይፈልጉ ነበርና ከየአገሩ አይሮፕላን እየገዙ መጀመሪያ የቤተ መንግሥት ሾፌሮችን በኋላ ደግሞ የተማሩ ልጆችን ለአይሮፕላን አብራሪነት አሠማርተው ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ኢትዮጵያ አሥራ አምስት አይሮፕላኖች ነበሩት። እነዚህም አይሮፕላኖች ዋናው ሥራቸው መልዕክት ማድረስና አንዳንዴም የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ማጓጓዝ ነበር። የጃንሆይ አጎት ደጃች ወልደ ሥላሴ ለመንግሥት ሥራ ደሴ ደርሰው ሲመለሱ አደጋ ተፈጥሮ ቀበቶ ሳያስሩ ቆመው ሲጮኩ አይሮፕላኑ ሲያርፍ ራሳቸውን በኃይል ስለመታቸው ከተሳፋሪዎቹ መካከል እሳቸው ብቻ በአደጋው ሞቱ። ስለኾነም በአይሮፕላን አደጋ

በመሞት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ እኚሁ የራስ መኮንን ወንድም ደጃች ወልደ ሥላሴ መሆናቸው ነው።

ይሁንና ከሰው ሰው ብርታት፥ ስለሚለይ የተፈሪ እርጋታና ዘዴኛነት በዚህ ዘመን ውስጥ ለተደረገው የመንግሥት የአስተዳደር ቅርጽ እመርታ ከማስገኘቱም በላይ የዘመኑን ሥልጣኔ በማስተዋወቅ ረገድ በጣም የሚያስመሰግን ውጤት እንደሰጠ ሁኔታው ይነግራል።






# ምዕራፍ ፲፯

# የጣሊያን ፕሮፓጋንዳና ዝግጅት

ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ለመያዝ በማቀድ ከአፄ ቴዎድሮስ በኋላ በነገሡት በአፄ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመን አሰብ ላይ መሬት ገዝቶ ያዘ። ቀጥሎም ምፅዋን ይዛ ከነበረችው ግብጽ ላይ እንግሊዝ ምፅዋን ያዘበት ነበርና ጣሊያን ወደ ምፅዋ ወታደር ሲያስገባ በተፈጠረው ቅሬታ እንግሊዝ አስታራቂ በመሆን የጣሊያን ይዞታ እንዲጸድቅላት ያጋፍር ነበር። ጣሊያን ደጋው ላይ ለመስፋፋት ሲሞክር በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የባሕር ነጋሽ ገዥ የነበሩት ራስ አሉላ ዓላማውን አኮላሹበት። ሆኖም ተስፋ ባለመቁረጥ በሹመት ከተከፉ ባላባቶች ጋር በመመሳጠር ሥር እየሰደደ ሄዶ አፄ ዮሐንስ ከድርቡሽ ጋር ባካሄዱት ጦርነት እንደሞቱ፥ ደጋውን የባሕር ነጋሽ ግዛት ያለ ምንም ተቀናቃኝ ያዘ። ጣሊያን እንደገና ከተደራጀ በኋላ መላውን ኢትዮጵያ ለመውረር በ1888 ዓ.ም ሞክሮ አድዋ ላይ በጦርነት ስለተሸነፈ ትልቅ ውርደት ተከናነበ። የሚቀጥለውን ጦርነት ለማሸነፍ አርባ ዓመት ሙሉ ሲዘጋጅ ኖሮ ወረራውን ለመጀመር በተዘጋጀበት ጊዜ አስቀድሞ በጋዜጦች ላይ አውሮፓ ውስጥ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ጀመረ። ከሚያካሂደውም የፕሮፓጋንዳ ጦርነት አንዱ የስም ለውጥ ማድረግ ነበር።

ጣሊያኖች የባሕር ነጋሽን ግዛት ከያዙ ጀምሮ ኤርትራ የሚል ስም ሰጥተውት ይኖሩ ነበር። ኤርትራ የጥንት የቀይ ባሕር ስም ሲሆን ከላቲን የመጣ ቃልና ትርጉሙም ቀይ ማለት ነው። ባሕሩ ቀይ ባሕር የተባለበት ምክንያት ውኃው ላይ የሚያድጉትና አሳዎች የሚመገቧቸው

አረማሞዎች (አልጌ) ቀይ ስለሆኑና ባሕሩን ሲመለከቱት ቀይ መስሎ ስለሚታይ ነው።



ፋሽስት ቤኒቶ ሙሶሊኒ

ኢትዮጵያ ከአምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የይፋ መጠሪያ ስሟ "ኢትዮጵያ" ሲሆን በጣሊያን ጋዜጦች ግን የሚጠቀሰው "አቢሲኒያ" የሚለው ስም ነበር። አቢሲኒያ አረቦች ለኢትዮጵያ ካወጡላት ሃበሻ ከሚለው ስም የተወሰደ የአውሮፓውያኖች አጠራር ነው። ሃበሳት ቀደም ብሎ በምዕራብ ሳዑዲ አረብያ ቀይ ባሕር ዳር የሚኖሩ ከጥቁር ጋር የተደባለቁ የአረብ ነገዶች ስም ነበር። የቃሉም ትርጉም ድብልቅ እንደማለት ነው። ከጊዜ ብዛት ይህ ስም ባሕሩን ተሻግሮ በአረቦች ዘንድ የኢትዮጵያውያን መለያ ስም ኾነ።



እንደሚታወቀው አንድ ልጅ ሲወለድ ስም ለራሱ አያወጣም። የተወለደው ልጅ እናቱ ወይም ቤተ ዘመድ ባወጣለት ስም ይጠራል። ስሙን ከወደደው ስሜ ነው ብሎ እስከ ዕድሜ ልኩ ይጠራበታል። ካልወደደው ግን እንዳይጠራበት ይከላከላል። አንድን ሰው ባልወደደው ስም ያለፍላጎቱ የሚጠራው ግን እንደ ስድብ ያህል ስለሚቆጠር ያቃቅራል። አገርም በአንድ ታሪክ አጋጣሚ ስም ይወጣላትና ስሜ ነው ብላ ከተቀበለችው ይፋ ታደርገዋለች። እንዲሁም ሕብረተ ሰብም ባልወደደው ስም መጠራት አይኖርበትም። አለበለዚያ አጨቃጫቂና የግጭት መንስዔ ሆኖ ይገኛል። ለምሳሌ ነፍጥ በትግርኛ ትርጉሙ ጠብመንጃ ማለት ነው። የመንግሥት ወታደሮችም በአፄ ምኒልክ ዘመን ነፍጠኛ ይባሉ ነበር። መደበኛ ወታደር ሲቋቋም ይህ ስም ጡረታ የወጡ ተዋጊዎች ስም ኾኖ ቀረ። በዛሬ ጊዜ አማራን ነፍጠኛ እያሉ የሚጠሩ አማሮችን ለማስከፋት አስበው ቢኾንም አማሮች ግን የሚያፍሩበት ባይኾንም መንፈሱን የሚወዱት አይመስልም። ነፍጠኛ የሚለውን ቃል ጉልተኛ ሥርዓትን ለመግለጽ የተጠቀሙበት ከኾነም ሁሉም ጎሣ ውስጥ ጉልተኛ ስለአለ የተለየ ጎሣን ብቻ አይመለከትም። ስለኾነም አማራዎች ነፍጠኛ፣ ኦሮሞዎች ጋላ፣ ወላይታዎች ወላሞ፣ አፋሮች አዳል፣ ወዘተ.. ብላችሁ አትጥሩን ስለሚሉ ይህ ጥያቄ መከበር አለበት። ከፍ ሲልም ኢትዮጵያውያን ሃበሻ ሲሏቸው እጅግም እንደማይደሰቱ ሁሉ አሜሪካኖችም ያንኪ ሲሏቸው ይጠሉታል።

ኢትዮጵያን ያስተዳድሩ የነበሩት ነገሥታት የኢትዮጵያ ንጉሥ ወይም ንጉሠ ነገሥት እያሉ በይፋ ያውጁ ነበር እንጂ የሃበሻ ንጉሥ ነን ብለው አላወጁም። ኢትዮጵያም በ1915 ዓ.ም የዓለም ማኅበር (ሊግ ኦፍ ኔሽን) አባል ሆና "ኢትዮጵያ" ተብላ መመዝገቧ እየታወቀ ጣሊያኖች በ1933 ዓ.ም ተሸንፈው ኢትዮጵያን እስከለቀቁ ድረስ አገሪቱን የይፋ ስሟ እያለ አቢሲኒያ እያሉ ይጠሩ ነበር። ሃበሻ የሚለውን ስም በይፋ ኢትዮጵያውያኖች ባይቀበሉትም የሚጠሉት ስም ስላልኾነ በጊዜ ብዛት በልማድ በንግግራቸው ውስጥ እያስገቡ የሃበሻ ልብስ፣ የሃበሻ ምግብ እያሉ እንደሚጠቀሙበት አይካድም። ቅሬታ የፈጠረው ጣሊያኖች ስሙን የአጠቃቀማቸው መንፈስ እንጂ የሚያሳፍር ኾኖ አልነበረም።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በግሪክኛ ቋንቋ ፀሐይ የለበለበው ፊት ማለት ሲሆን ብሉይ ኪዳን ሲተረጎም ግብጾችና አይሁዶች ኩሽ

የሚሉትን ቃል ተክቶ የገባ የግሪክ ቃል ነው። እንዲሁም ደግሞ ቀደም ብሎ የግሪክ ታሪክ ጸሐፊዎች ብዙ የጻፉበት ስም ስለኾነ የሕዝቦቹን ገናናነትና ትልቅነት ገልጸውበታል። በቅርብም ታሪክ ቢሆን ነጭን ያሸነፈ የጥቁር ሕዝብ መሰያ ስለኾነ ይህ ስም በተነሳ ቁጥር ማንኛውም ጥቁር ስሜቱ ከፍ ይላል። ስለዚህም ጣሊያኖች ይህንን ስም ለመጠቀም አልፈለጉም።

ከቀን ብዛት ኢትዮጵያውያንም ተለማምደውት አቢሲኒያ ወይም ሃበሻ የሚለውን ቃል መጠቀም ሲጀምሩ በ1944 ዓ.ም ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በውጭ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ቆንስላዎች፣ ለጋሲዮኖችና ኤምባሲዎች አቢሲኒያ ወይም ሃበሻ የሚለውን አጠራር እንዳይጠቀሙበት፤ ማሕተማቸውንና የደብዳቤ ርዕሳቸውን በሙሉ እንዲያርሙና ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ብቻ እንዲጠቀሙ የፅሑፍ ትዕዛዝ አስተላልፏል። በአሁኑ ጊዜ ታሪካዊ ስም እየመሰላቸው ጠላት ለፕሮፓጋንዳ ይጠቀምበት የነበረውን አቢሲኒያ የሚለውን ስም እንደ ታሪካዊ ስም በመቁጠር ሲጠቀሙበት ይታያል።

ሁለቱ የታሪክ ጠላቶች ግብጾችና እንግሊዞች በአፄ ምኒልክ ጊዜ በአዲስ አበባ ውስጥ አንድ ባንክ ሲያቋቁሙ ካላጡት ስም አቢሲኒያ ባንክ ያሉት ባልታሰበና ባልተጠበቀ መንገድ ማንኳሰሳቸው ነበር። በተለይ ሕዝቡን ዕዳ ውስጥ እያስገባ የከተማውን ቦታ ሁሉ በመውረስና ለአውሮፓውያኖች በመሸጥ ቀስ በቀስ በሠላማዊ መንገድ አገሪቱን በተዘዋዋሪ የቅኝ ግዛት ለማድረግ ጥረት ማድረጋቸው ስለታወቀና ባንኩ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለከፋ እንዲዘጋ ተደረገ[12]።

ስም በማንኛውም ቋንቋ አጠራሩ አንድ ዓይነት መሆን አለበት። ሃበሻ የሚለውን አቢሲኒያ ብለው መለወጣቸው ለምን እንደሆነ አይታወቅም። እንግሊዞች የፈደላቸው አነባበብ ላይ ችግር እያለባቸው ከእኛ ወዲያ ለአሳር በሚል አስተሳሰብ ስህተታቸውን ለማረም አይሞክሩም። ስለሆነም ሃበሻ የሚለውን አቢሲኒያ፣ የሱስ የሚለውን ጂሰስ፣ ኒል የሚለውን ናየል፣ ሚካኤል የሚለውን ማይክል፣ አሁን ደግሞ ኢራክ የሚለውን አይራክ፣ እያሉ መጠሪያ ስምን እንደፈለጋቸው ያበላሻሉ። ጣሊያኖችም የእንግሊዞቹን አጠራር

[12] ጣይቱ ብጡል በቀኛ ታደሰ ዘወልዴ ገጽ 44



ከመከተል እኛ በምንጠቀምበት ዓይነት ሃበሻ ማለት በተገባቸው ይሻል ነበር። ለምሳሌ ኮት ደ ቯዋር የምትባለው አፍሪካዊ አገር አይቮሪ ኮስት በሚል ስም እንዳትጠራ በቅርቡ አስታውቃ ይኸው ማስተካከያ ጸንቶ በሥራ ላይ ውሏል።

በሥነ ልቡና ረገድ ደግሞ የሚጠሩበት ስም ቀላል አይሆንም። ለዚህም ነው እያንዳንዱ ወላጅ ልጅ በተወለደ ገዜ ስም ለማውጣት ሲቸገር የሚታየው። በዚህም ምክንያት ሃይማኖተኛው ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከቁርዐን፣ ውበትን አድናቂው ከተፈጥሮ፣ ጀግናው ገድልን የሚገልጽ ስም ሲያወጣ ይታያል። እዚህ ላይ በሃይማኖት ሰበብ ለልጆች የግሪክ፣ የእብራይስጥና የአረብ ስም ሲያወጣ የኢትዮጵያውያን ስም እየተረሳ መሄዱ በብዙ ሰው ዘንድ የተዘነጋ ይመስላል።

ጣሊያን በጦርነት አሸንፎ አገሩን ከመያዙ በፊት አንስቶ በፕሮፓጋንዳ ልክ እንደራሱ ግዛት አድርጎ ስለሚወተውት አውቀውም ሆነ አጥርተው የማያውቁ አውሮፓውያን ኢትዮጵያን የጣሊያን ቅኝ ግዛት አድርገው መጻፍም ጀምረው ነበር። ይኸ ሁሉ አገሪቱን ለመውረር የተደረገ ዝግጅት ነበር። እንኳን በዚያን ወቅት አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ በሕዝብ ግንኙነት ሥራ ኋላ ቀር ነች። በውስጥ የሥልጣን ሹዝግብ ምክንያት የጣሊያንን ጠላትነት እንደ ትልቅ ቁም ነገር የቆጠረው ስላልነበረ በወቅቱ በፕሮፓጋንዳም ይሁን በጦር ኃይል ለመከላከል ጥሩ ዝግጅት ባለመደረጉ፣ በተለያዩ ተንኮሎችና በዘመን አመጣሽ መሣሪያ ብልጫ ኢትዮጵያ በ1928 ዓ.ም በተካሄደው ጦርነት ተሸነፈች። የተዋጋችው በፊት ለፊት ከጣሊያን ጋር ሲሆን በተዘዋዋሪ ግን ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ጭምር ነበር። በስዊዝ ካናል ጣሊያን እንደልብ ወታደርና መሣሪያ እንድታሳልፍ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ሲፈቀድላት ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የጦር መሣሪያ እንዳይገባ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን እ.አ.አ. በ1930 ዓ.ም ላይ ስምምነት አድርገው ነበር። በሊግ ኦፍ ኔሽን የዓለም ማኅበርም አቤቱታው ምላሽ እንዳያገኝ ያደርጉ የነበሩት እንግሊዝና ፈረንሳይ ነበሩ።